ኣዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ
ADDIS MEDIA NETWORK

# አዲስ ልሳን

ቅጽ 32 ቁጥር 3534 | ቅዳሜ ነሐሴ 10 ቀን 2017 ዓ.ም | ዋጋው 10.00 ብር




### ከኃይል ምንጭነት ባሻገር

3



ፎቶ- ከገፀ ድር

ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ከፊል ገፅታ

### ዘመናዊው የግብይት ማዕከል በ4 ኪሎ

16



ፎቶ በመባጽዮን ሀ/ገብርኤል

በ4 ኪሎ የገበያ ማዕከል ለግብይት ከተዘጋጁ መካከል የፍራፍሬ ምርቶች ይገኙበታል

### ቡሄን የሚያስናፍቁ ክዋኔዎች

12



ፎቶ- ከገፀ ድር

ቡሄን ከሚያደምቁት ክዋኔዎች መካከል የወጣቶች አልባሳትና ሙልሙል ዳቦ ተጠቃሾች ናቸው

# የፋብሪካው የምርት ውጤት

## “ለማኑፋክቸሪንግ የወጪ ንግድ ከፍተኛ አስተዋፅኦ አለው”

የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)

- ጠቅላይ ሚኒስትሩ በሀዋሳ ኢንዱስትሪ ፓርክ የቶዮ የፀሐይ ብርሃን ኃይል ማመንጫ ፋብሪካን ጎብኝተዋል

7



ፎቶ- ከገፀ ድር

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በሀዋሳ ኢንዱስትሪ ፓርክ የቶዮ የፀሐይ ብርሃን ኃይል ማመንጫ ፋብሪካን ሲጎበኙ

# መዲናዋ እና ኮንፈረንስ ቱሪዝም የተወዳጀችበት ምስጢር

- ከተሞችን ለጉባኤ አስተናጋጅነት ከሚያስመርጣቸው መካከል ምቹ መሰረተ ልማት አንዱ እንደሆነ ተገልጿል

በስንታየሁ ምትኩ

“በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ርዕይ ያለው አመራር አስገራሚ ለውጥ እያስመዘገበች ወደምትገኘው አዲስ አበባ በመምጣቴ በጣም ደስ ብሎኛል፡፡ ለውጡ በዓመታት ውስጥ የመጣ ቢሆን ያን ያህል የሚደንቅ ላይሆን ይችላል፡፡ ነገር ግን በአዲስ አበባ በየሰዓቱ፣ በየቀኑና በየሳምንቱ በሚታይ መልኩ ለውጥ እየመጣ ነው፡፡”

ይህ ናይጀሪያዊው፤ ተሰናባቹ የአፍሪካ ልማት ባንክ ፕሬዝዳንት አኪንውሚ አዴሲና (ዶ/ር) ሰሞኑን በቢሾፍቱ አቅራቢያ ለሚገነባው አዲስ ዓለም አቀፍ አየር ማረፊያ የግንባታ ወጪ ድጋፍ ለማስተባበር ከኢትዮጵያ አየር መንገድ ጋር ስምምነት ባደረጉበት ወቅት ያደረጉት ንግግር ነው፡፡

በርግጥም አዲስ አበባ ከቅርብ ዓመታት

ወደ ገጽ 8 ዞሯል



ፎቶ- ከገፀ ድር

ለኮንፈረንስ ቱሪዝም ተመራጩ የአዲስ ዓለም አቀፍ ኮንቬንሽን ማዕከል

# የወንዞቹ ሁለት መልክ

- በከተማዋ እየተከናወኑ የሚገኙ የወንዝ ዳርቻ ልማቶች የከተማዋን ገፅታ በመቀየርና የአካባቢ ጥበቃን በማረጋገጥ በኩል ትልቅ ትርጉም እንዳላቸው ተመላክቷል

በመለሰ ተሰጋ

“በቀበና ወንዝ ዳርቻ ለአስር ዓመታት ያህል ኖሬያለሁ፡፡ እናም ቀበናን በጣም አውቀዋለሁ፡፡ በክረምት ከእንጦጦ ጋራ ስር ጀምሮ አሰሱን ገሰሱን እየጠራረገ የተከራየኳትን ደሳሳ ጎጆ እየታከከ ይወርዳል፤ ይነጉዳል፡፡ እኔ ደግሞ ከዛሬ ነገ ከነቤተሰቦቼ ጠራርጎ ወሰደኝ እያልኩ ክረምቱን በስጋት አሳልፋለሁ፡፡”

ወደ ገጽ 4 ዞሯል




አድራሻ +251 111 112 218 +251 111 267 266 www.amn.gov.et 5 kilo infront of St. Mary Church Addis Ababa Ethiopia

# ርዕሰ አንቀፅ



## የተሰሩ መሰረተ ልማቶች የኮንፈረንስ ቱሪዝም እድገቱ የጀርባ አጥንት ናቸው!

እነደ ሀገር ከጥቂት ዓመታት ወዲህ ለቱሪዝም ዘርፉ የተሰጠው ትኩረት አመርቂ ነው። ቱሪዝም በፖሊሲ ደረጃ እንደ አንድ የኢኮኖሚ ምሰሶ ተቆጥሮ ራሱን ችሎ እንዲቆም መደረጉ ዘርፉ ያልተገደበ እድገት እንዲኖረው አስችሏል፡፡ በሌላ በኩል ለዘርፉ እድገት ጉልህ ሚና ለሚጫወቱ መሰረተ ልማቶች ግንባታ ትኩረት ተሰጥቶ ተሰርቷል፡፡

በአዲስ አበባ በርካታ የመሰረተ ልማት ስራዎች ተከናውነዋል፡፡ በተለይ ‘ገበታ ለሸገር’፣ የኮሪደር ልማት እና የወንዝ ዳርቻ ፕሮጀክቶች የከተማዋን ገፅታ በማሳመርና ለጎብኚዎች የተመቸች በማድረግ የቱሪዝም ዘርፉ እንዲያንሰራራ ብሎም መሻገሪያ ከተማነቷ በመዳረሻነት እንዲቀየር አስችሏል።

እነዚህ መሰረተ ልማቶች አንዳንዶቹ በቀጥታ ከኮንፈረንስ ቱሪዝም ጋር የተገናኙ ናቸው፡፡ ለአብነት ሳይንስ ሙዚየም፣ አብርሆት ቤተ-መጻሕፍት፣ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት አዳራሽ ዕድሳት፣ አዲስ ዓለም አቀፍ የኮንቬንሽን ማዕከል፣ በኮሪደር ልማቱ የተከናወኑ ከተማዋን የማስዋብ ተግባር እና የወንዝ ዳርቻ ልማቶች በሚያስናዷቸው ሁነቶች አማካኝነት በቀጥታ እና በተዘዋዋሪ መንገድ ዘርፉን ያሳድጋሉ፡፡

እንጦጦ ፓርክ፣ የወዳጅነት አደባባይ፣ አንድነት ፓርክ፣ የመስቀል አደባባይ መልሶ ግንባታ፣ የብሔራዊ ቤተ መንግስት ዕድሳት፣ የብሔራዊ ሙዚየም ዕድሳት እና የዓድዋ ድል መታሰቢያ በራሳቸው ቀጥተኛ የቱሪዝም መዳረሻ የሚሆኑ ናቸው፡፡ እነዚህ ሀብቶች ከተማዋን ተመራጭ የቱሪዝም መዳረሻ አድርገዋታል፡፡

በተለይ የኮሪደር ልማት ስራ የአዲስ አበባን መልክ በአዲስ ሁኔታዎች በመግለጥ የጎብኚዎች ዐይን ይበልጥ እንዲያርፍባት አድርጓል፡፡ ይህም ከተማዋን የቱሪስቶች መሸጋገሪያ ሳይሆን መዳረሻ እንድትሆን አስችሏታል፡፡

እነዚህ ልማቶች መከናወናቸው ለከተማዋ በርካታ ዓለም አቀፍና አህጉራዊ ኮንፈረንሶችን የማካሄድ ዕድል ፈጥረዋል። በ2017 በጀት ዓመት ከ150 በላይ አህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ ኮንፈረንሶች፣ ኤግዚቢሽኖችና ኤክስፖዎች በመዲናዋ ተካሂደዋል፡፡

በቅርቡም ከሐምሌ 20 እስከ ሐምሌ 22 ቀን 2017 ዓ.ም ለሶስት ቀናት የቆየውን እና የተለያዩ ሀገራት መሪዎች፣ ሚኒስትሮች፣ የስራ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች የተሳተፉበትን ሁለተኛው የተባበሩት መንግስታት የምግብ ስርዓት ጉባኤም ከተማዋ አሰናድታለች፡፡

ከጷጉሜን 3 እስከ ጷጉሜን 5 ቀን 2017 ዓ.ም ደግሞ ኢትዮጵያ ሁለተኛውን የአፍሪካ የአየር ንብረት ለውጥ ጉባኤን ከአፍሪካ ህብረት ጋር በመተባበር ታስተናግዳለች፡፡ በጉባኤውም ከ20 ሺህ እስከ 25 ሺህ ሰዎች የሚሳተፉ ሲሆን፣ የ45 የአፍሪካ ሀገራትና የሌሎችም ሀገራት መሪዎች፣ የዓለም አቀፍ ድርጅቶች ሊቀ መናብርት፣ ዲፕሎማቶች፣ አምባሳደሮች፣ በዘርፉ የተሰማሩ ግብረ ሰናይ ድርጅቶች፣ ሲቪል ማህበራት፣ የልማት አጋሮችና የተለያዩ ባለድርሻ አካላት እንደሚሳተፉ ተነግሯል፡፡ ይኸን ግዙፍ ጉባኤ የማስተናገድ አቅም እንዳላት የታመነባት አዲስ አበባ ያላትን የኮንፈረንስ ቱሪዝም እምቅ ሀብት ተረድታ አስፈላጊ የሆኑ መሰረተ ልማቶቿን መገንባት ላይ ማተኮሯ ተገቢና መቀጠል የሚገባው ነው፡፡ እነዚህ የኮንፈረንስ ቱሪዝም የጀርባ አጥንት የሆኑ መሰረተ ልማቶችን መንከባከብ የሁሉም ዜጋ መሆኑ ልብ ሊባል ይገባዋል፡፡

# የእኔ እይታ

ይህ ገፅ ዜጎች በማህበራዊ፣ በኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ ሃሳባቸውን በነፃነት የሚያንፀባርቁበት ሲሆን ይህም የጋዜጣዋን የዝግጅት ክፍል አቋም አይገልፅም።

## አገልግሎቱን እየፈተኑ ያሉ ድሮች

**በሰናይ ምግባሩ**

አንድ የመንግስት ሰራተኛ በትንሹ 8፡00 ሰዓት መስራት ግድ ይለዋል። ሆኖም ይህን በውጤታማነት ከመጠቀም አንጻር ቀላል የማይባል ውስንነት እንዳለ የአደባባይ ሃቅ ነው። ለሻይ ተብሎ ወጥቶ ከአንድ ሰዓት ያላነሰ ጊዜ አባክኖ መመለስ፣ የምሳ ሰዓትን ተገን አድርጎ ከሰላሳ ደቂቃ ያላነሰ ሽራርፎ የመግባት፣ መውጫ ሰዓት ደግሞ “ሰርቪስ ተጠቃሚ ነኝ” በሚሉ እና መሰል ሰበቦች አስቀድሞ መውጣት በድግግሞሽ የሚታዩ ጉዳዮች ናቸው፡፡ ከዚህ ላይ በስራ ሰዓት ስብሰባ ማድረግ ሲጨመርበት አገልግሎት አሰጣጡ ላይ የሚያሳድረው አሉታዊ አስተዋጽኦ በቀላሉ የሚታይ አይደለም፡፡

ከሰሞኑ ለአንድ አገልግሎት ወደ መንግስት መስሪያ ቤት ተቋም ሄድኩኝ። አስቀድሜ ደርሼ የአገልግሎት መጀመሪያ ሰዓታቸውን ስጠባበቅ በኃላፊዋ መሪነት ሁሉም የመስሪያ ቤቱ ሰራተኞች በስራ መጀመሪያ ሰዓት ላይ ስብሰባ ላይ ተቀመጡ፡፡ ሰዓቱ በገፋ ቁጥር የተገልጋዩ ቁጥር እየጨመረ ቢመጣም የስብሰባውን ርዝማኔ ማሳጠር ግን አልተቻለም፡፡ የሁለት ዓለም ሰዎች እስኪመስሉ ድረስ ተገልጋዩ ተገልግሎ ለመመለስ ሲቁነጠነጥ፣ የተቋሙ ሰራተኞች ደግሞ ተራ በተራ እጃቸውን እያወጡ ሀሳባቸውን ማቅረብ ጀመሩ። እኔን ጨምሮ ለአገልግሎት የመጣው ሰው “ለስራ የሚያግዙ ናቸው ተብለው የሚታመኑ ስብሰባዎች ስራን በሚበድል መልኩ ማካሄድ ምን ያህል ተገቢነት አለው” በማለት እርስ በእርስ ሀሳብ መለዋወጥ ጀመሩ፡፡

ይህ የሚያሳየው አንድ ቁም ነገር አለ፡፡ መንግስት የአገልግሎት አሰጣጡን በቴክኖሎጂ ለማዘመን እየሰራ መሆኑን በተደጋጋሚ እየገለጸ ነው፡፡ በፌደራል ደረጃ የተጀመረው መሶብ የአንድ ማዕከል አገልግሎት የዚህ የተግባር ማሳያ ነው፡፡ ይህ ይበል የሚያሰኝ ነው፡፡ ነገር ግን ቴክኖሎጂ ብቻውን በቂ አይደለም። የአገልጋዩን የአስተሳሰብ አድማስ ማስፋት አማራጭ የሌለው መፍትሔ ነው ብየ አስባለሁ። “ደንበኛ ንጉስ ነው” ከቃል መሻገር፣ ባህልም መሆን አለበት፡፡ “የማገለግለው ሀገሬን፣ ህዝቤን ነው” የሚለው የተቆርቋሪነት ስሜት በልኩ ሊሰርጸን ይገባል፡፡

መንግስትም ይህ የአገልግሎት መስጫ ሰዓት እንዲሸራረፍ የሚያደርጉ ድሮችን በውል በማጤን ሊበጣጥሳቸው፣ ዘላቂ መፍትሔም ሊሰጣቸው ሊያበጅላቸው ይገባል። በስራ ሰዓት አስገዳጅ እስካልሆነ ድረስ ስብሰባ ማድረግ አይቻልም የሚሉ አይነት የሆነ ጊዜ ብልጭ ድርግም የሚሉ መልካም ነገሮች በአግባቡ መምራት እና ባህል ሆነው እንዲቀጥል ማድረግ ላይ ትኩረት ሰጥቶ መስራት ይጠበቅበታል። እንደዚህ ሲሆን የአገልግሎት መስጫ ተቋማት ለአገልጋዩም፣ ለተገልጋዩም ተናፋቂ ይሆናሉ። ተመሰጋግነን እንጂ ተጨቃጭቀን የምንለያይባቸው አይሆኑም፡፡ ፈልገን እንጂ ተገድደን ወይም እንጀራ ሆኖብን የምንውልባቸው አይሆኑም። በጥቅሉ በአገልጋይና ተገልጋይ መካከል ጤናማ ግንኙነት ለመፍጠር የአስተሳሰብ ለውጥ ላይ አበክሮ መስራት ዋነኛ ጉዳይ ሊሆን ይገባዋል ባይ ነኝ፤ እናንተስ?

አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ
ADDIS MEDIA NETWORK

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ እየተዘጋጀች

ዘወትር ቅዳሜ ወደ አንባቢያን
የምትደርሰው ይህች ጋዜጣ

ግንቦት 1985 ዓ.ም
ተመሰረተች

**አድራሻ**
አምስት ኪሎ ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ፊት ለፊት
በሚገኘው ማህበረ ቅዱሳን ህንፃ ጎን
ስልክ ቁጥር 0111-574923
ፖ.ሣ.ቁ 27080 code 1000
ፋክስ - 559368
addislisan1985@gmail.com

**የገበያ አገልግሎት እና የማስታወቂያ ዝግጅት ዳይሬክቶሬት**
ስልክ 0111 - 112218

**አታሚ**
ሜልባ ፕሪንቲንግ ፐብሊሺንግ ኤንድ ፓኬጂንግ ሼር ካምፓኒ

**ግራፊክስ ዲዛይን**
ዳንኤል ተስፋይ

**ሌይአውትና ዲዛይን**
ፍልሰታ አየለ

**የእርምት ባለሙያ**
ቸርነት ዋለልኝ
ገነት መላኩ

**የዕለቱ አዘጋጆች**
አብርሃም ገብሬ
ሄለን ጥላሁን
ለይላ መሀመድ

**ዋና አዘጋጅ**
ምህረቱ ፈቃደ
Mehretu@gmail.com
አድራሻ ለሚ ኩራ ክ/ከተማ
ወረዳ 3 የቤት ቁጥር 34/55

**ም/ዋና አዘጋጅ**
ሰውነት ኃ/ጊዮርጊስ
መለስ ተሰጋ

**ከፍተኛ አርታኢያን**
ደረጀ ታደሰ
ጊዜው አማረ
ስንታየሁ ምትኩ
ሳህሉ ብርሃኑ

# ከኃይል ምንጭነት ባሻገር

- **ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ የቱሪዝም ፀሐይ በኢትዮጵያ ሰማይ ከፍ ብላ እንድትታይ የሚያደርግ ነው**

**በመለሰ ተሰጋ**



ፎቶ- ከገፀ ድር

ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ከፊል ገፅታ

"ለድሃ በሽታ - የድሃ መድኃኒት አግኝተናል፡፡" ይህንን ያሉት እውቁ ኢትዮጵያዊ ሳይንቲስት ፕሮፌሰር አክሊሊ ለማ ናቸው፡፡ እኔም አባባላቸውን ለዛሬ ልዋስና እንደ ሀገር ሰቅዞ የያዘንን ድህነት የተሰኘውን በሽታ ነቅሎ የሚጥል ውበት፣ ጥበብ እና ታሪክ የናፈቃቸውን የዓለም ጎብኝዎችንም እየማረከ የሚያመጣ የህዳሴ ግድብን የመሰለ ፈዋሽ መድኃኒት አግኝተናል ልበል፡፡

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የታሪክ ምሁሩ ፕሮፌሰር ባየልኝ ጣሰው (ዶ/ር) እንዲህ ይላሉ "ዐባይ የዘመን እና የቀን አቆጣጠር፣ የስሌትና የአስትሮኖሚ ዕውቀት፣ የመስኖና የምህንድስና ጥበብ፣ የዕምነት፣ የሥነ ምግባር ሕግጋትና ደንቦች፣ የፍልስፍና ፈሊጥና አድማስ፣ በአጠቃላይም የመንፈሳዊና ቁሳዊ ብሂል... ሁሉ ከዐባይ ጋር በእጅጉ የተቆራኙ ናቸው፡፡"

ዐባይ የተፈጥሮ ስጦታ፣ ለሚኖሩበት ሁሉ ሲሳይ፣ ፀጋ፣ በጥልቀት ሲታይ ደግሞ የተፈጥሮና ባህል ስንኝት ትዕምርት ነው፡፡ እናም ዐባይ ለእኛ ስማችን ነው፤ ኢትዮጵያችን! አዎ! ዐባይን በኢትዮጵያ ብንመስለው የጥልቀቱ፣ የምጥቀቱ፣ የግዝፈቱና የረቂቅነቱ ምስጢር እጅጉን የሚደንቅ ነው፡፡ ፅናት ያበረታው፣ ህብረት ያገነነው፣ ዘመን የማይረታው ጀግና፣ ማንም የማይፈታው ቅኔ ነው፤ ዐባይ፡፡

ዐባይ ከግሼ ተራራ ከሰከላ አንጀት ፈልቆ መልሶ በግሼ ሜዳ ላይ ግልገል ዐባይን ሆኖ ይቦርቃል፡፡ ግልገል ዐባይ በግሼ ሜዳ ላይ እንዳሻው እየዘለለ በጣና ሐይቅ ላይ ሲንጎባለል አይጨንቀውም፡፡

ይህን ለዘመናት የማይሰለች ድንቅ የተፈጥሮ ተውኔት ያየ የሀገሬ ሰው....

"ዐባይ በጣና ላይ ይሄዳል ዝም ብሎ፣

አንተም ውሃ ነህ እኔም ውሃ ብሎ፡፡ "በማለት ተቀኝቶለታል፡፡ እናም ዐባይ በጣና ላይ ከፍ ብሎ ወደ ዐባይ ሸጥ ይንደረደራል፡፡

የዐባይ ፏፏቴ ጋ ሲደርስ ቁልቁል ይምዘገዘግና ደረቱን ገልብጦ ከሚጠብቀው ደንዳና ቋጥኝ ላይ ይፈጠፈጣል፡፡ ሽቅብ አየሩ ላይ ይበተንና ዳግም ወርዶ ወደ ዐባይ ሸለቆ ይገባል። በገናናው ሸለቆ እንደ ሙሽራ ታጅቦ በእናት ሀገር ምድሩ 800 ኪሎ ሜትሮችን ያህል የእናቱን ለም አፈር እየዘገነ ወደ ፊት ይነጉዳል፡፡

እናም ዐባይ እንኳን ዛሬ ቀርቶ ለዘመን ዘመናት ያልተለወጠው ይህ አስደማሚ ጉዞው በራሱ የተመራማሪዎችን፣ ደራሲያንን እና ዓለም አቀፍ ጎብኝዎችን ብቻ ሳይሆን የሀገሬውን ሰው ቀልብ የሚገዛ ድንቅ የተፈጥሮ ፀጋ ነው፡፡ ወዳጁን የናፈቀ የዐባይ ማዶ ጉብል "ዐባይ ጉደል ብለው አለኝ ለትሳስ የማን ሆድ ይችላል እስከዚያው ድረስ" እያለ በስስት የሚያማክረው ውብ የተፈጥሮ ፀጋ ነው፤ ዐባይ፡፡

በጅማ ዩኒቨርሲቲ የሆስፒታሊቲ እና የቱሪዝም ማኔጀመንት ትምህርት ክፍል ኃላፊና መምህር ደመቀ ክብሩም ይህን ሀሳብ ይጋራሉ፡፡ አሁን ዐባይ 240 ኪሎ ሜትሮችን ወደ እናት ምድሩ ተመልሶ ከዘመን ድካሙ አረፍ ብሏል። የአፍሪካውያን ትልቁ ግድብ ብቻ ሳይሆን ከዐድዋ ድል ቀጥሎ ገናናው ድል ሆኗል። ብዙዎችም 'ዳግማዊ ዐድዋ' እያሉ ያሞካሹታል፡፡

> **የዐባይ ጥልቀቱ፣ ምጥቀቱ፣ ግዝፈቱና ረቂቅነቱ ምስጢር እጅጉን የሚደንቅ ነው። ፅናት ያበረታው፣ ህብረት ያገነነው፣ ዘመን የማይረታው ጀግና፣ ማንም የማይፈታው ቅኔ ነው**

በርግጥም በታሪክ ምዕራፍ ላይ ከዐድዋ የሶሎዳ ተራሮች ተነስተን የጉባንና አካባቢው ተራሮች ግርጌ ስንደርስ በልማት አርበኝነት በዓለም የታሪክ አደባባይ በደማቁ የተፃፈ ድል ያስመዘገብንበት የውሃ ሐውልት አለ፡፡ ይህ ሐውልት የዓለም ጎብኝዎችን ቀልብ የሚስብ መግነጢሳዊ ኃይል አለው፡፡

በዚህ ታሪካዊ ስፍራ ቁጭት የወለደው፣ ፍቅር የገመደው እና ትውልድ የገለጠው ሌላኛው የሀገር ወርቅ አለ፡፡ ይህ የአፍሪካውያን የኩራትና የመቻላቸው አብነት በታላቁ የዐባይ ወንዝ ላይ በህብር ተሸምኖና ከፍ ብሎ ይታያል፤ በመጭው መስከረም ላይ በኢትዮጵያ ሰማይ ከፍ ብሎ ወጥቶ አፍሪካ የአይቻልምን ጨለማ እንድትሰብር ብርታት የሚሆነው ፀሐይ ይወጣል፤ ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ፡፡

እናም እልፍ ትርጓሜ፣ ብዙ ጠቀሜታ ካለው ከዚህ ግድብ በረከቶች መካከል በቱሪዝም ብቻ ስለሚኖረው ፋይዳ ምሁራኑ እንዲህ ይላሉ፤ "ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ የቱሪዝም ፀሐይ አድማሷን አስፍታ በኢትዮጵያ ሰማይ ከፍ ብላ እንድትታይ የሚያደርግ ነው፡፡"

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የቱሪዝም ልማትና አስተዳደር ምሁር ተባባሪ ፕሮፌሰር ሽፈራው ሙለታ (ዶ/ር) የህዳሴው ግድብ ሰፊ ቦታን የሚሸፍን ውሃን ይይዛል፡፡ ይህ ደግሞ ለቱሪዝም ዘርፉ ተጨማሪ ጉልበት ነው፡፡ በአካባቢው ከ70 በላይ ደሴቶችም ይፈጠራሉ፡፡ ይህንን ተከትሎም እንደ ሌሎች የዓለማችን ሀገራት በግድቡ ዙሪያ ትልልቅ ሆቴሎች፣ ልዩ ልዩ ተቋማትና መናፈሻዎች ይገነባሉ፡፡ በተለይም እንደ ሀገር ብዙም ያልሰራንበት ስፖርታዊ የጀልባ ውድድሮች ይደረጋሉ፡፡ ሌሎች የዓለማችን ሀገራት ይህንን መሰል ውድድሮችን በማድረግ ዓለም አቀፍ ቱሪስቶችን በመሳብ ተጠቃሚ ሆነዋል። እኛም የህዳሴው ግድብ የፈጠረልንን ዕድል በመጠቀም ይህንን እና መሰል ሳቢ ነገሮችን ስናደርግ በቱሪዝም ዘርፍ የምናመነጨው ገቢ የበለጠ ከፍ ይላል ብለዋል፡፡

የውሃ አካላትና ቱሪዝም ከፍ ያለ ቁርኝት እንዳላቸው የጠቀሱት ሽፈራው (ዶ/ር)፣ ከዚህ አንፃር የህዳሴው ግድብ የሚፈጥረው የቱሪዝም ዕድል ትልቅ ነው። ግብፅና ሱዳንን የመሳሰሉ የተፋሰሱ ሀገራት የዐባይን ወንዝ በመገደብ አሊያም በተለያየ መልኩ ለቱሪዝም ምቹ በማድረግ ኢኮኖሚያቸውን ስለማሳደጋቸውም ጠቅሰዋል፡፡

በዓለማችን የውሃ ሀብት ያላቸው ሀገራት ደሴቶቻቸውን እና የባህር ዳርቻዎቻቸውን ለቱሪዝም መስህብነት በማዋል ተጠቃሚ ሆነዋል፡፡ ከቅርብ ሀገራትም ዛንዚባር፣ ሲሸልስ እና ኮሞሮስን መጥቀስ እንችላለን፡፡ በመሆኑም የህዳሴው ግድብ ከሐይል ማመንጨቱና መሰል ጥቅሞቹ ባሻገር ለቱሪዝሙ እድገት እንደ ሞተር ነው፤ ብለዋል የቱሪዝም ምሁሩ ሽፈራው (ዶ/ር)፡፡

የቱሪዝም ምሁሩ ደመቀ ክብሩ እንደሚሉት ግድቦች ከቱሪዝም ልማት ጋር በስልት ሲዋሃዱ ለአካባቢው ብልፅግና ምክንያት ይሆናሉ። ለዚህ ደግሞ ጋና፣ ፖርቹጋል እና ህንድን የመሳሰሉ ሀገራት እንዴት ግድቦቻቸውን ለቱሪዝም መስህብነት እንዳዋሉት መመልከት ይቻላል፡፡

የውሃ ሀብት ያላቸው ሀገራት ቱሪዝምን ከውሃ፣ ከኢነርጂ፣ ከመስኖ እና ከሥነ-ምህዳር ጥበቃ ጋር በማዋሃድ ግድቦቻቸውን ወደ ሁለገብ ፕሮጀክት መቀየር ችለዋል፡፡ ግድቦች የኃይል፣ የውሃ አቅርቦት፣ የስራ እድል እና የቱሪዝም ገቢ ያመነጫሉ፡፡ ይህም የሀገር ውስጥ ኢኮኖሚን በዘላቂነት ያሳድጋል። ለአካባቢው ማህበረሰብም ኢኮኖሚያዊ ጥቅሞችን በማምጣት እና ለጎብኚዎች ማራኪ መዳረሻዎችን በመፍጠር ዘላቂ የቱሪዝም በሮችን መክፈት እንደቻሉ የቱሪዝም ምሁሩ ጠቅሰዋል፡፡

እንደ ቱሪዝም ባለሙያው ገለፃ፣ ግድቡ ከሚያመነጨው የኤሌክትሪክ ኃይል፣ የግብርና እና መሰል ምርቶች ባሻገር ለቱሪዝም ዘርፉ መነቃቃት፣ ተጨማሪ የመስህብ ስፍራዎችን በመፍጠር እንደ ሀገር ከቱሪዝም ዘርፉ የምናገኘውን ኢኮኖሚያዊ፣ ዲፕሎማሲያዊና ማህበራዊ ፋይዳዎችን የበለጠ ከፍ ያደርገዋል፡፡

ግድቦች የመዝናኛ የውሃ አካላትን በመፍጠር፣ ውብ መልክዓ ምድሮችን በማጎልበት እና የተለያዩ ውሃን መሰረት ያደረጉ እንቅስቃሴዎችን በማበረታታት ቱሪዝምን በእጅጉ ይደግፋሉ፡፡ የህዳሴው ግድብም ከሀይል ማመንጫነት ባሻገር ለኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን ለአፍሪካ ቱሪዝም ዕድገት አዲስ በርን የሚከፍት ነው ብለዋል፡፡

በመሆኑም የህዳሴው ግድብ ለመዝናኛነት የሚውሉ ተጨማሪ መስህቦችን በመፍጠር፣ ለጀልባ፣ ለዓሳ ማጥመድ፣ ለመዋኛ እና ለሌሎች የውሃ ስፖርቶች የሚያገለግሉ ስፍራዎችን እንደ ሀገር ያጎናፅፈናል፡፡

በሌላ በኩልም ለአካባቢው ውበት ያለውን እሴት በመጨመር በተፈጥሮ እና በውሃ-ነክ መዝናኛዎች ላይ ፍላጎት ያላቸውን ዓለም አቀፍ ቱሪስቶች የበለጠ ለመሳብ ያስችላል፡፡ በሌላ በኩልም ለዱር አራዊት፣ ለአዕዋፍ እና ለልዩ ልዩ ማራኪ ፍጥረታት መኖሪያነትም ስለሚያገለግል የተመልካችን ቀልብ የበለጠ ይስባል። ይህም የቱሪዝም ዘርፉን ከፍታ ይጨምራል፡፡

የህዳሴው ግድብ ከሚፈጥረው የቱሪዝም ውብ ገፅታ እና ዕድል ባሻገርም በትውልድ ቅብብሎሽ እውን የሆነ የሀገር ምልክት ነው፡፡ ይህም ተጨማሪ ባህላዊ እና ታሪካዊ የቱሪዝም መዳረሻ ያደርገዋል። በመሆኑም የህዳሴው ግድብ በቱሪዝም መሠረተ ልማቶች ማለትም በሆቴሎች፣ ሬስቶራንቶችና የትራንስፖርት ተቋማት ላይ ኢንቨስትመንትን በማበረታታት የሀገር ውስጥ ኢኮኖሚን የበለጠ እንደሚያሳድገውም ቱሪዝም ምሁራኑ ጠቁመዋል፡፡

# የወንዞቹ ... ከገጽ 1 የዞረ



ፎቶ- ከገፀ ድር
በወንዝ ዳርቻ ልማት አዲስ ገጽታ የተጎናጸፈው የግንፍሌ ወንዝ በከፊል

"በጋው ሲመጣ ደግሞ በየጥጋጥጉ አሸዋ እያለበሰ ያስቀመጣቸው የእንስሳት በድኖች እና መሰል ቆሻሻዎች ዘግናኝ ጠረን አይጣል ነው፡፡ ቢሆንም በአካባቢው የወንዝ ዳር ልማት እንደሚከናወን ሲነገረኝ ወደ ሌላ አካባቢ ቤት ለመቀየር የወሰንኩባት ያቺ የመጨረሻዋ ምሽት ከወዳጄ ቀበና ጋር በመንፈስ የተጨዋወትንባት ልዩ ዕለት ናትና አትረሳኝም፡፡"

"ቀበና እውነት እንደ ሌሎች የዓለማችን ወንዞች አንተም አምሮብህ አይህ ይሆን? ብዙ የኖርኩብህ፣ ከፉና ደጉን ያሳለፍኩብህ አንተ ቀበና እንደገና ጥርት ብለህ እዝናናብህ ይሆን? እያልኩ አናግሬው ነበርና፡፡"

ይህንን ሀቅ ያጫወቱን በቀበና አካባቢ በተለምዶ '06' ወይም 'ኖራ ሜዳ' ተብሎ በሚጠራው ስፍራ ተከራይተው ይኖሩ የነበሩት አቶ አዳም ባንተይርጋ ናቸው፡፡ በርግጥም የዝግጅት ክፍላችን ለስራ ምክንያት በየጊዜው ተዘዋውሮ ሲመለከታቸው እንደነበረው የመዲናዋ ወንዞች የትላንት መልካቸው አቶ አዳም ባንተይርጋ እንደገለፁት እጅግ አስፈሪ ነበር፡፡ ለአብነትም በክረምት ወቅት በጎርፍ አደጋና ተያያዥ ችግሮች የሚደርሱ አደጋዎች ከመገናኛ ብዙሃን የዜና ዝርዝሮች መካከል እንደማይጠፋ የቅርብ ጊዜ ትዝታችን ነው፡፡

ለአብነትም መጋቢት 12 ቀን 2015 ዓመት ምህረት ለሊት 'በከተማዋ በጣለው ዝናብ እናት እና ልጆችን ጨምሮ አራት ሰዎች በጎርፍ መወሰዳቸው ተሰምቷል' የሚለው ዘገባ የሀገር ውስጥ መገናኛ ብዙሃን ያሰሙት አሳዛኝ ዜና ነበር፡፡ በዕለቱም ከምሽቱ 12:05 ሰዓት በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ወረዳ 11 ማንጎ ሰፈር ወንዝ ዳርቻ ላይ በሚገኙ መኖሪያ ቤቶች ውስጥ ጎርፍ ገብቶ እንደነበር ተገልጿል፡፡ በአደጋውም የ46 ዓመት ወላጅ እናትን ጨምሮ የ3፣ የ13 እና የ15 ዓመት ልጆች ሕይወታቸውን ማጣታቸውን የከተማዋ እሳትና አደጋ ስጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን ማስታወቁ አይዘነጋም፡፡

የሌሎች ሀገራት ወንዞች ታሪክ ግን ከዚህ የተለየ ነው፡፡ በክረምት ወቅት የሚደርሰውን አደጋ በቅርበት የሚያውቁት አቶ አዳም ባንተይርጋም፣ "ቀበና እውነት እንደ ሌሎች የዓለማችን ወንዞች አንተም አምሮብህ አይህ ይሆን?" እንዳሉት በርግጥም በሌሎች ሀገራት ወንዞች ውበት የሚፈልቅባቸው፣ የሚጎርፍባቸው እና እንዳሻው የሚገማሸርባቸው ድንቅ የተፈጥሮ ሀብቶች ናቸው፡፡

"....የሀገር ፀጋ የሀገር ልብስ" እንዳለች ተወዳጇ ድምፃዊ እጅጋየሁ ሽባባው አባይ ወንዝ ትናንት ለካርቱምና ካይሮ ከተሞች የውበታቸው ሰገነት፣ ምግብና መጠጣቸው ነው፡፡ ዛሬ ደግሞ ለኢትዮጵያ ልብሷም ጉርሷም ነው፡፡ ወደ አውሮፓ ከፍ ብንልም የቴምዝ ወንዝ የለንደን ታሪክ እና ባህል ዓርማ ነው። 346 ኪሎ ሜትር የሚሸፍነው ይህ ወንዝ ከተማዋን እያረሰረሰ፣ ፈገግታን በፊቷ ላይ እየነሰነሰ እና የፍቅር አክርማን እየቀነጠሰ መሃል ለመሃል ደስታዋን እየጨመረ አቋርጧት ያልፋል፡፡

በወንዙ ዳር ያሉ ፓርኮች፣ የእግረኛ መንገዶችና መሰል የሰውን ልጅ በሀሴት የሚያረሰርሱ መናፈሻዎች ለለንደን ከተማ ነዋሪዎች ብቻ ሳይሆኑ ለጉብኝት፣ ለስብሰባና ለልዩ ልዩ ጉዳዮች ወደ ከተማዋ ለሚመጡ እንግዶች ተመራጭ መዳረሻዎች፣ ጭንቀትና ናፍቆትን ማስረሻዎች እና ተበልቶ የማያልቅ የልቦና ማዕድ ናቸው፡፡

በአምስተርዳም የአምስቴል ወንዝ ለከተማው የውበት ምንጭ ነው፡፡ በወንዞቹ ዳርና ዳር ያሉ ታሪካዊ ሕንፃዎች እና ድንቅ ስፍራዎች በየዓመቱ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ጎብኚዎችን የሚስብ ልዩ ውበትን ፈጥረዋል። የአምስቴል ወንዝ ለከተማዋ የውበት ምንጭ ብቻ አይደለም፤ ከጫፍ እስከ ጫፍ መመላለሻና ካሰቡት መድረሻ መንገድም ነው፡፡

የሞስኮቫ ወንዝ በሞስኮ እምብርት ውስጥ የተንሰራፋ እና የከተማዋን የህንፃ ጥበብ በውሃ መስታወትነት የሚያሳይ ድንቅ ፀጋዋ ነው፡፡ የወንዙ ዳርቻዎች በመናፈሻ ቦታዎች፣ በእግረኛ መንገዶች እና በባህላዊ ተቋማት የተሞሉ በመሆናቸው ከተማዋን የእንቅስቃሴ ማዕከል አድርጓታል፡፡ ይህ ወንዝ በደማቋ ከተማ ውስጥ በተፈጥሮ እና በከተማ ህይወት መካከል ያለውን ጣፋጭ መስተጋብር የሚያሳይ ዋቢ ምስክርም ሆኖ ያገለግላል፡፡

የአዲስ አበባ ወንዞች ግን ለዚህ ክብር አልታደሉም ነበር፡፡ ሁሉም ጀርባውን ሰጥቶ ቆሻሻ የሚጥልባቸው፣ አፍንጫውን ይዞ እየሮጠ የሚያልፍባቸው፣ የአካባቢው ነዋሪም ቢሆን በዘፈን እና በአባባል ከማወደስ ባለፈ የመፀዳጃ ቤት ቆሻሻውን የሚያራግፍባቸው አመድ አፋሾች ነበሩ፡፡

እውቋ ብራዚላዊት የስነ ሕንፃ እና ከተማ ፕላን ተመራማሪ ቲፋኒ ኒኮሊ ዋና መቀመጫውን በአሜሪካን ሀገር ቺካጎ ባደረገው እና በርካቶች የምርምር ስራዎቻቸውን በሚያሳትሙበት 'Urban Design Lab's' (የከተማ ዲዛይን ቤተ ሙከራ) ላይ የከተማ ወንዞች ፋይዳ ወይም 'The value of urban rivers: European experiences and a South American perspective' በሚል

> **በመዲናዋ የተጀመረው የወንዝ ዳር ልማት የአዲስ አበባ ወንዞችን ወደ ሞት ሳይሆን ወደ ውበት፣ ወደ ብክለት ሳይሆን ወደ ሀብት እንዲፈስሱ የሚያደርግ ነው**

ርዕስ ባሳተሙት ጥናታዊ ፅሑፋቸው እንደገለፁት በብዙ የአውሮፓ ዋና ከተሞች ያሉ ወንዞች የውበት፣ የሀብት፣ የሰው ልጆች ብቻ ሳይሆን የዓሳም፤ የሀሳብም መመላለሻ ናቸው፡፡ ለዚህ ደግሞ በፓሪስ፣ በለንደን፣ በስቶክሆልም፣ በኦስሎ እና መሰል ከተሞች ያሉ ወንዞችን መጥቀስ ይቻላል፡፡

የወንዝ ሀብታም የሆነችው አዲስ አበባ ግን ይህንን ውበትና ጥቅም ለማጣጣም አልታደለችም ነበር፡፡ በመጋቢት ወር 2017 ዓ.ም በከተማዋ ያሉ 76 ወንዞችና ገባሮች የተበከሉ መሆናቸው የአዲስ አበባ የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ይፋ ያደረገው መረጃ ያመለክታል፡፡

መረጃዎች እንደሚያሳዩት በአዲስ አበባ 7 ትልልቅና ከ75 በላይ ትንንሽ ወንዞች ቢኖሩም ለከተማዋ ውበትና ሀብት መሆን ግን አልቻሉም ነበር፡፡ ከታላላቅ ወንዞቿ መካከልም ቀበና፣ ባንተይቀጡ፣ ቀጨኔ፣ ቁርጡሚ፣ ቡልቡላ፣ አቃቂ እና የቄራ ወንዞችን መጥቀስ በቂ ነው፡፡ የአዲስ አበባ ወንዞች የማይነኩት ወረዳና ክፍለ ከተማ የለም፤ በዚያው ልክ ችግሩም የማይነካው የለም።

የአካባቢ ሳይንስ ባለሙያው አቶ ገነነ ካሳሁን እንደሚሉት የከተማዋ ወንዞች የቀደመ ታሪካቸውም ሆነ አሁንም አልፎ አልፎ በአንዳንዶቹ ላይ እንደሚታየው በጣም አካባቢን የሚበክሉና ለሰው ልጆች የጤና ጠንቅ የሆኑ ናቸው፡፡ ይሁን እንጂ እንደ ከተማ በተጀመረው የአረንጓዴ ልማት ስራ በወንዞቹና በዙሪያቸው አስደማሚ ለውጦች እየተመዘገቡ ነው። ለዚህ ደግሞ የቀበና ወንዝ ልማትን ለአብነት ጠቅሰዋል፡፡

የአረንጓዴ ዐሻራውን ተከትሎም በወንዞቹ አካባቢ በርካታ ችግኞች በስፋት እየተተከሉ በመሆናቸው በሌሎች የዓለማችን ከተሞች የምናየውን ወንዞች ውበትና ጥቅም በአዲስ አበባ ከተማም እውን የሚሆንበት ጊዜ ቅርብ መሆኑን ከእንጦጦ ጀምሮ በመዲናዋ ወንዞች ላይ እየተሰሩ ያሉ ልማቶች ማሳያ ስለመሆናቸውም ጠቅሰዋል፡፡

በመዲናዋ የተጀመረው የወንዝ ዳር ልማት የአዲስ አበባ ወንዞችን ወደ ሞት ሳይሆን ወደ ውበት ወደ ብክለት ሳይሆን ወደ ሀብት እንዲፈስሱ የሚያደርግ ዕድል እንደሆነም የአካባቢ ሳይንስ ባለሙያው አቶ ገነነ ካሳሁን ይናገራሉ፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ምክትል ስራ አስኪያጅ አቶ አሰግደው ወልደጊዮርጊስ እንደሚሉት ሀገራዊ ለውጡን ተከትሎም ለዘመናት ተረስተው የቆዩት ወንዞችን ለማልማት፣ የተጎሳቆለውን ገፅታቸውን ለመቀየር፣ ከብክለት ለመታደግ የከተማ አስተዳደሩ በቁርጠኝነት እየሰራ ይገኛል። በሁለተኛው ምዕራፍ የኮሪደር ልማት ከተያዙና ግንባታቸው በፍጥነት እየተከናወኑ ከሚገኙ የወንዝ ዳርቻ ልማቶች መካከል 20 ኪሎ ሜትር ርዝመት የሚሸፍነው የቀበና ወንዝ ዳርቻ ይጠቀሳል፡፡

አቶ አሰግደው እንደሚገልፁት፤ በቀበና ወንዝም ሆነ በሌሎች አካባቢዎች እየተከናወኑ የሚገኙ የወንዝ ዳርቻ ልማቶች የከተማዋን ገፅታ በመቀየርና የአካባቢ ጥበቃን በመጠበቅ በኩል ትልቅ ትርጉም ያላቸው ናቸው፡፡

በርካታ ዜጎችም በወንዝ ዳርቻ፣ የቤታቸውን ግድግዳ ወንዙ ስር በማድረግ ራሳቸውን ለአደጋ አጋልጠው ይኖሩ ነበር፡፡ በዚህም በተለያዩ ጊዜያት በሰው ህይወትና ንብረት ላይ አደጋዎች ሲያጋጥም ቆይቷል፡፡ በወንዝ ዳርቻ ልማት ለጎርፍ ተጋላጭ የሆኑ ነዋሪዎችን በማንሳትና ንፁህና ደህንነቱ በተጠበቀ አካባቢ እንዲኖሩ በማድረግ፣ የጎርፍ መከላከያ የድጋፍ ግንቦችን በመገንባት፣ የአፈርና ውሃ ጥበቃ ስራዎችን በመስራት የጎርፍ አደጋ ስጋትን መከላከል የሚያስችል አቅም መፍጠር እንደተቻለም ተናግረዋል፡፡

ትናንት የቀበናን ጎስቋላ መልኩን፣ በክረምት ሙላቱን፣ በበጋ ደግሞ መጥፎ ጠረኑን እያዩ ለአስር ዓመታት በአካባቢው የኖሩት አቶ አዳም ባንተይርጋ፣ "ቀበና እውነት እንደ ሌሎች የዓለማችን ወንዞች አንተም አምሮብህ አይህ ይሆን?" በማለት በመጨረሻዋ ምሽታቸው ከቀበና ጋር መጨዋወታቸውን ነግረውናል፡፡ ዛሬ ደግሞ የቀበና ወንዝ ልክ ፀጉሯን በመልኩ፤ በረድፉ፤ እንደተጎነጎነች ሐር የመሰለው የፀጉሯ ውበትም ከአጠላለፉ ጋር እንደሚታይላት ሙሽራ አሊያም እንደ ሐምሌ ፀሐይ ጉምና ጭጋጉን እየገላለጠ በመውጣት ለመዲናዋ የውበት ብርሃኑን መፈንጠቅ በመጀመሩ መደሰታቸውን ካጫወቱን በላይ የፊታቸው ገፅታ ብዙ ይናገራል፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ አስተዳደር በወረዳ 01 ክልል ውስጥ በአቶ ይስሐቅ ወ/ገብርኤል ስም በካርታ ቁጥር 030306 ሴሪ ቁጥር 030211 በሆነ የተመዘገበው ይዞታ፣ የቤት ባለቤትነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት /ካርታ ስለጠፋባቸው በማንኛውም መልኩ በእጁ ይገኛል የሚል አካል ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ30 ቀን ጊዜ ውስጥ በጽ/ቤታችን ይዘው መቅረብ የሚችሉ መሆኑን እያሳወቅን ይህ ካልሆነ በምትኩ ሌላ የመሬት ይዞታ መብት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እንደሚሰጣቸው እናሳውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ አቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ ቅ/ጽ/ቤት**

---

ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው በለሚ ኩራ ክ/ከተማ ክልል ውስጥ የሚገኝ በካርታ ቁጥር የካ13/12633/01 ሴሪ ቁጥር 102358 መስከረም ሽፈራው ከበደ ስም ተመዝግቦ የሚገኝ የኮንዶሚንየም ቤት እናት ማህደር ከለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት በማህደር ክፍላችን ተፈልጎ ባለመገኘቱ ማህደራቸውን ልናደራጅላቸው ስለሆነ ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት ቀን አንስቶ በ30 ቀናት ውስጥ በለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት ተቃውሞውን እንዲያቀርቡ እያሳሰብን፣ በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ተቃውሞ የማያቀርቡ ከሆነ በምትኩ መመሪያው በሚፈቅደው መሰረት ሌላ ካርታ የሚሰጣቸው መሆኑን እንገልጻለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

እነ በእነ ጌጤነሽ ገብርዬ ስም በልደታ ክ/ከተማ አዲሱ ወረዳ 03 ቀበሌ 04/06 የቤት ቁጥር 1096/1095 በቀን 04/08/2003 ዓ.ም፣ በካርታ ቁጥር ል.04/28/591/00 የጠፋባቸው በመሆኑ በጋዜጣ ታውጆ አገልግሎት እንዲሰጣቸው አመልክተዋል፡፡ በመሆኑም በጠየቁት መሰረት የምትክ ካርታ አገልግሎት ለመስጠት ያመች ዘንድ ከላይ በተጠቀሱት ካርታ ቁጥር እና በባለጉዳዮቹ ስም የተመዘገበውን የይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት /ኦርጅናል ካርታም ሆነ ኮፒውን/ ይዤዋለሁ የሚል ማንኛውም አካል ካለ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ 30 ቀን ድረስ ልደታ ክ/ከተማ የመሬት ይዞታ መብት ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ካልቀረበ በመመሪያ ቁጥር 61/2010 አንቀጽ 72 ንኡስ አንቀጽ 3 መሰረት በምትኩ ሌላ የመሬት ይዞታ መብት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የሚሰጣቸው መሆኑን እንገልጻለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ልደታ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

አቶ ዮናታን ጎኦሽ መለስ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በቦሌ ክ/ከተማ ወረዳ 12 ካርታ ቁጥር ቦሌ12/57/5/6/10753/226228/01 ሴሪ ቁጥር 0157425 ተመዝግቦ የነበረው ኦርጅናል /ዋናው የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ስለጠፋባቸው በተለያየ ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ በአዲስ ልሳን ጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባለው 20 ቀናት ውስጥ በቦሌ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ጽ/ቤት ለይዞታ አገልግሎትና ማስተካከል ዳይሬክቶሬት ካልቀረበ በምትኩ ሌላ አዲስ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ የሚሰጣቸው መሆኑን እንገልጻለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የቦሌ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው በለሚ ኩራ ክ/ከተማ ክልል ውስጥ የሚገኝ በካርታ ቁጥር ቦሌ9/98/7/6/44653/00 በሴሪ ቁጥር 0667910 በአቶ/በወ/ሮ/በወ/ሪት በመሠረት ጌታቸው ባልቻ ስም ተመዝግቦ የሚገኝ ቤት እናት ማህደር ከለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት በማህደር ክፍላችን ተፈልጎ ባለመገኘቱ ማህደራቸውን ልናደራጅላቸው ስለሆነ ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት ቀን አንስቶ በ30 ቀናት ውስጥ በለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት ተቃውሞውን እንዲያቀርቡ እያሳሰብን፣ በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ተቃውሞ የማያቀርቡ ከሆነ በምትኩ መመሪያው በሚፈቅደው መሰረት ሌላ ካርታ የሚሰጣቸው መሆኑን እንገልጻለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በአራዳ ክ/ከተማ በአዲሱ ወረዳ 06 በቤት ቁጥር 116 በፋሚሊ ሞደርን ትሬዲንግ ኃ/የተ/የግ/ማህበር ስም የወጣው ቁጥሩ የካ/210781/10 ሴሪ ቁጥር 0122286 በቀን 17/11/2010 ዓ.ም ወጪ የሆነ ኦርጂናል ካርታ ስለጠፋባቸው በምትኩ ካርታ ተዘጋጅቶ እንዲሰጣቸው 28/11/2017 በተፃፈ ማመልከቻ ጠይቋል፡፡

በመሆኑም የጠየቁትን አገልግሎት ለመስጠት ያመች ዘንድ ከላይ በተጠቀሰው የተመዘገበውን የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ይዤዋለሁ የሚል ማንኛውም አካል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ አስከ 30 ቀን ድረስ ለአራዳ ክፍለ ከተማ የመሬት ይዞታ አስተዳደር ጽ/ቤት ድረስ እንዲያቀርቡ እያሳወቅን ካልቀረቡ ግን የጠየቁትን አገልግሎት የምንሰጣቸው መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አሰተዳደር ቢሮ የአራዳ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

ተስፋልደት አዘናው ስም የተመዘገበ በካርታ ቁጥር ቦሌ10/136/8/13/250011/00 የሴሪ ቁጥር 1556016 የተሰጠበት ቀን 11/06/2013 ዓ.ም የቦታው ስፋት በሰነድ 34.36 ሜ.ካ የሆነው ካርታ መጥፋቱ ተገልጾ ለፖሊስ እንዲጻፍልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡

በመሆኑም በለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ጽ/ቤት ወረዳ 03 የሆነው መኖሪያ ቤት ተስፋልደት አዘናው ስም የተመዘገበ ቦሌ10/136/8/13/250011/00 የሴሪ ቁጥር 1556016 የተሰጠበት ቀን 11/06/2013 ዓ.ም የቦታው ስፋት በሰነድ 34.36 ሜ.ካ የሆነው የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ኦርጅናል የጠፋ ስለሆነ ይዞታ ቤቱን በዕዳ ይዤዋለሁ፤ አስይዤዋለሁ የሚል አካል በ30 ቀናት በጋዜጣ ጥሪ ስለሚደረግ በተጠቀሰው ቀናት ውስጥ ለተቋሙ እንዲያሳውቁን እያልን በዚህ ምክንያት ለ30 ቀናት የሚቆይ በጋዜጣ ጥሪ እንዲደረግ እየጠየቅን ይህ ጋዜጣ ጥሪ ከተደረገበት በኋላ ካርታውን የምናዘጋጅ ይሆናል፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በአቶ በቀለ ነጋሽ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ አስተዳደር ወረዳ 01 ክልል ውስጥ የሚገኝ ይዞታ ተመዝግቦ የተሰጣቸው ካርታ ቁጥር 018366 ሴሪ ቁጥር 000250 የቦታው ስፋት 94.64 ካሬ ሜትር የሆነ ካርታ የጠፋባቸው በመሆኑ በጋዜጣ እንዲታወጅ እየገለጽን በማንኛውም ምክንያት የጠፋውን ካርታ ይዤዋለሁ የሚል አካል ካለ ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከታወጀበት ዕለት ጀምሮ እስከ 20 ተከታታይ የሥራ ቀናት ባለው ጊዜ ውስጥ በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ የመሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት ካላቀረቡ በምትክ ሌላ ካርታ የምንሰጣቸው መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

ወ/ሪት የትናየት በጋሻው አልዳዳ በጉለሌ ክ/ከተማ ወረዳ 3 የቤት ቁጥር 89 ካርታ ቁጥር 5/56/3344/01 ተመዝግቦ በእጃቸው መገኘት የነበረበት ካርታ የጠፋ በመሆኑ ይህንኑ አስመልክቶ የሚቀርብ ማንኛውም መቃወሚያ ካለ ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ታትሞ ከወጣ በ20 ቀን ውስጥ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ ጉለሌ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ማስረጃውን ይዞ ካልቀረበ ካርታው እንደጠፋ ተቆጥሮ በምትኩ አዲስ ካርታ በማዘጋጀት አገልግሎት የምንሰጥ መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የጉለሌ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

**የጠፋ ካርታ በጋዜጣ እንዲወጣ ስለማሳወቅ**

ከላይ በርዕሱ ለመጥቀስ እንደተሞከረው የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የካ ክፍለ ከተማ ቅርንጫፍ ፅ/ቤት በወረዳ 07 በ የውብዳር ገብረማርያም ሙሜቻ ስም የተመዘገበ የይዞታ ልዩ መለያ ቁጥር AA000050700862 የተሰጠበት ቀን 28/01/2017 ዓ.ም እና ሴሪ ቁጥር R 0116623 የሆነ የመብት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት እንደጠፋባቸው በቁጥር የካ/ፖ/ለ/ቁ/5/1030 በቀን 05/12/2017 ዓ.ም የሚገልፅ መረጃ በማቅረብ አመልክተዋል፡፡ ይህም በጋዜጣ ታትሞ እንዲወጣልኝ ሲሉ ያመለከቱ ስለሆነ ካርታውን አይቻለው ወይም መብት አለኝ ባይ በ90 ቀን ውስጥ በአዲስ አበባ ከተማ የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የካ ቅርንጫፍ ቀርቦ እንዲያሳውቅ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች በምትክ ሰርተፍኬት የሚሰጥ መሆኑን በአክብሮት እንገልፃለን።

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የካ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

ከላይ በርዕሱ ለመጥቀስ እንደተሞከረው በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ አዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ቅርንጫፍ ከአዲስ ከተማ ክ/ከተማ ወረዳ 06 የቤት ቁጥር 534 በእነ ፈለቀች ካሳ ያደቴ ስም የተመዘገበው የይዞታ ልዩ መለያ ቁጥር (ካርታ ቁጥር) 006/45/1/12418 በቀን 22/02/2010 ሴሪ ቁጥር 042264 የሆነው የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፍኬት (ካርታ) እንደጠፋባቸው በቀን 02/12/2017 ዓ.ም ያመለከቱ ሲሆን ይህንኑን የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ይዤዋለሁ (አግኝቼዋለሁ) የሚል አካል ካለ ይህ ማስታወቂያ በአዲስ ልሳን ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት ተከታታይ በ 30 ቀናት ውስጥ በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ የመሬት ይዞታ ምዝገባ እና መረጃ ኤጀንሲ ቅ/ጽ/ቤት ማቅረብ የሚችል ሲሆን ይህ የማይሆን ከሆነ ግን ምትክ የይዞታ የማረጋገጫ ሰርተፍኬት (ካርታ) የሚሰጣቸው መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ አዲስ ከተማ ክ/ከተማ ቅ/ጽ/ቤት**

---

ከላይ በርዕሱ ለመጥቀስ እንደተሞከረው በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ አዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት ይዞታው በአዲስ ከተማ ክ/ከተማ ወረዳ 10 የቤት ቁጥር አዲስ በሽብሬ ታደለ ደስታ ስም የተመዘገበው የይዞታ ልዩ መለያ ቁጥር (ካርታ ቁጥር) AA000021001246 የሆነ ሴሪ ቁጥሩ 0258338 የሆነ የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፍኬት (ካርታ) እንደጠፋባቸው በቀን 30/11/2017 ዓ.ም ያመለከቱ ሲሆን ይህንኑን የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ይዤዋለሁ (አግኝቼዋለሁ) የሚል አካል ካለ ይህ ማስታወቂያ በአዲስ ልሳን ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት ተከታታይ በሆኑ 90 ቀናት ውስጥ በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ የመሬት ይዞታ ምዝገባ እና መረጃ ኤጀንሲ ቅ/ጽ/ቤት ማቅረብ የሚችል ሲሆን ይህ የማይሆን ከሆነ ግን ምትክ የይዞታ የማረጋገጫ ሰርተፍኬት (ካርታ) የሚሰጣቸው መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ አዲስ ከተማ ክ/ከተማ ቅ/ጽ/ቤት**

---

ገብረመስቀል በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ ወረዳ 01 ክልል ውስጥ የሚገኝ ይዞታ ካርታ ተመዝግቦ የተሰጣቸው ካርታ ቁጥር 033439 የሴሪ ቁጥር 034177 የይዞታ ስፋት 94.64 ካ.ሜትር የሆነ ካርታ የጠፋባቸው መሆኑን ከፖሊስ ማስመዝገባቸው በቁጥር መመ15/15105157 በቀን 09/05/17 በተገለፀልን መሰረት ወጪውን ግለሰቡ በመቻል በጋዜጣ እንዲታወጅላቸው እየገለጽን በማንኛውም ምክንያት የጠፋውን ካርታ ይዤዋለሁ የሚል አካል ካለ እስከ 20 ተከታታይ የስራ ቀን ባለው ግዜ ውስጥ በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ካርታ የምንሰጣቸው መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ በአዲሱ አደረጃጀት ወረዳ 13 በቀድሞ ወረዳ 25 ቀበሌ 03 የቤት ቁጥር 489 ለሆነው ቤት የካርታ ቁጥር ኮ/ቀ/የማ/ን/መ/11/19878/01 በሴሪ ቁጥር 069666 በወ/ሮ አየለች መንጂ አሰና ስም የይዞታ/የቤት ባለቤትነት ማረጋገጫ ካርታ ተሰጥቶ የነበረ ቢሆንም ካርታው በመጥፋቱ ምክንያት የካርታ ኮፒ አገልግሎት የተጠየቀ ሲሆን አገልግሎቱን ለመስጠት የመብት ፈጠራና የይዞታ አገልግሎት አሰጣጥ ደንብ ቁጥር 163/2016 አንቀጽ 23 መሰረት የባለይዞታው የይዞታ ማረጋገጫ ሰነድ መጥፋቱ በአዲስ ልሳን ጋዜጣ ማስታወቂያ ወጥቶ በ30 (ሰላሳ ቀን) ቀን ውስጥ ተቃዋሚ ካልቀረበ አገልግሎቱን መስጠት እንደሚቻል ተደንግጎ ይገኛል፡፡ ስለሆነም ካርታውን ይዤዋለሁ የሚል አካል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ30 (ሰላሳ ቀን) ቀን ውስጥ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ አዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ይዞ እንዲቀርብ እያሳሰብን ይህ ካልሆነ ግን በመመሪያው መሰረት የጠፋውን ካርታ አምክነን በምትክ ሌላ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ የምንሰጥ መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የአዲስ ከተማ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

# የግልፅ ጨረታ ማስታወቂያ

## መለያ ቁጥር 01 /2018

በልደታ ክፍለ ከተማ ትምህርት ጽ/ቤት የህዳሴ ልደታ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት ለ2018 በጀት ዓመት አገልግሎት የሚውሉ የደንብ ልብስ፣ የደንብ ልብስ ስፌት፣ ኤሌክትሮኒክስ፣ ፈርኒቸር እቃዎች፣ ስቴሽነሪ/የፅህፈት መሳሪያ፣ አላቂ የትምህርት እቃዎች፣ አላቂ የብሮ እቃዎች፣ ሌሎች አላቂ እቃዎችና አቅርቦቶች፣ ልዩልዩ መሳሪያዎች፣ በግልጽ ጨረታ አወዳድሮ ግዥ መፈፀም ይፈልጋል፡፡

ስለሆነም በጨረታዉ ለመሳተፍ የምትፈልጉ ከዚህ በታች በዝርዝር የቀረቡትን መስፈርት የምታሟሉ ተጫራቾች በሙሉ በጨረታዉ እንድትሳተፉ እንጋብዛለን፡፡

1. አገልግሎቱን እና እቃዉን በጥራት ለማቅረብ የሚያስችል ብቃት ሕጋዊ የንግድ ፍቃድ ያላቸዉ እና የ2018 ዓ.ም የታደሰ ንግድ ፍቃድ ያላቸዉ፡፡
2. ተጫራቾች በአቅራቢዎች ዝርዝር ውስጥ የተመዘገቡና የምስክር ወረቀት ኮፒ ከጨረታ ሰነዱ ጋር አያይዘዉ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡
3. ተጫራቾች በተጨማሪ እሴት ታስክ (VAT) ተመዝጋቢ የሆኑና ለዚህም የተመዘገቡበትን ኮፒ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡
4. ተጫራቾች ለጨረታ ማስከበሪያ
   - ሎት01. የደንብ ልብስ፣ የደንብ ልብስ ስፌት 19,400.00 ብር (አስራ ዘጠኝ ሺ አራት መቶ)፣
   - ሎት02. ኤሌክትሮኒክስ 110,166.00 ብር (አንድ መቶ አስር ሺ አንድ መቶ ስልሳ ስድስት ብር)፣
   - ሎት03. ልዩ ልዩ መሳሪያዎች 6800.00 ብር (ስድስት ሺ ስምንት መቶ ብር)
   - ሎት04. ስቴሽነሪ/የፅህፈት መሳሪያ 18,000.00 ብር (አስራ ስምንት ሺ ብር)
   - ሎት 5. ሌሎች አላቂ እቃዎችና አቅርቦቶች 15,000.00 ብር (አስራ አምስት ሺ ብር)
   - ሎት 6. ለፈርኒቸር እቃዎች 58,000.00 ብር (አምሳ ስምንት ሺ ብር)፣
   - ሎት 7. አላቂ የህክምና እቃዎች 1000.00 (አንድ ሺ ብር)

   በባንክ በተረጋገጠ CPO ከጨረታዉ ከሰነድ ጋር በፖስታ በማሸግ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡
5. ተጫራቾች የጨረታውን ዝርዝር ሰነድ የማይመለስ ብር 200.00/ሁለት መቶ ብር ብቻ/ ብቻ በመክፈል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት 10(አስር) ተከታታይ የስራ ቀናት ውስጥ ጎማ ቁጠባ ፊት ለፊት ከሚገኘው ህዳሴ ልደታ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት ፋይናንስ ክፍል መውሰድ ይችላሉ፡፡
6. በአነስተኛ እና ጥቃቅን የተደራጁ ህጋዊ ማረጋገጫ የዋስትና ደብዳቤ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡
7. ጨረታዉ ከመከፈቱ በፊት ናሙና ለሚቀርብላቸዉ እቃዎች ናሙና ያቀረቡ ተወዳዳሪዎች ብቻ የሚወዳደሩ ሲሆን ቋሚ እቃዎችን በስፔስፊኬሽን መሰረት የምናወዳድር ይሆናል፡፡
8. ተጫራቾች በገዙት የጨረታ ሰነድ ላይ በተዘጋጀዉ የዋጋ ዝርዝር መሙያ ላይ ሞልተዉ ማቅረብ አለባቸው፡፡ በሌላ ሰነድ የተሞላ ተቀባይነት የለዉም፡፡
9. ተጫራቾች በሚያቀርቡት የዋጋ ዝርዝር ላይ ቫትን ማካተት አለባቸዉ፡፡
10. ት/ቤቱ በሚገዛዉ እቃ ላይ 20% መጨመርና መቀነስ መብቱ የተጠበቀ ነዉ፡፡
11. ጨረታዉ በአዲስ ልሳን ጋዘጣ ታትሞ ከወጣበት ዕለት ጀምሮ ለአስር(10) ተከታታይ የስራ ቀናት ወስጥ ተጫራቾች የጨረታ ሰነዱን የሚጫረቱበትን የመወዳደሪያ ዋጋ ሞልተዉ በታሸገ ፖስታ ት/ቤቱ ባዘጋጀዉ ሳጥን ማስገባት አለባቸዉ፡፡
12. ጨረታዉ በአሰራ አንደኛዉ ቀን በ8፡00 ሰዓት ታሽጎ በ8፡30 ሰዓት ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸዉ በተገኙበት ሳጥኑ ይከፈታል፡፡ ጨረታዉ የሚከፈቱበት 11ኛዉ ቀን በዓል ወይም ቅዳሜና እሁድ ከዋለ በቀጣይ ባለዉ የስራ ቀን ይከፈታል፡፡
13. የጨረታ አሸናፊ የሚለየዉ በሞላዉ ነጠላ ዋጋ ነዉ፡፡
14. አሸናፊዎች ያሸነፉትን እቃ በራሳቸዉ ትራንስፖርት እስከ ት/ቤቱ ማቅረብ አለባቸዉ፡፡
15. የጨረታ አሸናፊ ከተረጋገጠበት ቀን ጀምሮ ባሉት አምስት /5/ የስራ ቀናት ዉስጥ የዉል ማስከበሪያ ባሸነፈበት እቃ ላይ 10% CPO ማስያዝ የአለበት፡፡

### ማሳሰቢያ

- ት/ቤቱ የተሻለ ዘዴ ካገኘ ጨረታዉን በከፊልም ሆነ ሙሉ በሙሉ የመሰረዝ መብቱ የጠበቀ ነዉ፡፡
- ሁሉም እቃ አዲስ መሆን አለበት፡፡
- ናሙና ጨረታ ከወጣበት ቀን አንስቶ 10 የስራ ቀናት ብቻ የምንቀበል ይሆናል፡፡
- ተጨራቾች ዝርዝር መረጃ ካስፈለገዎት በስልክ ቁጥር 0118698784 ደውለው ማግኘት ይችላሉ፡፡

**አድራሻ፡-** በልደታ ክ/ከ/ወረዳ 05 ጎማ ቁጠባ ፊት ለፊት ወይም ጤና ጥበቃ ሚኒስርቴር ፊት ለፊት

**አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ት/ቢሮ ልደታ ክ/ከተማ ትምህርት ጽ/ቤት ህዳሴ ልደታ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት**

---

ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው በለሚ ኩራ ክ/ከተማ ክልል ውስጥ የሚገኝ የካ/15058/13 በሴሪ ቁጥር 0700469 ቦጃ ቀጀላ ጎጂ ስም ተመዝግቦ የሚገኘው ቤት እናት ማህደር ከለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት በማህደር ክፍላችን ተፈልጎ ባለመገኘቱ ማህደራቸውን ልናደራጅላቸው ስለሆነ ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት ቀን አንስቶ በ30 ቀናት ውስጥ በለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት ተቃውሞውን እንዲያቀርቡ እያሳሰብን፣ በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ተቃውሞ የማያቀርቡ ከሆነ በምትኩ በመመሪያው በሚፈቅደው መሰረት ሌላ ካርታ የሚሰጣቸው መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ወረዳ 3 ውስጥ በካርታ ቁጥር 1728/ኤ በሴሪ ቁጥር 57650 በሻለቃ ግርማ ሰጠኝ አላምረው ስም የተመዘገበ ማህደር ከማህደር ክፍላችን የጠፋ ስለሆነ ማህደሩን የያዘ ካለ ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት በ30 ቀን ጊዜ ውስጥ በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት ድረስ መጥተው ካላሳወቁ ካርታ በማዘጋጀት አገልግሎት የምንሰጣቸው መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

ወ/ሮ ሙሉ ሲሳይ ፍልቀቱ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ለሚ ኩራ ክ/ከተማ ወረዳ 03 የካርታ ቁጥር AA00006100751021O305 የሆነው ሰርተፍኬት በጽህፈት ቤታችን ተመዝግቦ የሚገኝ ሲሆን የቤት ባለቤትነት ካርታ ስለጠፋባቸው በማንኛውም ምክንያት አግኝቸዋለሁ የሚል ግለሰብም ይሁን ሌላ አካል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እስከ 30 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረበ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት /ካርታ/ ተዘጋጅቶ እንደሚሰጣቸው እናሳውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የለሚ ኩራ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

ህሩት ገ/መድህን ወ/ስላሴ ስም የተመዘገበ በካርታ ቁጥር ለ/ኩ/8/4/3/8/154209/00 የሴሪ ቁጥር 1670415 የተሰጠበት ቀን 09/09/2015 ዓ.ም የቦታው ስፋት በሰነድ 55.11 ሜ.ካ የሆነው ካርታ መጥፋቱ ተገልጾ ለፖሊስ እንዲጻፍልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡

በመሆኑም በለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ጽ/ቤት ወረዳ 03 የሆነው መኖሪያ ቤት በህሩት ገ/መድህን ወ/ስላሴ ስም የተመዘገበ ለ/ኩ/8/4/3/8/154209/00 የሴሪ ቁጥር 1670415 የተሰጠበት ቀን 09/09/2015 ዓ.ም የቦታው ስፋት በሰነድ 55.11 ሜ.ካ የሆነው የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ኦርጅናል የጠፋ ስለሆነ ይዞታ ቤቱን በዕዳ ይዤዋለሁ፤ አስይዤዋለሁ የሚል አካል በ30 ቀናት በጋዜጣ ጥሪ ስለሚደረግ በተጠቀሰው ቀናት ውስጥ ለተቋሙ እንዲያሳውቁን እያለን በዚህ ምክንያት ለ30 ቀናት የሚቆይ በጋዜጣ ጥሪ እንዲደረግ እየጠየቅን ይህ ጋዜጣ ጥሪ ከተደረገበት በኋላ ካርታውን የምናደራጅ ይሆናል፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ወረዳ 1 አስተዳደር ውስጥ በካርታ ቁጥር 044378 በሴሪ ቁጥር 038779 በአቶ ሀ/ማርያም ወ/ሚካኤል የተመዘገበ ይዞታ ማህደራቸው ከማህደር ክፍላችን መገኘት የነበረበት የጠፋባቸው ስለሆነ ማህደሩን የያዘ ግለሰብ ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት በ30 ቀን ጊዜ ውስጥ በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት ድረስ መጥተው ካላሳወቁ ማህደር በማዘጋጀት አገልግሎት የምንሰጣቸው መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በቤተሰብ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በን/ስ/ላ/ክ/ከተማ ወረዳ 01 የሚገኘው በይዞታ ካርታ ቁጥር ዴ1/ን/ስ/ላ/ክ/ከ/ሊዝ/ስ/392/98/63491/71022/02 በሴሪ ቁጥሩ 032450 በስማቸው በጽ/ቤታችን ተመዝግቦ የሚገኘው ይዞታ የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ስለጠፋባቸው በማናቸውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ/ ይዤዋለሁ/ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ 90 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የንፋስ ስልክ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በቀድሞ ወረዳ 23 ቀበሌ 15 በአዲሱ ወረዳ 8 በቤት ቁጥር ........ በካርታ ቁጥር 21501/20208/20570/02 እና በ ውልታ አሰፋ ይፍሩ ስም የተመዘገበ ማህደር የጠፋባቸው መሆኑን በመግለጽ በምትኩ ማህደር እንዲደራጅላቸው በቀን ሀምሌ 8/2017 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ አገልግሎት እንድንሰጣቸው ጠይቀውናል፡፡

ስለሆነም ባመለከቱት መሰረት አገልግሎት ሊሰጣቸው መሆኑን እያሳወቅን አገልግሎት ከመሰጠቱ በፊት ተቃዋሚ ካለ በፍ/ቤት በማሳገድ ወይም የመንግስትና የህዝብ ንብረት መሆኑን የሚገልፁ ማስረጃዎችን በመያዝ በ30 ቀን ጊዜ ውስጥ እንዲያቀርብ እያሳሰብን በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ተቃውሞ የማይቀርብ ከሆነ በምትኩ ሌላ ማህደር የሚዘጋጅላቸው መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የልደታ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ወረዳ 8 አስተዳደር ውስጥ በካርታ ቁጥር 010381 በሴሪ ቁጥር 025779 በ ወ/ሮ ሙሉ አረጋይ የተመዘገበ ይዞታ ማህደራቸው ከማህደር ክፍላችን መገኘት የነበረበት የጠፋባቸው ስለሆነ ማህደሩን የያዘ ግለሰብ ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣት በ15 ቀን ጊዜ ውስጥ በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት ድረስ መጥተው ካላሳወቁ ማህደር በማዘጋጀት አገልግሎት የምንሰጣቸው መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

አቶ አበረ ደባቡ እና ወ/ሮ ተኛኘ ካሰኝ በጉለሌ ክ/ከተማ ወረዳ 4 የቤት ቁጥር 866 ካርታ ቁጥር 35089 በተመዘገበ በእጃቸው መገኘት የነበረበት ካርታ የጠፋ በመሆኑ ይህንኑ አስመልክቶ የሚቀርብ ማንኛውም መቃወሚያ ካለ ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ታትሞ ከወጣ በ20 ቀን ውስጥ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ ጉለሌ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ማስረጃውን ይዛ ካልቀረበ ካርታው እንደጠፋ ተቆጥሮ በምትኩ አዲስ ካርታ በማዘጋጀት አገልግሎት የምንሰጥ መሆኑን እናሳውናቃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ በጉለሌ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በለሚ ኩራ ክ/ከተማ ወረዳ 03 ካርታ ቁጥር ቦ/አያ/10/100/1/20/17234/00 ሴሪ ቁጥር 1457126 ቤቱ ስፋት 46.54 ቤት ቁጥር 06/01 በአቶ ተስፋአለም ገ/ጊዮርጊስ ናይዝጊ ስም የተመዘገበ የቤት ማረጋገጫ ካርታ የጠፋ ስለሆነ ቤቱን በዕዳ ይዤዋለሁ፤ አስይዤዋለሁ የሚል አካል በ30 ቀናት በጋዜጣ ጥሪ ስለሚደረግ በተጠቀሰው ቀናት ውስጥ ለተቋሙ እንዲያሳውቁን እያልን በዚህ ምክንያት ለ30 ቀናት የሚቆይ በጋዜጣ ጥሪ እንዲደረግ እየጠየቅን ይህ ጋዜጣ ጥሪ ከተደረገ በኋላ አዲስ ካርታ የምንሰራ መሆኑና ሀላፊነት የማንወስድ መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

# የፋብሪካው የምርት ውጤት

## “ለማኑፋክቸሪንግ የወጪ ንግድ ከፍተኛ አስተዋፅኦ አለው”

የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)

- **ጠቅላይ ሚኒስትሩ በሀዋሳ ኢንዱስትሪ ፓርክ የቶዮ የፀሐይ ብርሃን ኃይል ማመንጫ ፋብሪካን ጎብኝተዋል**

**በስንታየሁ ምትኩ**

በሐዋሳ ኢንዱስትሪ ፓርክ የቶዮ የፀሐይ ብርሃን ኃይል ማመንጫ ፋብሪካ በከፍተኛ ጥራት የሚያመርታቸው የፀሐይ ብርሃን ሀይል ማመንጫዎች በማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ የሚገኘውን የወጪ ንግድ በማሳደግ ከፍተኛ አስተዋፅኦ እንደሚኖረው የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ገልጸዋል፡፡



ፎቶ- ከገፀ ድር

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በሀዋሳ ኢንዱስትሪ ፓርክ የቶዮ የፀሐይ ብርሃን ኃይል ማመንጫ ፋብሪካን ሲጎበኙ

ጠቅላይ ሚኒስትሩ በትናትናው ዕለት በሀዋሳ ኢንዱስትሪ ፓርክ የፀሐይ ብርሃን የኃይል ማመንጪያዎችን በማምረት ላይ ያለውን የቶዮ የፀሐይ ብርሃን ኃይል ማመንጫ ፋብሪካን እንቅስቃሴ በጎበኙበት ወቅት እንደተናገሩት፣ ፋብሪካው በከፍተኛ ጥራት በብዛት ምርት የማምረት አቅም የተላበሰና በዘመናዊ የማሽን ሥርዓት የሚሰራ ነው፡፡

ሁለት ተጨማሪ ማምረቻዎች በግንባታ ሂደት ላይ እንደሚገኙና ወደ ምርት የገባውን ማምረቻ ሥራ ሂደት መመልከታቸውን ያነሱት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ (ዶ/ር)፣ “ሥራው እሴት የተጨመረባቸው እና ያስቀመጥናቸውን ግቦች እና ፖሊሲዎች የሚያሳኩ ጨዋታ ቀያሪ ፕሮጀክቶች ላይ ትኩረት ከሚያደርገው የኢንቨስትመንት ስትራቴጂያችን ጋር የተጣጣመ ነው” ብለዋል፤ በይፋዊ የማህበራዊ ትስስር ገፃቸው ባሰፈሩት መረጃ።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ (ዶ/ር)፣ ከቀዳማዊት እመቤት ዝናሽ ታያቸው እና ልዑካቸው ጋር በመሆን ከሶስት ወር በፊት በቬትናም ለሶስት ቀናት ይፋዊ ጉብኝት ማድረጋቸው ይታወሳል፡፡ ጠቅላይ ሚኒስትሩ በጉብኝታቸው በሀገሪቱ የፀሐይ ብርሃን ሐይል ማመንጫዎችን (ሶላር ፓኔል) በማምረት ወደ ውጭ የሚልከውን ቶዮ የተሰኘውን የጃፓን ኩባንያ ተመልክተዋል፡፡ ኩባንያው በሐዋሳ ኢንዱስትሪ ፓርክ በመግባት ስራ የጀመረ ሲሆን፣ በጉብኝታቸው ፋብሪካው የፀሐይ ብርሃን ሀይል ማመንጫዎችን ከማስፋት በተጨማሪ የፀሀይ ሀይል ማመንጫዎች ግንባታ ላይ እንዲሳተፍ መጠየቃቸው ይታወሳል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ (ዶ/ር) በጉብኝታቸው ወቅት ባደረጉት ንግግር በእስያ በወጪ ንግድ በግንባር ቀደምትነት ከሚጠቀሱ ሀገራት መካከል ቬትናም አንዷ ናት፡፡ በዓመትም እስከ 400 ቢሊዮን ዶላር ገቢ ከወጪ ንግድ ታገኛለች፡፡ የውጭ ንግዷንም ያሳደገችው ኢንቨስትመንትን በመሳብ ነው፡፡ ከዚህም ኢትዮጵያ ልምድ በመቅሰም የወጪ ንግድ አቅሟን ማሳደግ ይጠበቅባታል፡፡

ቬትናም ከወጪ ንግድ ከፍተኛ ገቢ ከምታገኝባቸው ዘርፎች አንዱ የፀሐይ ብርሃን ሀይል ማመንጫ እንደሆነ ያነሱት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ (ዶ/ር)፣ ኢትዮጵያ የምትከተለው የአረንጓዴ ልማት ፖሊሲ እንደመሆኑ አዳጊ የሆነውን የሀይል አቅርቦት ፍላጎቷን ለመመለስ ንፁህ የሀይል አማራጮች ላይ መስራት ያስፈልጋታል፡፡ ለዚህም ከፍተኛ የማምረት አቅም ያለው የቶዮ የፀሐይ ብርሃን ኃይል ማመንጫ በኢትዮጵያ ያለውን ተሳትፎን እንዲያጠናክር መጠየቃቸው ይታወሳል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትሩ በቬትናም የቬትናም ጠቅላይ ሚኒስትር ፋም ሚን ቺን በቤተ መንግሥታቸው ይፋዊ የአቀባበል ስነ ስርዓት ያደረጉላቸው ሲሆን፣ ሁለቱ መሪዎችና የልኡካን ቡድኖቻቸው ለትብብር የሚሆኑ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ጉዳዮችን በተለይም የልምድ ልውውጥንና ኢንቨስትመንትን ጨምሮ በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ሀሳብ መለዋወጣቸው ይታወሳል፡፡

መሪዎቹ በተገኙበትም ሁለቱ ሀገራት በንግድ እና በትምህርት ትብብር ላይ የመግባቢያ ስምምነቶችን ተፈራርመዋል። በተጨማሪም በአዲስ አበባ እና በሃኖይ መካከል በኢትዮጵያ አየር መንገድ የቀጥታ በረራ መንገድ የሚያመቻች የሲቪል አቪዬሽን ስምምነት ተደርጓል።

የጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) የቬትናም ጉብኝት በሁለቱ ሀገራት መካከል ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት ከተመሰረተ ከሃምሳ ዓመታት በኋላ በሀገር መሪ ደረጃ የመጀመሪያ ይፋዊ ጉብኝት መሆኑን የጠቅላይ ሚኒስትር ፅህፈት ቤት ያወጣው መረጃ ያመለክታል፡፡

# ማስታወቂያ

በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ወረዳ 02 በአዲሱ ወረዳ 13 በካርታ ቁጥር 02/94/12671/00 በሴሪ ቁጥር 055174 ሸዋዬ ገዳሙ ተሰጥቷቸው የነበረው ማህደር የጠፋ ስለሆነ በባለጉዳዩ አናንያ መስፍን በኩል ስለደረሰን በማናቸውም ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል በጋዜጣ ከወጣበት እስከ 20 ቀን ድረስ ለንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ መሬት አስተዳደር ጽ/ቤት ድረስ አቤቱታ እንዲቀርብ፡፡ ይዤዋለሁ የሚል ከሌለ ሌላ ማህደር እንደሚከፈትላቸው እናሳውቃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የን/ስ/ላ/ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

አቶ ወ/ሮ እነ ፲ አለቃ አበበ መሡለ ላቀው የተባሉት በየካ ክ/ከተማ ወረዳ .... ቀበሌ .... ወይም በቀድሞው ወረዳ - ቀበሌ - የቤት ቁጥር 1311 የካርታ ቁጥር 28948 ሴሪ ቁጥር - ተመዝግቦ የተሰጣቸው ካርታ ስለጠፋባቸው በማንኛውም ምክንያት ይዤዋለው የሚል ካለ እስከ 20 ቀን ድረስ አዲስ አበባ ከተማ የካ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት እንዲቀርቡ ባይቀርቡ ግን በምትኩ ሌላ የሚሰጣቸው መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የየካ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

አቶ ይስሐቅ አለባቸው በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 14 የካርታ ቁጥር ቦሌ14/71/7/7/95-4317/30202/01 ሴሪ ቁጥር 058593 የሆነው ይዞታ የቤት ባለቤትነት ምዝገባ ምስክር ወረቀት ስለጠፋባቸው በማናቸውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ /ይዤዋለሁ/ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እስከ 90 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፍኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ቦሌ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ወረዳ 1 አስተዳደር ውስጥ በካርታ ቁጥር 044379 በሴሪ ቁጥር 038430 በወ/ሮ ከበቡሽ ክብርቴ የተመዘገበ ይዞታ ማህደራቸው ከማህደር ክፍላችን መገኘት የነበረበት የጠፋባቸው ስለሆነ ማህደሩን የያዘ ግለሰብ ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት በ30 ቀን ጊዜ ውስጥ በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት ድረስ መጥተው ካላሳወቁ ማህደር በማዘጋጀት አገልግሎት የምንሰጣቸው መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

አቶ/ወ/ሮ/ወ/ሪት ወልዴ መስፍን ጤናዬ የተባሉት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በየካ ክ/ከተማ በቀድሞ ወረዳ 12 በቀድሞ ቀበሌ 19 በአዲሱ ወረዳ 03 የሚገኘው ቤትና ይዞታ በካርታ ቁጥር የካ/19868/09 በሴሪ ቁጥር 049621 የሆነ በአቶ/ወ/ሮ/ወ/ሪት ወልዴ መስፍን ስም በቀን 03/05/09 ዓ.ም ተመዝግቦ የተሰጣቸው የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ የጠፋባቸው ስለሆነ በማንኛውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ (ይዤዋለሁ) የሚል አካል(ሰው) ካለ እስከ 30 ቀን ድረስ በየካ ክ/ከተማ የመሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የይዞታ አገልግሎት ቡድን ድረስ እንዲቀርቡ ካልቀረቡ ግን በምትኩ ሌላ የይዞታ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት (ካርታ) የምንሰጣቸው መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የየካ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

## መዲናዋ ... ከገጽ 1 የዞረ

ወዲህ በሁለንተናዊ መልኩ ለውጥ እያመጣች ትገኛለች:: እንደ የዲፕሎማሲ ማዕከልነቷም የዓለምን ዓይንና ቀልብ የሳቡ ትላልቅ ዓለም አቀፍ ጉባኤዎችን በስፋት በማስተናገድ ላይ ናት:: በየጊዜው በሚደረጉ ትላልቅ ጉባኤዎች የሚሳተፉ እንግዶችንም እንደ ስሟ ውብና አበባ ሆና፣ እንደ ብርሃን ፈክታ ተቀብላ እየሸኘች ነው::

የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ የከተማዋን የ2017 በጀት ዓመት የዕቅድ አፈፃፀም በአዲስ አበባ ምክር ቤት ተገኝተው ባቀረቡበት ወቅት እንደተናገሩት፣ በበጀት ዓመቱ ከ150 በላይ አህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ ኮንፈረንሶች፣ ኤግዚቢሽኖችና ኤክስፖዎች በመዲናዋ ተካሂደዋል:: በቅርቡም ከሐምሌ 20 እስከ ሐምሌ 22 ቀን 2017 ዓ.ም ለሶስት ቀናት የቆየውን እና የተለያዩ ሀገራት መሪዎች፣ ሚኒስትሮች፣ የስራ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች የተሳተፉበትን ሁለተኛው የተባበሩት መንግስታት የምግብ ስርዓት ጉባኤ ማካሄዷ ይታወሳል::

ከጳጉሜ 3 እስከ ጳጉሜ 5 ቀን 2017 ዓ.ም ደግሞ ኢትዮጵያ ሁለተኛውን የአፍሪካ የአየር ንብረት ለውጥ ጉባኤን ከአፍሪካ ህብረት ጋር በመተባበር ታስተናግዳለች:: በጉባኤውም ከ20 ሺህ እስከ 25 ሺህ ሰዎች የሚሳተፉ ሲሆን የ45 የአፍሪካ ሀገራትና የሌሎችም ሀገራት መሪዎች፣ የዓለም አቀፍ ድርጅቶች ሊቀ መናብርት፣ ዲፕሎማቶች፣ አምባሳደሮች፣ በዘርፉ የተሰማሩ ግብረ ሰናይ ድርጅቶች፣ ሲቪል ማህበራት፣ የልማት አጋሮችና የተለያዩ ባለድርሻ አካላት እንደሚሳተፉ የኢፌዴሪ ፕላንና ልማት ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ስዩም መኮንን ከአንድ ሳምንት በፊት ለመገናኛ ብዙሃን በሰጡት መግለጫ ጠቁመዋል::

### አዲስ አበባ እንዴት ተመራጭ ልትሆን ቻለች?

የኢትዮጵያውያንና የአፍሪካ መዲና፣ የተለያዩ ቀጣናዊ፣ አህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ ድርጅቶች፣ የበርካታ ኤምባሲዎችና ቆንስላዎች መገኛ የሆነችው አዲስ አበባ በዓለም አቀፍ ደረጃ ቀዳሚ ከሚባሉት የዲፕሎማሲ ከተሞች ከኒውዮርክ እና ጀኔቭ በመቀጠል ሶስተኛ ደረጃ ላይ ትገኛለች:: ለዚህ የበቃችው ኢትዮጵያ በረጅም ዘመን ታሪኳ ነፃነቷን አስጠብቃ በመዝለቋ፣ የአፍሪካ ሀገራት ከቅኝ ግዛት እንዲላቀቁ ባደረገችው ትግል፣ ከየዓለም መንግስታት ማህበር (ሊግ ኦፍ ኔሽን) እስከ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት፣ የአፍሪካ ህብረት (የቀድሞ አፍሪካ አንድነት ድርጅት) ድርጅቶችን በመመስረትና በአባልነት፣ በተለያዩ አህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ ጉዳዮች ያላት ሚና እና ጉልህ ተሳትፎ እንደሆነ በኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ ዲፕሎማሲን ያስተማሩት እና በሶማሊላንድ ሃርጌሳ ዩኒቨርሲቲ የሰላምና ደህንነት ጉዳዮች መምህር በመሆን እየሰሩ የሚገኙት የፖለቲካ ሳይንስ እና ዓለም አቀፍ ግንኙነት ምሁር አቶ በፈቃዱ ዳባ ለዝግጅት ክፍላችን ተናግረዋል::



ፎቶ- ከገፀ ድር

ለኮንፈረንስ ቱሪዝም ተመራጭ ከሆኑት አንዱ ኮሪደር ልማቱ ነው

አዲስ አበባ በዓለም አቀፍ ዲፕሎማሲ ከፍ ያለ ቦታ ያላት ቢሆንም፤ ከዓመታት በፊት እንግዶቿን በአግባቡ ማስተናገድ የሚያስችል በቂ የመሰረተ ልማት አቅርቦትና አገልግሎት ነበራት ማለት አይቻልም:: ገፅታዋ እና የምታቀርበው አገልግሎት ስሟንና ሚናዋን የሚመጥን እንዳልነበር ብዙዎች ይስማሙበታል:: ስድስት አስርት ዓመታት ወደኋላ መለስ ብንል በፈረንጆቹ አቆጣጠር በ1950ዎቹ መጨረሻ አካባቢ የተባበሩት መንግስታት የአፍሪካ ኢኮኖሚክ ኮሚሽን ዋና ፅህፈት ቤት ኢትዮጵያ ውስጥ እንዲሆን ሲወሰን በአዲስ አበባ ዓለም አቀፍ ኮንፈረንሶችን ለማስተናገድ የሚመጥን የመሰብሰቢያ አዳራሽ ማግኘት ፈተና ሆኖ ነበር። በወቅቱ የኢትዮጵያ መሪ የነበሩት ቀዳማዊ ኃይለ ስላሴ ለድርጅቱ ጽህፈት ቤትና ለስብሰባ አገልግሎት የሚውል ህንጻ በአጭር ጊዜ እንዲገነባ አዝዘው እ.ኤ.አ በ1961 ዛሬ የአፍሪካ አዳራሽ እየተባለ የሚጠራው ህንፃ እንደተመረቀ "የአፍሪካ አዳራሽ አዲስ አበባ" በሚል ርዕስ በተባበሩት መንግስታት የአፍሪካ ኢኮኖሚክ ኮሚሽን ገፀ ድር የወጣው ሰነድ ያሳያል::

ከዚህ በኋላ በተለያዩ ጊዜያት ከአፍሪካ አዳራሽ በተጨማሪ የአፍሪካ ህብረት ዋና ፅህፈት ቤት ህንፃን ጨምሮ ደረጃቸውን የጠበቁ ዘመናዊ ሆቴሎች፣ መሰረተ ልማቶች ተገንብተው ወደ አገልግሎት ገብተዋል:: እንደዚያም ሆኖ የተሰሩት ስራዎች መዲናዋ ያላትን ስምና ሚናዋን የሚመጥኑ ነበሩ ማለት እንደማይቻል የተባበሩት መንግስታት ድርጅትን ጨምሮ በተለያየ ኃላፊነት ከሶስት አስርት ዓመታት በላይ ኢትዮጵያን በዲፕሎማሲው መስክ ያገለገሉት አንጋፋው ዲፕሎማት አምባሳደር ጥሩነህ ዜና ከዚህ ቀደም ለዝግጅት ክፍላችን በሰጡት መረጃ ማንሳታቸው ይታወሳል::

**አዲስ አበባ የአፍሪካ ህብረት ዋና ፅህፈት ቤት መቀመጫ፣ በዓለም ሶስተኛዋ የዲፕሎማሲ ማዕከል ከመሆኗ ባሻገር በኮሪደር ልማት፣ የወንዝ ዳርቻ እና ትላልቅ ፕሮጀክቶችን በመገንባት፣ በፅዳትና ውበት ገፅታዋ በመቀየሩ ለጉባኤዎች ተመራጭ አድርጓታል**

አምባሳደር ጥሩነህ እንደሚናገሩት፣ የአፍሪካ መሪዎች ከዚህ ቀደም የአፍሪካ ህብረት የመሪዎች ጉባኤ ላይ ለመሳተፍ ወደ አዲስ አበባ በሚመጡበት ጊዜ ከአፍሪካ አዳራሽ ውጪ የሚሰበሰቡበት ስፍራ አልነበረም:: የጉባኤ ታዳሚዎች ከቦሌ ዓለም አቀፍ አየር ማረፊያ አንስቶ የአፍሪካ ኢኮኖሚክ ኮሚሽን ግቢ ውስጥ የሚገኘው የአፍሪካ አዳራሽ እስኪደርሱ ድረስ፣ ከመንገድ በግራና በቀኝ ያሉት ስፍራዎች ቆሻሻ፣ ለእይታ ምቹና ደስ የማይሉ ስለነበር በቆርቆሮ ይታጠሩ ነበር።

የፖለቲካ ሳይንስ እና ዓለም አቀፍ ግንኙነት ምሁር አቶ በፈቃዱም ይህንን ሀሳብ ይጋሩታል:: "ከዚህ በፊት አንዳንድ የአፍሪካ መሪዎች በአፍሪካ ህብረት ስልጣን ለማግኘት ሳይሳካላቸው ሲቀር እንዲሁም በተለይ የነበራትን የመሰረተ ልማት ሁኔታ በማንሳት የአዲስ አበባ የአፍሪካ መዲናነት ላይ ጥያቄ ያነሱ ነበር። በቅርብ ዓመታት ከተማዋን ለመቀየር በተሰሩ ስራዎች ሲነዙ የነበሩ አሉታዊ ፕሮፖጋንዳዎችን ማፍረስ ተችሏል። በአሁኑ ሰዓት በማይታመን መልኩ ፅዱ፣ ውብና አረንጓዴ ከተማ ሆናለች" ብለዋል።

የአፍሪካ ልማት ባንክ ፕሬዝዳንት አዴሲና ሰሞኑን፣ "አዲስ አበባ የአፍሪካ ህብረት መቀመጫ ብትሆንም ከብዙ ዓመታት በፊት የነበራት ደረጃ ይህንን ተቋም ለማስተናገድ የሚመጥን አይደለም በሚል ቅሬታ ይነሳ ነበር። ዛሬ በየትኛውም የከተማዋ አካባቢ ብንመለከት 'አፍሪካ የምትኮራባት' ከተማ ሆናለች" ነው ያሉት::

የአዲስ አበባ ከተማ ቱሪዝም ኮሚሽን ኮሚሽነር አቶ ሁንዴ ከበደ ለአዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ እንደተናገሩት፣"በአዲስ አበባ ከዚህ በፊት ባልተለመደ መልኩ ግዙፍ የቱሪዝም መሰረተ ልማቶች እየተገነቡ ነው:: ከአፍሪካ ህብረት አዳራሽ በተጨማሪ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ አዲስ አበባን ለኮንፈረንስ ቱሪዝም ምቹ ያደረጉ የዓድዋ ድል መታሰቢያ፣ የአዲስ ዓለም አቀፍ ኮንቬንሽን ማዕከልና ሌሎች መሰረተ ልማቶች ተገንብተዋል።"ብለዋል::

የፖለቲካ ሳይንስና ዓለም አቀፍ ግንኙነት ምሁሩ አቶ በፈቃዱ ለዝግጅት ክፍላችን እንደገለፁት፣ ለዓለም አቀፍ ጉባኤዎች ተመራጭ የሚሆኑት ምቹ መሰረተ ልማትና አስተማማኝ ሰላም ያለባቸው ሀገራት ከተሞች ናቸው። አዲስ አበባ የአፍሪካ ህብረት ዋና ፅህፈት ቤት መቀመጫ፣ በዓለም ሶስተኛዋ የዲፕሎማሲ ማዕከል ከመሆኗ ባሻገር በኮሪደር ልማት፣ የወንዝ ዳርቻ እና ትላልቅ ፕሮጀክቶችን በመገንባት፣ በፅዳትና ውበት ገፅታዋ በመቀየሩ ለጉባኤዎች ተመራጭ አድርጓታል። አስተማማኝ ሰላም እና ምቹ የአየር ሁኔታ መኖር እንዲሁም የህዝቡ እንግዳ ተቀባይነት አኩሪ ባህል መኖርም ሌሎች ተጠቃሽ ምክንያቶች ናቸው::

ወደ ገጽ 10 ዞሯል

ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍትህ ቢሮ ጋር በመተባበር ዘወትር ቅዳሜ የሚቀርብ

# እንደራሴነት /ውክልና/ ምንድን ነው?

**በመሰረት ፀሐይ (ዐቃቤ ህግ)**



## እንደራሴነት /ውክልና/ ምንድን ነው? ከምን ይመነጫል? ለምን ይጠቅማል?

በማንኛውም የኑሮ መስመር ሰዎች ማከናወን ያለባቸውን ተግባር እራሳቸው የሚያከናውኑት ሲሆን፤ አንዳንድ ህጋዊ ተግባራትን በራስ ማከናወን የማይቻልበት ሁኔታ ያጋጥማል፡፡ ለምሳሌ አንድ ሰው ያሰበውን ተግባር ለመፈጸም /ለማከናወን/ ህመም ወይም በሌላ ምክንያት በአካል ሳይገኝ ሊቀር ይችላል፡፡ በመሆኑም ስለ እርሱ ሆኖ ህጋዊ ተግባራትን የሚያከናውን ሰው መሾም/መሰየም/ አስፈላጊ ይሆናል ማለት ነው፡፡ ከዚህ አኳያ የኢትዮጵያ ፍትሐ ብሔር ህግ ከቁጥር 2179 እስከ 2265 ስለውክልና በግልፅ አስቀምጧል፡፡

በፍትሐ ብሔር ህግ አንቀፅ 2179 ላይ በግልፅ እንደተቀመጠው ውክልና በወካይና በተወካይ መካከል በሚደረግ ስምምነት ወይም ከህግ ሊመነጭ ይችላል፡፡

አንድ ተወካይ የውክልና ወሰኑን ሳያልፍ ያከናወነው ህጋዊ ተግባር በወካዩ ስም እንዳደረገው የሚቆጠር መሆኑን የፍትሐ ብሔር ህጉ በአንቀፅ 2189(1) ደንግጓል። የውክልና ተግባር የሚከናወነው በወካዩ ስም መሆኑ ህጉ ያሰምርበታል፡፡ አንድ ተወካይ ከተወከለበት ስራ ውጭ አከናውኖ ቢገኝ ሿሚው እስካላጸደቀው ድረስ ስለሚያስከትለው ኃላፊነት የተወካዩ ኃላፊነት ብቻ ይሆናል ማለት ነው፡፡ ሆኖም የሦስተኛ ወገኖች መብት ለመጠበቅ ሲባል ተወካዩ ስለሚያደርሰው ጉዳት ሿሚው ኃላፊነት እንዳለበት የዚሁ ቁጥር ንዑስ አንቀጽ(3) ያመላክታል፡፡

ውክልና በፍትሐ ብሔር ህጉ አንቀፅ 2204 እና 2205 መሰረት ጠቅላላ እና ልዩ ውክልና ተብሎ ለሁለት ሊከፈል ይችላል፡፡ ጠቅላላ ውክልና የወካዩን ንብረት ጠቅላላ የማስተዳደር ስራን የሚያመላክት ሲሆን የወካዩን ሀብት የማስቀመጥ፣ የመጠበቅ፣ ከሦስት ዓመት ለማያልፍ ዘመን የማከራየት፣ በብድር የተሰጠውን ሀብት መሰብሰብ፣ ከሀብት የሚመጣውን ገቢ ተቀብሎ የማስቀመጥ እና የተሰጠውን ሀብት የመሰብሰብ ለተከፈሉ እዳዎች ደረሰኝ የመስጠት ስራዎች ያካትታል፡፡ ከእነዚህ ውጭ ያሉ ተግባራትን ለማከናወን ወካዩ ለተወካዩ ልዩ ውክልና መስጠት እንዳለበት የህጉ መልዕክት ያስረዳል፡፡

ለምሳሌ የማይንቀሳቀስ ንብረት መሸጥ፣ መለወጥ፣ ካፒታሎችን አሲዞ መበደር፣ ስጦታ ማድረግ፣ በአንድ ማህበር ዘንድ ለመግባት የለውጥ ግዴታን ውል መፈራረም፣ ስለወካይ ሆኖ ይቅርታ ማድረግ፣ በፍርድ ቤት ጠበቃ ሆኖ ለመከራከር የተለየ ውክልና እንደሚያስፈልግ የፍትሐ ብሔር ህጉ አንቀፅ ቁጥር 2205 ላይ ተደንግጓል፡፡

ስለዚህ ውክልና በህብረተሰቡ ከተለመዱ ህጋዊ ተግባራት አንዱ ቢሆንም የህግ ውክልና ግንዛቤ ይዞ በማይንቀሳቀስ ተወካይ ኃላፊነት የሚያስከትል በመሆኑ ማንኛውም ዜጋ የህግ ግንዛቤ እንዲኖረው ያስፈልጋል፡፡

ውክልና ከህግ ሊመነጭ ይችላል። በተለይም በቤተሰብ ህጉና በሌሎችም ህጎቻችን ውክልና ከህግ እንደሚመነጭ ይታወቃል፡፡ በውክልና ህግ በኩል ዳኞችም ውክልና እንደሚሰጡ በዚሁ ህግ አንቀፅ 2253 ላይ ደንግጓል፡፡ "አንድ የተወሰነ ስራን ወይም የተመደቡ ስራዎችን በሌላ ስም ሆኖ እንዲያከናውን ዳኞች ጠባቂ ባለአደራ ለተባለው ለአንድ ሰው ውክልና ለመስጠት ይችላሉ፡፡" በሚል ተጠቅሷል፡፡ ይህም የሚያስከትለው ውጤት በተከታታይ አንቀጾች ተደንግጓል፡፡ አንድ ሰው በውል ከወካይ ጋር ግንኙነት ሳይኖረው በራሱ ፈቃድ አንዳንድ ተግባራትን ስለ ሌላው ሊያከናውን ይችላል፡፡ በግልጽ ውክልና ስልጣን ሳይሰጠው አንድን ስራ የሚያከናውን ሰው የወካዩን ፈቃድ እስኪያገኝ ድረስ የፍትሐ ብሔር ህግ ኃላፊነት ስለሚያስከትልበት አስቀድሞ መጠንቀቅ አለበት፡፡

በዋናነት ውክልና አንድ ሰው በሌላ ሰው ስም የሌላውን ህጋዊ ተግባር ማከናወን ሲሆን በግዢ ወይም የሽያጭ ኮሚስዮን አንድ ውክልና የተሰጠው ሰው በራሱ ስም ህጋዊ ተግባራትን ሊያከናውን እንደሚችል የፍትሐ ብሔር ህጉ በአንቀፅ 2234 እና ተከታዮቹ ስራ ባሉት ድንጋጌዎች ያስቀምጣል፡፡ የግዢ ወይም የሽያጭ ኮሚስዮን ማለት ኮሚሲዮነሩ ተብሎ የሚጠራው ተወካይ ኮሚስዮን ሰጭ ተብሎ ለሚጠራው ወካይ ተወካይ በራሱ ስም ሆኖ፤ ነገር ግን ለወካዩ ጥቅም የንግድ እቃዎችን፣ ዋጋ ያላቸውን ወረቀቶችን ወይም ይህንን የመሳሰሉትን ሌሎች ነገሮች ለመግዛት ወይም ለመሸጥ ግዴታ የሚገባበት ውክልና ማለት ነው። ውክልና ውል እንደመሆኑ የሦስተኛ ወገኖች መብት ምንጊዜም ይጠበቃል። አንድ ተወካይ በወካዩ ላይ ጉዳት እንዳያደርስ ህግ ከጣለበት ግዴታ በላይ ስራውን የሚያከናውን በጥብቅ እምነት መሆን እንዳለበት የውክልና ህግ በጥብቅ ይደነግጋል፡፡ በተጨማሪም ተወካዩ በሦስተኛ ወገኖች ላይ ለሚያደርሰው ጉዳት የወካይ ኃላፊነት መሆኑ በተለያዩ አንቀፆች ተመላክቷል፡፡ ስራን በትጋት የሚያከናውን ተወካይ የድካም ዋጋ እንደሚያገኝ፣ ያወጣው ማንኛውም ወጪ እንደሚካካስለት በፍ/ህ/ቁ 2219 ንዑስ አንቀጽ(1) ላይ ተመላክቷል፡፡

በአጠቃላይ ውክልና አንድ በራሱ ስራን ማከናወን ያልቻለ ሰው በስሙ ሌላ ሰው እንዲያከናውንለት የሚደረግ ግንኙነት ሲሆን፤ ሰው ባለው ተፈጥሮ ምሉዕነት ስለማይኖረው እንዲህ አይነቱ ግንኙነት ጠቃሚ የሆነ ማህበራዊ ግንኙነት ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ ለምሳሌ አንድ ሰው ከአቅም በላይ በሆነ ሁኔታ ስራውን ላያከናውን ይችላል፡፡ በህመም፤ በህግ ቁጥጥር ስር መሆን፤ ከሀገር ውጭ በመሆን፤ ስራው ውስብስብ በመሆኑ ምክንያት በራሱ ሁኔታዎችን ላያከናውን ይችላል። ስለሆነም ህጉ ባስቀመጠው መርህ መሰረት ይህንኑ ህጋዊ ተግባር ሊያከናውን የሚችል ማንኛውንም ሰው በመምረጥ እና ህጋዊ ውል በመዋዋል ስራውን ማከናወን መቻል ተቀባይነት ያለው ጉዳይ ስለሆነ በዚህ ረገድ ተጠቃሚ መሆን ይቻላል ማለት ነው፡፡

# ማስታወቂያ

## የቅጥር ማስታወቂያ

**የአዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ ከዚህ በታች በተገለፁት ክፍት የስራ መደቦች ላይ አመልካቾችን አወዳድሮ ለመቅጠር ይፈልጋል።**

| ተ.ቁ | የሥራ መደብ መጠሪያ | ደረጃ | ተፈላጊ የትምህርት ደረጃ | አግባብ ያለው የሥራ ልምድ | የሙያ ዓይነት | መደብ መታወቂያ ቁጥር | ብዛት | የቅጥር ሁኔት | ደመወዝ | የሥራ ቦታ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| **የዲጂታል ሚዲያና ህትመት ዘርፍ** | | | | | | | | | | |
| 1 | የአፋን ኦሮሞ ማህበራዊ ሚዲያ ከፍተኛ ሪፖርተር | X | ቢ.ኤ./ኤም.ኤ ዲግሪ | 5/3 ዓመት | በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን፣ በሀገር ውስጥ ቋንቋና ሥነ ጽሁፍ፣ ፖለቲካል ሳይንስና ዓለም አቀፍ ግንኙነት፣ ቲያትሪካል አርት፣ በህግ፣ እንዲሁም በጤና፣ በቢዝነስና ኢኮኖሚክስ፣ በማህበራዊ ሳይንስ፣ በስነ ትምህርት ዘርፎች ወይም በተዛማጅ የት/ት መስክ | አ/18.1147 | 1 | በቋሚነት | በተቋሙ ስኬል መሰረት | አዲስ አበባ |

1. አመልካቾች ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት 10/አስር/ ተከታታይ የስራ ቀናት ውስጥ የትምህርት ማስረጃችሁን ዋናውንና የማይመለስ ፎቶ ኮፒ በመያዝ በተቋሙ የሰው ኃብት ስራ አመራር እና ልማት ዳይሬክቶሬት ቢሮ ቁጥር 05 ድረስ በመምጣት እንድትመዘገቡ እናሳስባለን፡፡
2. ከግል ድርጅቶች የሚቀርብ የስራ ልምድ ማስረጃ የስራ ግብር የተከፈለበት ስለመሆኑ ከግብር ሰብሳቢ መ/ቤት ማስረጃ ማምጣት ይኖርባቸዋል፡፡
3. የስራ ልምድ የሚጠይቀው ከወጣው ክፍት መደብ ጋር ቀጥተኛ መሆን አለበት፡፡
4. በቴክኒክና ሙያ/ሌቬል የሚወዳደሩ የብቃት ማረጋገጫ/COC ማቅረብ አለባቸው፡፡
5. የምዝገባው ቀን ከነሐሴ 12 ቀን 2017 ዓ.ም እስከ ነሐሴ 23 ቀን 2017 ዓ.ም ድረስ
6. የፈተና ቀን በውስጥ ማስታወቂያ ይገለፃል፡፡
7. ለበለጠ መረጃ አድራሻ አምስት /5/ ኪሎ ቅድስተ ማርያም ፊት ለፊት ማህበረ ቅዱሳን ህንፃ ጐን ስልክ 0111551848

**አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ**

---

ከላይ በርዕሱ ለመግለጽ እንደተሞከረው በሰብለድንግል ገብረትንሳኤ አድሃኖም ስም በልደታ ክ/ማ ወረዳ 03 በካርታ ቁጥር 20919/26164/00 ሴሪ ቁጥር 050435 የተመዘገበ ይዞታ ካርታ ጠፋብኝ ብለው በቀን 25/11/2017 ዓ.ም በማመልከቻ የጠየቁ ስለሆነ፣ በመሆኑም በጠየቁት መሰረት የምትክ ካርታ አገልግሎት ለመስጠት ያመች ዘንድ ከላይ በተጠቀሱት ካርታ ቁጥሮች እና በባለጉዳይ ስም የተመዘገበውን የይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት /ኦርጅናል ካርታም ሆነ ኮፒውን/ ይዤዋለሁ የሚል ማንኛውም አካል ካለ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ 30 ቀን ድረስ ልደታ ክ/ከተማ የመሬት ይዞታ መብት ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ካልቀረበ በመመሪያ ቁጥር 61/2010 አንቀጽ 72 ንዑስ አንቀጽ 3 መሰረት በምትኩ ሌላ የመሬት ይዞታ መብት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የሚሰጣቸው መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ልደታ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በባንችአምላክ አባተ አሊ ስም የተመዘገበ በካርታ ቁጥር ቦሌ15/4/8/6/116730/211323/01 የሴሪ ቁጥር 0161230 የተሰጠበት ቀን 20/08/2012 ዓ.ም የቦታው ስፋት 400 ሜ.ካ የሆነው ካርታ መጥፋቱ ተገልጾ ለፖሊስ እንዲጻፍልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡

በመሆኑም በለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ጽ/ቤት ወረዳ 03 የሆነው መኖሪያ ቤት በባንችአምላክ አባተ አሊ ስም የተመዘገበ በካርታ ቁጥር ቦሌ15/4/8/6/116730/211323/01 የሴሪ ቁጥር 0161230 የተሰጠበት ቀን 20/08/2012 ዓ.ም የቦታው ስፋት 400 ሜ.ካ የሆነው የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ኦርጅናል የጠፋ ስለሆነ ይዞታ ቤቱን በዕዳ ይዤዋለሁ፤ አስይዤዋለሁ የሚል አካል በ30 ቀናት በጋዜጣ ጥሪ ስለሚደረግ በተጠቀሰው ቀናት ውስጥ ለተቋሙ እንዲያሳውቁን እያልን በዚህ ምክንያት ለ30 ቀናት የሚቆይ በጋዜጣ ጥሪ እንዲደረግ እየጠየቅን ይህ ጋዜጣ ጥሪ ከተደረገበት በኋላ ካርታውን የምናዘጋጅ ይሆናል፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

ሱራፌል አለነ ስዩም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 08 የይዞታ መለያ ቁጥር AA000060808580 የሆነው ይዞታ በጽ/ቤታችን ተመዝግቦ የሚገኘው ይዞታ የቤት ባለቤትነት ምዝገባ ምስክር ወረቀት ስለጠፋባቸው በማናቸውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ /ይዤዋለሁ/ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እስከ 90 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ቦሌ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

## መዲናዋ... ከገጽ 8 የዞረ

መዲናዋ በኮንፈረንስ ማዕከልነቷ ተመራጭ እንድትሆን አቅም ከሆኗትና በ2017 ዓ.ም አገልግሎት መስጠት ከጀመሩ ፕሮጀክቶች መካከል የአዲስ ዓለም አቀፍ ኮንቬንሽን ማዕከል ተጠቃሽ ነው፡፡ ማዕከሉ በተመረቀበት ወቅት የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ እንደተናገሩት፣ ከለውጡ ማግስት ጀምሮ የተሰሩ በርካታ ስራዎች "አዲስ አበባን እንደ ስሟ አበባ፣ የዓለም አቀፍ ዲፕሎማሲ ማዕከልነቷ የተጠናከረ፣ በአፍሪካና በዓለም አቀፍ ያለባትን ድርብርብ ኃላፊነት በብቃት የምትወጣና ተወዳዳሪ ከተማ" እያደረጋት እንደሆነ ተናግረዋል፡፡

የአዲስ ዓለም አቀፍ ኮንቬንሽን ማዕከል የማያቋርጥ ሀብት መፍጠሪያ፣ ለገፅታ ግንባታና ለቱሪስት ስበት ትልቅ ሚና የሚጫወት ነው፡፡ አለም አቀፋዊ ኮንፈረንሶችን፣ የንግድ ውይይትና ስምምነቶችን፣ ባህላዊ መድረኮችን፣ ልዩ ኤግዚቢሽን የሚስተናገዱበት ቦታ ነው፡፡ "አዲስ አበባ የአፍሪካ ህብረት ጉባኤዎችን ብቻ አይደለም፣ ማንኛውም ዓለም አቀፍ ጉባኤ፣ ኮንፈረንስ፣ ኤግዚቢሽን ለማስተናገድ የሚያስችላትን ግብአት እያሟላች ስለመሆኗ አንዱ ማሳያ ነው።" ብለዋል፡፡

አዲስ አበባ በዓለም አቀፍ ደረጃ የኮንፈረንስ ማዕከል እንድትሆን በቅርብ ዓመታት ከተማዋ እያሳየችው ካለው እድገትና የማስተናገድ አቅሟ እያደገ መምጣት ባሻገር ኢትዮጵያ በጉባኤዎቹ በሚመከርባቸው የተለያዩ ጉዳዮች ላይ ያከናወነችው አርዓያነት ያለው ተግባር አስተዋፅኦ አድርጓል፡፡ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) የ2017 በጀት ዓመት የአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብር ማስጀመሪያ ፕሮግራም ላይ እንደተናገሩት፣ ኢትዮጵያ ከተባበሩት መንግስታት ድርጅትና ኢጣሊያ ጋር በመተባበር ሁለተኛውን የምግብ ስርዓት ጉባኤ እንድታዘጋጅ የተመረጠችው በምግብ ራስን ለመቻል በሚደረግ ጥረት ተምሳሌት የሆነች ሀገር በመሆኗ ነው፡፡ በጿጉሜ ወር ላይ ሁለተኛውን የአፍሪካ የአየር ንብረት ለውጥ ጉባኤን እንድታዘጋጅ የተመረጠችበት ዋነኛው ምክንያትም የአየር ንብረት ለውጥን ለመከላከል በሚደረገው ጥረት ፊር ቀዳጅ ስራ እያከናወነች እንደሆነ በመታመኑ ነው፡፡

ሁለተኛው የአፍሪካ የአየር ንብረት ለውጥ ጉባኤ ገፀ-ድሩ ላይ የወጣው መረጃም የጠቅላይ ሚኒስትሩን ሀሳብ የሚያጠናክር ነው፡፡ የአፍሪካ የዲፕሎማሲ መዲና፣ የአፍሪካ ህብረት ዋና መቀመጫ፣ የነፃነት ምልክት የሆነችው ኢትዮጵያ የአየር ንብረት ለውጥን ለመከላከል ለሚያስፈልገው የጋራ ርዕይና አንድነት ወካይ ናት፡፡ ኢትዮጵያ ለረጅም ጊዜ በተለያዩ ዘርፎች ከአረንጓዴ መር እድገት ጋር የተስማማ የአየር ንብረት ፖሊሲ በማውጣትና በቁርጠኝነት በመተግበር በተለይም በአረንጓዴ አሻራ፣ በታዳሽ ሀይል እንዲሁም ዘላቂነት ያለው ትራንስፖርት በመዘርጋት ቀዳሚ ናት። አዲስ አበባ ያላት ምቹ የአየር ፀባይና ለአረንጓዴ ልማት ያላት ቁርጠኝነት ጉባኤውን ለማዘጋጀት ተመራጭ ስፍራ እንዳደረጋትም አትቷል፡፡

አዲስ አበባ በዓለም አቀፍ ደረጃ በኮንፈረንስ ማዕከልነት ወይም ጉባኤዎችን በማስተናገድ ተመራጭ መሆኗ ዘርፈ ብዙ ጥቅሞችን እንደሚያስገኝ የፖለቲካ ሳይንስ ምሁሩ አቶ በፍቃዱ ያስረዳሉ። አንደኛ በየጉባኤዎች ለመሳተፍ የሚመጡ እንግዶች ሀገራቸውን ወይም የሚሰሩበትን ተቋም የሚወክሉ በመሆናቸው ሲመለሱ በከተማዋ ስላዩት ነገር ለሌሎች ያጋራሉ፡፡ እንግዶች ሆቴል፣ ትራንስፖርትና ሌሎች አገልግሎቶችን ሲጠቀሙ ከሚያወጡት ወጪ ሀገሪቱ የውጭ ምንዛሪ ታገኝበታለች፡፡ የውጭ ኩባንያዎችና ባለሀብቶች በተለያዩ መስኮች መዋዕለ ንዋያቸውን ለማፍሰስ የሚስማሩበት ዕድል ይፈጠራል፡፡ የሀገር መሪዎችና የትላልቅ ተቋማት ኃላፊዎች መምጣት የዓለም አቀፍ መገናኛ ብዙሃን ትኩረት ይስባል፡፡ ይህም ኢትዮጵያ ራሷን ለመቀየር እያደረገች ያለውን ጥረት በተጨባጭ በዓይናቸው አይተው እንዲረዱ ያደርጋል፡፡

በተጨማሪም ሀገር በዓለም አቀፍ ደረጃ ያላትን ገፅታና ክብር ከፍ ያደርጋል። ኢትዮጵያ በታሪክ የአፍሪካ ህብረትን ጨምሮ የተለያዩ የዓለም አቀፍ ተቋማትን በመመስረትና ንቁ ተሳትፎ በማድረግ ስትጫወት የነበረውን ሚና፣ ስሟን የምታድስበት ሁኔታ ይፈጥራል፡፡ አሁን ደግሞ በምግብ ራስን በመቻል፣ በአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብር ከ40 ቢሊዮን በላይ ችግኝ በመትከል፣ ከአረንጓዴ ልማት ጋር የተወዳጁ ቴክኖሎጂዎችን በመተግበር ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር ኢኮኖሚ በመገንባት ላይ ትገኛለች፡፡ ይህም ኢትዮጵያ በዓለም አቀፍ ደረጃ ያላትን ተሰሚነትና ተፅዕኖ ፈጣሪነት የሚያሳድግ፣ መልካም ገፅታዋንም የሚገነባ እንደሆነ አስረድተዋል፡፡

አዲስ አበባን እንደ ስሟ ውብና አበባ፣ ለኑሮ ምቹ ከተማ ለማድረግ ሰፋፊ ስራዎች ተከናውነዋል፤ በመከናወን ላይም ይገኛሉ፡፡ እንደ እንጦጦና አንድነት ፓርኮች፣ ወዳጅነት አደባባይ፣ የብሔራዊ ቤተ መንግስት እድሳት፣ የዓድዋ ድል መታሰቢያ፣ የኮሪደርና የወንዝ ዳርቻ ልማትና ሌሎች ትላልቅ ልማቶች የከተማዋን ደረጃና ገፅታ በማሳደግ፣ ለጎብኚዎች ምቹ፣ በዓለም ተመራጭ የኮንፈረንስ ማዕከል የሆነች ከተማ እንድትሆን አዎንታዊ አስተዋፅኦ እያበረከቱ ይገኛል፡፡

# የኪነ-ጥበብ መሰናዶዎች ጥቁምታ

**በአብርሃም ገብሬ**

ባለፉት ቀናት በአዲስ አበባ የተለያዩ ኪነ ጥበባዊ ዝግጅቶች ለጥበብ አፍቃሪያን ሲደርሱ ቆይተዋል:: ዛሬን ጨምሮ በሚቀጥሉት ቀናትም መሰል ዝግጅቶች ይካሄዳሉ:: ከእነዚህ ውስጥ የመጽሐፍ ውይይት እና የሥዕል አውደ ርዕይ ይገኙበታል:: ለመረጃ ይሆንዎት ዘንድ የአዲስ ልሳን ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል የተወሰኑትን እንደሚከተለው አዘጋጅቷቸዋል::

## መጽሐፍት

አንጋፋው ምሁር ሃይሉ አርዓያ (ዶ/ር) በአንድ ጊዜ ሶስት መጽሐፎችን ለንባብ አብቅተዋል። ባሳለፍነው ሳምንት ለንባብ የበቁት እነዚህ ስራዎች፣ በሥነ ልቦና ጉዳዮች ላይ ያተኮረው "የማፍቀር ጥበብ"፣ በትውልድ ግንባታ ሂደት ውስጥ የመምህራን የላቀ አስተዋጽዎን የሚያስቃኘው "ሐዋርያው" እና በኢትዮጵያ የስነ ቃል ጥበብ ላይ የሚያተኩረው "Ethiopian Folk Poetry Recreated" ናቸው::

ሃይሉ (ዶ/ር) በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ለዓመታት የስነ-ልሳን መምህርና ተመራማሪ ሆነው ሀገራቸውን አገልግለዋል። በዩኒቨርሲቲው ቋንቋዎች ጥናት ኢንስቲትዩት መስራች ሲሆኑ፣ በደርግ ጊዜ ደግሞ "የብሔረሰቦች ጥናት ኢንስቲትዩት" ሰብሳቢም ነበሩ::

በሌላ ዜና "ፉካ" የተሰኘ የአጫጭር ልብ ወለዶች ስብስብ መጽሐፍ ለንባብ ሊበቃ ነው:: መጽሐፉ የፊታችን ረዕቡ ለንባብ እንደሚበቃ ደራሲዋ ዘቢብ መልኬ በማህበራዊ የትስስር ገጿ አሳውቃለች::

በሌላ መረጃ፣ በዛሬው እለት በኢትዮጵያ ሳይንስ አካዳሚ ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ የሥነ ጥበባት ማዕከል "የልጆች መጽሐፍት በኢትዮጵያ" በተሰኘ ርዕስ የልምድ ልውውጥና ሙያዊ ውይይት ይካሄዳል:: ሙያዊ ውይይቱ በአካዳሚው ቅጥር ግቢ ውስጥ በ 8:00 ሰዓት ይጀመራል:: የዕለቱ ተጋባዥ ደግሞ በርካታ የልጆች መጽሐፍትን ለሕትመት ያበቃው ደራሲ፣ ተርጓሚና የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የቀድሞ መምህር ዓለም እሸቱ ነው:: በዕለቱ የሥነ ጥበባት ማዕከሉ ዳይሬክተር አቶ ይታገሱ ጌትነት በኢትዮጵያ የልጆች መጽሐፍት ታሪክና ተግዳሮት ዙሪያ የመነሻ ጽሑፍ እ ን ደ ሚ ያ ቀ ር ቡ ታውቋል።




ፎቶ- ከገፀ ድር

በከተማችን ከተዘጋጁ ኪነ ጥበባዊ መሰናዶዎች በከፊል

ይህ መርሃ ግብር በኢትዮጵያ ሳይንስ አካዳሚ እና በኢትዮጵያ ቤተ መዛግብትና ቤተ መጽሐፍት አገልግሎት ትብብር በኢትዮጵያ ደራስያን ማኅበር አማካኝነት የሚሰናዳው የክረምት ወራት የሥነ ጽሑፍ ሥልጠና አንዱ አካል ነውም ተብሏል::

በሌላ መረጃ ደግሞ ነገ ነጻ ፈቃድ እና ተወሳኝነትን በሚመለከት ፍልስፍናዊ ውይይት ይደረጋል:: የውይይቱ መነሻ ሃሳብ የሚያቀርበው መልአኩ አዳል (ዶ/ር) ሲሆን፣ በውይይቱ ላይ መጥታችሁ መሳተፍ ትችላላችሁ ተብሏል:: ውይይቱ ከ8:00 ሰዓት ጀምሮ ብሔራዊ በሚገኘው በወመዘክር አዳራሽ ይቀርባል:: ውይይቱን ያሰናዳው ደግሞ ዐውደ ፋኅስ የውይይት ክበብ ነው::

## ሥዕል

የቡድን የግራፊክስ ጥበብ አውደ ርዕይ በመታየት ላይ ነው:: ባለፈው ሳምንት ረዕቡ ሐምሌ 30 ቀን 2017 ዓ.ም በይፋ በተከፈተው የጥበብ አውደ ርዕይ የተለያዩ ሰዓሊያን ስራዎች በመታየት ላይ ይገኛሉ::

በዚህ የጥበብ አውደ ርዕይ ሥራዎቻቸው ካቀረቡ ከያኒያን መካከል ታደሰ ባይሳ፣ ሚኪያስ ሰለሞን፣ ቤርሳቤህ አለማየሁ፣ ምህረት እሸቱ፣ ዳግማዊ ጸጋዬ፣ ሱራፌል መክብብ ይገኙበታል:: ዓውደ ርዕዩ እየታየ ያለው በሀያት ሪጀንሲ ሆቴል ውስጥ በሚገኘው የፈንዲቃ የባህል ማዕከል ውስጥ ሲሆን እስከ ፊታችን ነሐሴ 28 ቀን 2017 ዓ.ም ድረስ ይቆያል::

# የቁጥር ጨዋታ

## የባለፈው ሳምንት ጥያቄ መልስ

ውድ የአዲስ ልሳን ጋዜጣ አንባቢዎቻችን ባለፈው ሳምንት የቁጥር ጨዋታ አቅርበንላችሁ ነበር:: የጥያቄው ትክክለኛ አሰራርና መልስ የሚከተለውን ይመስላል:: በሦስት ማዕዘኑ አናት ላይ የተቀመጠው ቁጥር በግራ በኩል በታችኛው መስመር ላይ ከተቀመጠው ቁጥር ጋር እንደምራለን:: ደምረን ያገኘነው ውጤት በቀኝ በኩል በታችኛው ረድፍ ባለው ቁጥር እናባዛዋለን። አባዝተን ያገኘነው ውጤት ደግሞ የመሐለኛው ቁጥር መምጣት ይኖርበታል። በዚህ መሰረት የመጀመሪያ ሦስት ማዕዘንን አብረን እንስራለን:: 9 + 8 =17 ይሆናል:: ከዚያ በኋላ 17 x 1 = የመሐለኛው 17 ይሆናል።

በዚህ መሰረት የጥያቄው አሰራርና መልስ እንደሚከተለው ይሆናል:: 3 + 11 = 14 ይሆናል:: ከዚያ በኋላ ደግሞ 14 x 2 = 28 የጥያቄው ትክክለኛ መልስ ይሆናል::




## የዛሬው የቁጥር ጨዋታ

ውድ አንባቢዎቻችን ከታች በምስሉ ላይ የቁጥር ጨዋታ አቅርበንላችኋል:: በጥያቄ ምልክቱ ቦታ ላይ መግባት ያለበት ትክክለኛው ቁጥር ስንት ነው? በጥያቄው ራስዎን እየፈተኑ ይዝናኑ:: የጥያቄውን መልስ በቀጣይ ሳምንት እትማችን ይዘን እንቀርባለን::



# ቡሄን የሚያስናፍቁ ክዋኔዎች



ፎቶ- ከገፀ ድር

ቡሄን ከሚያደምቁት ክዋኔዎች መካከል የወጣቶች አልባሳትና ሙሉሙል ዳቦ ተጠቃሾች ናቸው

## በጊዜው አማረ

የነሐሴ ወር ሲጋመስ የቡሄ በዓል ትዝታ ይመጣል። ክረምቱ ጠንክሮ ዝናቡ መሬቱን በውኃ ሲያጥበው፣ ሰማዩም በጉም ሲሸፈን ከዚያ እንደገና ወደ ብራ ወቅት ሲቃረብ ቡሄ የልጅነት ትዝታን ይዞ ከተፍ ይላል፡፡

ቡሄ ብራ ነው፡፡ ሰማይ ከጭጋግ ወደ ብሩህነት የሚለወጥበት የመሸጋገሪያ ወቅት ተደርጎ ይቆጠራል፡፡ “ቡሄ ከዋለ የለም ክረምት፣ ዶሮ ከጮኸ የለም ሌሊት” የተባለውም ለዚሁ ነው፡፡ በሌላ በኩል ሙልሙል ዳቦ የሚጋገርበት ወቅት ነው፡፡ የልጆች ዜማ ደግሞ ሌላኛው ቡሄ የመድረሱ ምልክት እና አዲስ ዓመት ስለመቅረቡ አስታዋሽ ትዝታ ነው፡፡

የቡሄ በዓል፣ ከትምህርት ቤት የእረፍት ጊዜ ጋር ተገጣጥሞ የሚመጣ፣ የበርካቶች የልጅነት አሻራ የታተመበት በዓል ነው፡፡ ይህ በዓል የራሱ የሆነ የፍቅር፣ የደስታ እና የትዝታ ስሜት አለው። ልጆች በየሰፈሩ እየተሰባሰቡ ዱላ እና ድምፅ የሚያወጡ ቁርጥራጭ ብረቶችን በመያዝ “ሆያ ሆዬ” እያሉ በየቤቱ ይዞራሉ። በሚያቀርቡት ጭፈራም በቅድሚያ የቤቱን አባዎራና እማዎራ እንዲሁም የቤተሰቡን አባል ክራሞት፡-

እዚህ ቤት ያላችሁ እንደምን ናችሁ፣

በዓመት አንድ ቀን መጣንላችሁ... በማለት ይጠይቃሉ፡፡

ለቡሄ ሕፃናትና ወጣቶች፣ በቡድን በቡድን በመሆን “ቡሄ በሉ” እያሉ ከቤት ወደ ቤት እየተዘዋወሩ ይጨፍራሉ፡፡ በዘፈናቸውና በጭብጨባቸው ውስጥ የደስታ እና ተስፋ ስሜት አለ። ከልጆች ጭፈራ በተጨማሪ ሙልሙል ዳቦ ደግሞ የቡሄ በዓል ሌላኛው ድምቀት ነው። ልጆችም እንዲህ እያሉ ይጨፍራሉ፡-

ሆያ ሆዬ ሆ

መጣና በዓመቱ

ኧረ እንደምን ሰነበቱ
ሆያ ሆዬ
ሆያ ሆዬ ጌታ ጠንበለል
ዝናቡ መጣ ወዴት ልጠለል
አባብዬ ቤት እጠለላለው
ሙልሙል ዳቦዬን ይዤ እሄዳለው...፡፡

የቡሄ ጭፈራ የመዝናኛ እና የደስታ መግለጫ ከመሆን ባለፈ፣ ጥልቅ የሆነ ማህበራዊ አንድምታ አለው። ጭፈራው ሰዎች እርስ በእርስ እንዲገናኙ፣ እንዲተዋወቁ እና ያላቸውን ልዩነት ወደ ጎን በመተው አብረው እንዲደሰቱ ያደርጋል። ልጆች ከማህበረሰባቸው ጋር ያላቸው ትስስር ከፍ እንዲል ይረዳል፡፡ ይህ ደግሞ በህብረተሰቡ ውስጥ ሰላምን፣ ፍቅርን እና መተሳሰብን ያሳድጋል። ጭፈራው የትውልድን እሴት ከአዲሱ ትውልድ ጋር በማገናኘት፣ ባህላዊ እሴቶች እንዲጠበቁ ያግዛል።

ከሀበሻ ኳየር የኪነ ጥበብ ባንድ መስራቾች ውስጥ አንዱ የሆነው ቢተው ዳዊት ለቡሄ ልጆች ጅራፍ ያጮሃሉ፤ ይጨፍራሉ፡፡ ሙልሙል ዳቦ ይቀበላሉ፡፡ በታላላቆች ይመረቃሉ፡፡ ሲጨፍሩ ደግሞ በህብረትና አንድነት ነው፡፡ በአጠቃላይ ቡሄ ባህልን አጉልቶ የሚያሳይ መነጽር ነው ማለት ይቻላል ይላል፡፡

የቡሄ ዳቦ የሚሉት ሙልሙል

ጎበዝ ተሰብሰብ ቡሄ እንበል።

ሆያ ሆዬ ጉዴ... እየተባለ የሚጨፈረው በዓሉ በአንድነት፣ በአብሮነትና በመተሳሰብ የሚከበር መሆኑን ለማመላከት ነው፡፡ የጅራፍ ድምጽ፣ ህብረ ዝማሬ፣ ምርቃትና ሙልሙል ስጦታ ቡሄን የሚያስናፍቁ ክዋኔዎች ናቸው፡፡

የሆያ ሆዬ ግጥሞች ከአካባቢ አካባቢ ሊለያዩ ይችላሉ፡፡ ሆኖም ዋናው መልዕክቱ በረከት፣ ፍቅርና አንድነት ላይ ያተኩራል። የቤቱን አባዎራና እማዎራ ማወደስና ማመስገንም የጭፈራው አካል ነው፡፡

ሰዋሰው ገጸ-ድር በ2015 ዓ.ም የቡሄ በዓል ትውፊትና አከባበርን አስመልክቶ በጻፈው ጽሑፍ ላይ እንደገለጸው፣ ልጆቹ ሆያ ሆዬ በሚጨፍሩበት ወቅት ወደ ቤት የሚገቡት ሲፈቀድላቸው ብቻ ነው፡፡ ከዛም በሩ ተከፍቶ እንዲጨፍሩ ሲፈቀድላቸው የቤቱን ጌታና እመቤት በግጥምና በዜማቸው ማወደስና ማሞገሱን ይያያዙታል፡፡ የቤቱን አባወራ ከሚያወድሱባቸው ግጥሞች ውስጥ የሚከተሉትን ስንኞች መጥቀስ ይቻላል፡፡

የኔ ጌታ የሰጠኝ ሙክት

ግንባሩ ላይ አለው ምልክት

መስከረም ጠባ እሱን ሳነክት

በጌታዬ ቤት በጉልላቱ

ወርቅ ይፍሰስበት ባናት ባናቱ።

የኔማ ጌታ ጌታ ነው ጌታ

ሲቀመጥ ሲያምር ሲቆም ሲረታ።

የኔማ ጌታ የሰጠኝ ላም

አስር ዓመትዋ ኖረች በዓለም... እያሉ ያወድሳሉ፡፡ በእርግጥ የሚወደሰው አባወራው ብቻ አይደለም፡፡ እመቤቲቱም በግጥምና በዜማ ይወደሳሉ፡፡ በዘፈናቸውና በጭፈራቸውም ቤት ውስጥ ያሉትን የቤተሰብ አባላት በመልካምነታቸው ያደንቃሉ፤ ያሞግሳሉ።፡

የኔማ እመቤት መጣንልሽ

የቤት ባልትና ልናይልሽ።

የኔማ እመቤት የጋገረችው

የንብ እንጀራ አስመሰለችው።

የኔማ እመቤት ብትሰራ ዶሮ

ሽታው ይጣራል ገመገም ዞሮ...፡፡

ልጆቹ ዘፈናቸውን አጠናቅቀው ከቤት ደጃፍ ላይ ሲደርሱ፣ የቤቱ አባዎራዎችና እማዎራዎች የሚያቀርቡላቸው ሽልማቶች አሉ። ዋናው ሽልማት ሙልሙል ዳቦ ነው። አሁን አሁን ግን፣ ሙልሙል ዳቦ የመስጠቱ ባህል በተለይ በከተሞች አካባቢ ቀስ በቀስ በገንዘብ እየተተካ መምጣቱን መታዘብ ይቻላል። ብዙ ጊዜ ልጆች ዘፈናቸውን ሲያጠናቅቁ፣ የቤቱ አባወራዎች ገንዘብ ስጦታ በማበርከት ያበረታቷቸዋል።

የኪነ ጥበብ ባለሙያው ቢተው ዳዊትም ይሄን ነገር የታዘብኩት ጉዳይ ነው ይላል፡፡ ባለሙያው ገንዘብ ባህልን ሊያስጥል አይገባም፡፡ ባህልን መጠበቅ የሀገር ፍቅር አንዱ መገለጫ ነው፡፡ ባህል የሀገር ፍቅርን ያጎላል፡፡ ቱሪዝምን ያሳድጋል፡፡ ምክንያቱም ፈረንጆች የሚመጡት ልዩ የሆነውን ባህል ለማየት ነው፡፡ በመሆኑም እኛ የኪነ ጥበብ ሰዎችና ወላጆች ትክክለኛውን ባህል ለትውልዱ በማሳወቅ በኩል ብዙ ይጠበቅብናል፡፡

ይሁን እንጂ፣ በአንዳንድ አካባቢዎች በተለይ በገጠር ባህሉ አሁንም እንደቀድሞው ሙልሙል ዳቦ በማዘጋጀት ይከበራል። በከተሞች አካባቢ ትክክለኛ ባህሉን እየለቀቀ ነው የሚለው አስተያየት እንዳለ ሆኖ የቡሄ በዓል ጭፈራ ከትውልድ ትውልድ በተለያየ መልኩ እየተላለፈ ዛሬ ደርሷል፡፡ ቡሄ በመጽሐፍ፣ በስነ ቃል፣ በፊልምና በሌሎችም የጥበብ መንገዶች ተሰርቷል፡፡ ነገር ግን በኪነ ጥበብ በሚገባው ደረጃ ተገልጿል ማለት እንደማይቻል አብራርቷል፡፡

ቡሄን ጨምሮ በዓላትን ከማስተዋወቅ አንጻር የኪነ ጥበብ ባለሙያዎች መስራት ያለብንን አልሰራንም፡፡ ለዚህ ደግሞ ሁላችንም ተወቃሽ ነን፡፡ የአንድ ሀገር መገለጫ በዓልም ይሁን ባህል የህዝብ ነው፡፡ ስለዚህ የኪነ ጥበብ ባለሙያ ይህን የሀገራችንን መገለጫ ማስተዋወቅ ግዴታው ነው በማለትም ያክላል፡፡

በእርግጥ ቡሄ በሙዚቃ ስራዎች ውስጥ በተወሰነ መልኩ ተንጸባርቋል ማለት ይቻላል፡፡ ቀደም ካሉት ታዋቂ ድምጻውያን ሰለሞን ደነቀን ከወጣቶቹ ደግሞ ቃልአብ ክንፈ ይጠቀሳል፡፡ ወጣቱ ድምጻዊ ሙዚቃውን የሰራው በ2014 ዓ.ም ነው፡፡ እስኪ ሆያ ሆዬ ከተሰኘ ሙዚቃው ስንኞች ውስጥ ጥቂቶችን እንጥቀስ፡-

መጣና በዓመቱ

እንደምን ሰነበቱ

ክፈት በለው ተነሳ

ይህን አንበሳ

ክፈት በለው በሩን

የጌታዬን

ሆያ ሆዬ ሆ

ሆያ ሆዬ ሆ

እዚህ ቤቶች እንደምን ናችሁ

በዓመት አንድ ቀን መጣንላችሁ

በዓመት አንድ ጊዜ ለመጣ እንግዳ

ምሳው ሙክት ነው እራቱ ፍሪዳ

ሆያ ሆዬ ጉዴ

ጨዋታ ነው ልማዴ... በማለት ነሐሴ ወር እና ቡሄ በዓመት አንድ ጊዜ የሚመጡ፣ ተናፋቂና ተወዳጅ መሆናቸውን አቀንቅኗል፡፡

በአጠቃላይ ሆያ ሆዬ የብዙ ሰዎች ትዝታ እና የህጻናት ፌሽታ ነው፡፡ ወቅቱ ለመጻፍ፣ ለመግጠም፣ ለመዝፈን እና ለሌሎች የኪነ ጥበብ ስራዎች መነሻ ሐሳብ በመሆን ያገለግላል፡፡

# ልጆች፤ ስለ ቡሄ ጨዋታ ምን ያህል ታውቃላችሁ?

በለይላ መሀመድ

ልጆች፤ ስለ ቡሄ ጨዋታ ምን ያህል ታውቃላችሁ? አብረዋችሁ ካሉ ልጆች ጋር በጉዳዩ ዙሪያ ሀሳባችሁን ተለዋወጡ፡፡ እኛ ደግሞ ያነጋገርናቸውን እንደሚከተለው አቅርበንላችኋል፡፡



ፎቶ- ከገፀ ድር

ዱላ በመያዝ የተለያዩ ግጥሞችን በዜማ ማለት ከልጆች የቡሄ ጨዋታ መካከል የሚጠቀስ ነው

ናሆም ሰለሞን እባላለሁ፡፡ የምኖረው መነን አካባቢ ነው፡፡ ቡሄ ከሌሎች ልጆች ጋር ሰብሰብ ብለን የምናከብረው ስለሆነ እወደዋለሁ፡፡ ለበዓሉ እናቴ ሙልሙል ዳቦ በኮባ ጠቅልላ በመጋገር ለእኔም፣ ለጓደኞቼም ትሰጠናለች፡፡ ቡሄ ሲቃረብ አስቀድመን ዝግጅት እናደርጋለን፡፡ በዚህም በቡሄ ጭፈራ በተለየ የሚባሉትን ግጥሞች እናጠናቸዋለን፡፡ ለመጨፈሪያ የሚያገለግለንን ዱላ እናዘጋጃለን፡፡ በእለቱም ተሰባስበን በየቤቱ እንዞራለን። እንኳን አደረሳችሁ ወደምንልበት ቤት ገና ሳንገባ፣ መንገድ ስንቀሳቀስ፤ እንዲሁም ከአንዱ ቤት ወደሌላው ቤት ስንጓዝ የቡሄ ጨዋታን ግጥም እያልን ነው፡፡

ልጆችዬ ለቡሄ ጭፈራ ከሚባሉት የግጥም ስንኞች መካከል የተወሰኑትን እናካፍላችሁ፤

ቡሄ በሉ፣

ልጆች ሁሉ

ቡሄ መጣ፤

ያ መላጣ

ቅቤ ቀቡት፣ እንዳይነጣ

እነዚህን ከላይ ያሉ የግጥም ስንኞች በዜማ እያሉ ልጆች ከአንዱ ቤት ወደ ሌላኛው ይጓዛሉ፡፡ ከዚያ "እንኳን አደረሳችሁ" ወደሚሉበት ቤት ከደረሱ በኋላ ደግሞ የሚከተለውን ግጥም በዜማ ይጫወታሉ፤

መጣና በዓመቱ፤

ኧረ እንደምን ሰነበቱ፡፡

እዚህ ቤቶች እንደምን ናችሁ፤

በዓመት አንድ ቀን መጣንላችሁ፤

በዓመት አንድ ቀን የመጣ እንግዳ

እራቱ ሙክት፣ ምሳው ፍሪዳ

እነዚህን ግጥሞች በዜማ እያሉና እያሞገሱ ከጨፈሩ በኋላ፤ ብዙ ሰዎች የብር ስጦታ ይሰጧቸዋል፡፡ አንዳንድ ሰዎች ደግሞ ሙልሙል ዳቦ ይሰጧቸዋል። የሚሰጧቸውን ብር ወይንም ሙልሙል ዳቦ ተቀብለው በግጥም እና በዜማ አመስግነው ወደሌላኛው ቤት ይጓዛሉ። ለሽልማት ወይም ለስጦታው የምስጋና ዜማ የሚከተሉትን ዓይነት ግጥሞች ይይዛል፡፡

ዓመት አውደ ዓመት

ያባብዬን ቤት

ወርቅ ይዝነብበት

እዚህ ቤት

ይግባ በረከት፡፡...

ልጆችዬ ከላይ የተገለፀውን ዓይነት የቡሄ ጨዋታ ግጥሞችን ናሆም ከጓደኞቹ ጋር በየዓመቱ ሲጫወት እንደነበር ነግሮናል። ለዘንድሮም ጥሩ ዝግጅት እያደረገ መሆኑን ገልፆልናል። ህጻን ናሆም በዓሉ ላይ ካከናወኑት ጭፈራ በኋላ ስለሚያደርጉት ተግባር፤ "የሚሰጡንን ሙልሙል ዳቦ ተከፋፍለን እንበላለን፤ የሰበሰብነውን ገንዘብ እኩል በመከፋፈል ለትምህርት የሚያስፈልጉ ቁሳቁስ ለመግዛት እናስቀምጠዋለን" በማለት ገልፆልናል፡፡

ሌላኛው ስለቡሄ ጨዋታ አስተያየት የሰጠን ህፃን ሳሙኤል ተክሉ ነው። የቡሄን በዓል ጨዋታ በልዩ ሁኔታ እንደሚያከብረውና እንደሚወደው ይናገራል፡፡ ህጻን ሳሙኤል የቡሄ ጨዋታ አስመልክቶ ያለውን ልምድ የገለጸው፤ "ከሳምንት በፊት አባቴ ጅራፍ ይሰራልኛል፡፡ የቡሄ እለት ከሰፈር ጓደኞቼ ጋር በመሆን ጅራፉን ሳስጮህ አረፍዳለሁ፡፡ በኋላም ከጓደኞቼ ጋር በየቤቱ በመዞር ለበዓሉ የሚባሉትን ግጥሞች በማለት እንኳን አደረሳችሁ እላለሁ፡፡ በዓሉን ከጓደኞቼ ጋራ ሆኜ ማክበሬ ደስታን ይፈጥርልኛል፡፡ ወላጅ እናቴም ሙልሙል ዳቦ በመጋገር አብረው ለሚጨፍሩ፣ እንዲሁም በተለያየ ሰዓት ቤታችን እየጨፈሩ ለሚመጡት ልጆች ትሰጣለች፡፡ ዘንድሮም የቡሄ ጨዋታን ለመጫወት ከጓደኞቼ ጋር እየተዘጋጀሁ ነው" በማለት ነው፡፡

በባህርዳር ዩኒቨርሲቲ የፎክሎር ምሁር የሆኑት አስቴር ሙሉ (ዶ/ር) ባስተላለፉበት መልዕክት፣ "ልጆች፤ ባህሉን ያልጠበቁ ግጥሞችን መግጠምና ማዜም የለባችሁም፡፡ የገንዘብ ማግኛ እንዳይሆን ጥንቃቄ ማድረግ ይጠበቅባችኋል" ብለዋል፡፡ እንኳን ለቡሄ በዓል አደረሳችሁ ሲሉም ለእናንተ ለልጆች መልካም ምኞታቸውን ገልጸዋል።

## 5 ልዩነቶችን ፈልጉ



## እንቆቅልሽ

### ያለፈው ሳምንት ጥያቄ

**የሰጡትን የሚበላ፤ ሲያጠጡት የሚጠፋ**

**መልስ፡-** ለ. እሳት

### የዚህ ሳምንት ጥያቄ

**ሊሰርቅ ሲመጣ በስውር ፤ ሰርቆ ሲወጣ በግርግር**

ሀ. ሌባ

ለ. ሰርግ

ሐ. ሞት

**ልጆች መልስ ይሆናል የምትሉትን በዌብ ሳይታችን አድርሱን፤ እኛም በተደጋጋሚ የመለሰውን እንሸልማለን፤ ስለዚህ ተሳተፉ፤ ተሸለሙ፡፡**

# የጂኦስፓሺያል መረጃ በአረንጓዴ ዐሻራ

- ለአረንጓዴ ዐሻራ የጂኦስፓሺያል መረጃን የማከናወን ሥራው በየዓመቱ ዕድገት እያሳየ ነው




ፎቶ- ከገፀ ድር

በቅርቡ የተካሄደው የአንድ ጀንበር የችግኝ ተከላውን የሚያሳየው የጂኦስፓሺያል መረጃ

**በደረጀ ታደሰ**

በጎርጎሮሳውያን የዘመን አቆጣጠር 1675 አካባቢ እንደተመሰረተች ይነገርላታል፤ የኮሎምቢያዋ ከተማ ሜደሊን፡፡ ከቦጎታ በመቀጠል በስፋቷ ሁለተኛዋ ትልቋ ከተማ ነች፡፡ በጎርጎሮሳውያን የዘመን አቆጣጠር ከ1980 እስከ 1990ዎቹ ድረስ ያሉት ዓመታት ለከተማዋ ዕድገት በወርቃማነታቸው የሚዘከሩ ናቸው፡፡ ለከተማነት ዕድገቷ ዘመናዊ የቴክኖሎጂ ፈጠራዎችን በቁልፍ ግብዓትነት በመጠቀምም ትታወቃለች። በዚህ ተግባሯም በጎርጎሮሳውያን የዘመን አቆጣጠር በ2023 በወል ስትሪት ጆርናል እና በአርባን ላንድ ኢንስቲትዩት የዓመቱ ምርጥ የኢኖቬሽን ከተማ ተብላ ለመመረጥ ችላለች፡፡ ይህ ያልተቋረጠ ዕድገት እና መስፋፋት የኋላ ኋላ በከተማዋና በነዋሪዎቿ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ወደ መፍጠር ተሸጋግሯል፡፡ ከተማዋ ከጊዜ ወደ ጊዜ በአየር ሙቀት እና በአካባቢ ብክለት የሚደርስባት ፈተና እየበዛ መጣ፡፡

ከተማዋ የተጋረጠባትን ፈተና የተመለከቱት የኮሎምቢያ መንግስት እና የከተማዋ አስተዳደር በቸልታ ማየት አልፈለጉም፡፡ በጥናት ላይ የተመሰረተ መፍትሔ ወደማፈላለግ ገቡ፡፡ "የአረንጓዴ ኮሪደር" ልማት ፕሮጀክትን ይፋ አደረጉ። "How Medellin Solved Heat Problem with Tree-Planting" በሚል ርዕስ ተሰናድቶ፣ በጎርጎሮሳዊያን የዘመን ቀመር በወርሃ ነሐሴ 2025 በኮሎምቢያ ዋን ዶት ኮም ገፀ ድር ላይ ለንባብ የበቃው ጥናታዊ ፅሁፍ እንደሚያመላክተው፤ በሜደሊን ከተማ ተግባራዊ የተደረገው "የአረንጓዴ ኮሪደር" ልማት ፕሮጀክት ዓላማ የከተማዋን ማስተር ፕላን ባገናዘበ መልኩ የአረንጓዴ ዕጽዋት ሽፋንን ማሳደግ ነው፡፡ በጎርጎሮሳውያን የዘመን አቆጣጠር ከ2019 ጀምሮ የተተገበረው ፕሮጀክቱ፤ የከተማዋን ዋና ዋና የመንገድ ዳርቻዎችና አካፋዮች፣ አደባባዮች፣ ፓርኮች፣ የወንዝ ዳርቻዎች፣ ተራራና ኮረብታዎች እንዲሁም አዳዲስ ሥፍራዎችን ያካተቱ 30 ቦታዎችን አካልሏል፡፡ 70 ሄክታር መሬት እና 20 ኪሎ ሜትር የሚረዝም መንገድን በዕፅዋት ልማት ለመሸፈን ተሰርቷል፡፡ እ.ኤ.አ. በ2021 ብቻ ከተማዋ በነበራት የደን ሀብት ላይ 2 ነጥብ 5 ሚሊዮን የተለያዩ ዝርያ ያላቸው ዕፅዋት እና ከ880 ሺህ በላይ ዛፎች ተተክለዋል፡፡

በተጨማሪም፤ በየዓመቱ ያለማቋረጥ እየተተገበረ ላለው ፕሮጀክት ከተማዋ ከ16 ነጥብ 3 ሚሊዮን ዶላር በላይ ገንዘብ ወጪ አድርጋለች፡፡ ሥራው ከተማዋ ለነዋሪዎቿ የተመቸች እንድትሆን እያደረጋት እንደሚገኝ በመረጃው ተጠቅሷል፡፡

አዲስ አበባ ከተማም የሜደሊንን ዓይነት ስኬት ለማስመዝገብ በሚያስችላት ጉዞ ላይ እንደምትገኝ በቅርብ ዓመታት እየተሠሩ ያሉ ለአረንጓዴ ልማት መስኩ ትኩረት የሰጡ ተግባራት ማሳያዎች ናቸው፡፡ ሥራዎቹም ዘላቂ ውጤት እንዲያመጡ በጥናትና ምርምር ስለመደገፋቸው ከአረንጓዴ ዐሻራ መርሃ ግብር ጋር በተያያዘ የኢትዮጵያ ስፔስ ሣይንስ እና ጂኦስፓሽያል ኢንስቲትዩት እየተወጣ ያለው ተቋማዊ ኃላፊነት መጥቀስ በቂ ነው፡፡

የአረንጓዴ ዐሻራ መርሃ ግብር ውጤታማ እንዲሆን የተለያዩ ተቋማት በመቀናጀት ተግባሩን የመምራት እና የማስተባበር ኃላፊነትን ይወጣሉ። ከእነዚህ ተቋማት መካከል አንዱ፤ ስፔስ ሣይንስ እና ጂኦስፓሽያል ኢንስቲትዩት ነው፡፡ ይህ ተቋም በዋናነት ጥራት ያላቸው መረጃዎች ጥቅም ላይ እንዲውሉ ያግዛል።፡ ከችግኝ ማፍላት ጀምሮ፣ የተከላ፣ የፅድቀት እና የደን ሽፋን ደረጃውን በትክክል የሚያመላክቱ መረጃዎችን በመሰብሰብ፣ በማደራጀት እና በመተንተን ውጤቱን ለሚመለከታቸው አካላት ያሰራጫል፤ ገለፃ ያደርጋል፡፡

አቶ ቴዎድሮስ ካሳሁን፤ የኢትዮጵያ ስፔስ ሣይንስ እና ጂኦስፓሽያል ኢንስቲትዩት የካርታ ሥራ ክፍል መሪ ሥራ አስፈፃሚ ናቸው፡፡ ኢንስቲትዩቱ የአረንጓዴ ዐሻራ መርሃ ግብርን መሰረት አድርጎ የሠራቸውን ተግባራት በተመለከተ ሲያብራሩ፤ በያዝነው የ2017 ዓ.ም. እየተከናወነ ካለው የአረንጓዴ ዐሻራ መርሃ ግብር ጋር በተያያዘ ኢንስቲትዩቱ ወሳኝ ሥራዎችን በሀገር አቀፍ ደረጃ ከተቋቋመው የስትሪንግ ኮሚቴ ጋር በመቀናጀት ሰርቷል፡፡ ከእነዚህም መካከል፤ በሀገር አቀፍ ደረጃ ለተለዩ 13 ሺህ 84 የተከላ ቦታዎች ካርታ ተዘጋጅቷል፡፡ ካርታ የተዘጋጀላቸው የመትከያ ቦታዎች አጠቃላይ ስፋት 294 ሺህ ሄክታር የሚሸፍን ሲሆን፤ መሬት ላይ በቦታው በአካል በመገኘት ተለክቶ በተወሰደ መረጃ ላይ ተመስርቶ የተከናወነ ነው፡፡ እያንዳንዱ የመትከያ ቦታ፤ የሚገኝበት ክልል፣ ወረዳ፣ ቀበሌ፣ የመትከያ ቦታው (ሳይት) እንዲሁም የቦታው መገኛ ማዕከላዊ ነጥብ (Center Point) በዝርዝር በካርታዎቹ ተመላክቷል፡፡

ለ2017 ዓ.ም. የአረንጓዴ ዐሻራ መርሃ ግብር የችግኝ ተከላ እንዲከናወንባቸው በሀገር አቀፍ ደረጃ ከተለዩ እና ካርታ ከተዘጋጀላቸው 13 ሺህ 84 ቦታዎች መካከል፤ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሚገኙት ብዛት በቁጥር 277 (ሁለት መቶ ሰባ ሰባት) ሲሆን፤ ስፋታቸውም 348 ሄክታር ይሸፍናል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ፤ በኦሮሚያ ክልል የመሬት ሽፋናቸው 212 ሺህ 560 ሄክታር የሆኑ 6 ሺህ 595 የመትከያ ቦታዎች እንዲሁም በአማራ ክልል ሽፋናቸው 57 ሺህ 497 ሄክታር የሆኑ 4 ሺህ 50 የመትከያ ቦታዎች ካርታ ተዘጋጅቷል ብለዋል፡፡

ለአረንጓዴ ዐሻራ መርሃ ግብር የሚሆን የጂኦስፓሺያል መረጃዎችን የማሰባሰብ እና የማጠናቀር ሥራ በቋሚነት መከናወን የጀመረው በ2015 ዓ.ም. እንደሆነ ያስታወሱት አቶ ቴዎድሮስ፤ ሥራው በየዓመቱ ዕድገት አሳይቷል፡፡ ባለፈው የ2016 ዓ.ም. 8 ሺህ የሚሆኑ የመትከያ ቦታዎች ካርታ ተዘጋጅቶላቸዋል። ለዘንድሮው የአረንጓዴ ዐሻራ መርሃ ግብር የተዘጋጁ የተከላ ቦታዎች ካርታ ከአምና አንፃር ብልጫ አለው፡፡ ለዚህ ደግሞ በየደረጃው ያሉ አመራሮች እና ባለሙያዎች የአረንጓዴ ልማት ሥራቸውን በተጨባጭ መረጃ ላይ ተመስርቶ ለማከናወን ያላቸው ተነሳሽነት እና የመፈፀም ብቃት ከጊዜ ወደ ጊዜ መሻሻል ማሳየቱ ትልቅ እገዛ ማድረጉን ጠቅሰዋል፡፡

አቶ ቴዎድሮስ አክለው እንዳስረዱት፤ የመትከያ ቦታዎችን ካርታ ማዘጋጀትን ጨምሮ፤ ከችግኝ ማፍላት ጀምሮ፣ የተከላ፣ የፅድቀት እና የደን ሽፋን ደረጃውን በትክክል የሚያመላክቱ መረጃዎችን በመሰብሰብ፣ በማደራጀት እና በመተንተን ውጤቱን ለሚመለከታቸው አካላት የማሰራጨት ኃላፊነትን በአግባቡ ለመወጣት እንዲቻል የስፔስ ሣይንስ እና ጂኦስፓሽያል ኢንስቲትዩት የተለያዩ ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎችንና መተግበሪያዎችን (ሶፍትዌሮችን) ይጠቀማል፡፡ ከእነዚህ ውስጥ የሳተላይት ምስሎችን የሚሰጡ የሳተላይት እና የጂፒኤስ (GPS) ቴክኖሎጂዎች እንዲሁም ኪውጂአይኤስ (QGIS) የመሳሰሉ የመረጃ መተንተኛ ሶፍትዌሮች ይጠቀሳሉ፡፡

"ሥራ ያለምክንያት አይፈጠርም። እንደ ሀገር መጠኑ ይለያይ እንጂ፤ የአረንጓዴ ልማት ሥራ የማከናወን ልምድ አለ፡፡ ይህ ልምድ በኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) አነሳሽነት በተጀመረው የአረንጓዴ ዐሻራ መርሃ ግብር በስፋት መከናወን ከተጀመረ ዓመታት ተቆጥረዋል፡፡ ልማቱ ውጤታማ እንዲሆን ሥራዎች በመረጃ ላይ ተመስርተው መከናወን አለባቸው" ሲሉ የኢትዮጵያ ስፔስ ሣይንስ እና ጂኦስፓሽያል ኢንስቲትዩት የካርታ ሥራ ክፍል መሪ እና ሥራ አስፈፃሚ አቶ ቴዎድሮስ ካሳሁን ተናግረዋል፡፡

ዘመናዊ ቴክኖሎጂንና አሠራሮችን ተጠቅሞ እየተተገበረ ያለው መረጃዎችን የማጠናቀር ተግባር ለአረንጓዴ ልማት ያለውን አስተዋፅኦ ከቀደመው ተለምዷዊ አሠራር ጋር አነጻጽረው ሲያብራሩም፤ ከዚህ ቀደም የችግኝ ተከላ፣ ፅድቀት እና የመሳሰሉ ሥራዎች ውጤታማነታቸው የሚለካው ከታች ወደላይ በሚመጡ ሪፖርቶች እና መረጃዎች ነበር፡፡ ይህ ደግሞ ያልተተከለው እንደተተከለ፣ ያልፀደቀው እንደፀደቀ ተደርጎ እንዲወሰድ እና የመረጃ መፋለስ እንዲፈጠር ያደርጋል። ከዚህ አንፃር የስፔስ ሣይንስ እና የጂኦስፓሺያል ኢንስቲትዩት ከአረንጓዴ ዐሻራ ጋር የተያያዙ መረጃዎችን በጥራት እና በፍጥነት እንዲሰበስቡ፣ እንዲተነተኑና እንዲሰራጩ ከማድረግ አንፃር እየሠራ ያለው ሥራ ቀደም ሲል ይታይ የነበረውን ክፍተት የሸፈነ ነው፡፡ በሀገሪቷ ሁሉም አካባቢዎች፤ በተለይም ካርታ በተዘጋጀላቸው እያንዳንዱ የችግኝ መትከያ ቦታ ላይ ስለሚከናወኑ እና ስለተከናወኑ የአረንጓዴ ልማት ሥራዎች ውጤታማነት (የተተከለ ችግኝ፣ የፅድቀት መጠን፣ ሽፋኑን..) የሚያሳዩ መረጃዎችን በቀላሉ ማግኘት ተችሏል፡፡ ከአረንጓዴ ልማት ጋር የተያያዙ መረጃዎችን ለውሳኔ ሰጪ እና ክትትልና ድጋፍ ለሚያደርጉ አካላት፣ ለጥናትና ምርምር ተቋማትና ባለሙያዎች... ጥራት ያለው መረጃ እንዲደራጅ አቅም ፈጥሯል፡፡ ውጤታማ ተሞክሮን ለማስፋት እንዲሁም ተጠያቂነትን ለማስፈን ተጨባጭ ማስረጃ ማደራጀት ተችሏል፡፡ የአረንጓዴ ልማት አንድ ውጤት ከሆነው የካርበን ሽያጭ ተጠቃሚ ለመሆን የሚያስችለውን የተደራጀ መረጃ ዓለም አቀፍ ስታንዳርዱን በጠበቀ መልኩ ለማዘጋጀት እና ለማቅረብ ወሳኙ ተግባር እንዲከናወን አግዟል፡፡

ከ2011 ዓ.ም. ጀምሮ ያለማቋረጥ እየተተገበረ ያለው የአረንጓዴ ዐሻራ መርሃ ግብር ተጨባጭ ውጤት እያመጣ ይገኛል፡፡ የሀገሪቱን የደን ሽፋንም ዕድገት አሳይቷል፡፡ ይህንን አስመልክቶ የተሠራ ጥናትን ዋቢ በማድረግ የግብርና ሚኒስቴር ባሰራጨው መረጃ፤ መርሃ ግብሩ ከመጀመሩ በፊት የነበረውን 17 ነጥብ 2 በመቶ የደን ሽፋን ወደ 23 ነጥብ 6 በመቶ ማደጉን አመላክቷል፡፡ ለዚህ ደግሞ አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደርን ጨምሮ በመላው ኢትዮጵያ፤ በቢሊዮን የሚቆጠሩ ችግኞችን በየዓመቱ የመትከሉ ተግባር ባህል ወደመሆን ያሸጋገረው የአረንጓዴ ዐሻራ መርሃ ግብር ትልቁን ድርሻ ይወስዳል፡፡ በዘንድሮው ዓመትም ይሄው ሀገር አቀፍ መርሃ ግብር በታላቅ መነሳሳት እና በከፍተኛ ሕዝባዊ ተሳትፎ መከናወኑን ቀጥሏል፡፡

ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መንገዶች ባለስልጣን ጋር በመተባበር ዘወትር ቅዳሜ በየአስራ አምስት ቀኑ የሚቀርብ

# ለወገን ደራሽነት በተግባር ሲገለጥ

## “በቀድሞው ቤቴ ያሳለፍኩትን ህይወት ሳስታውሰው የአሁኑን ዳግም እንደተወለድኩ ነው የምቆጥረው”

የቤት ዕድሳት ተጠቃሚ የሆኑት ወይዘሮ እናኑ መሸሻ

**በላዋይሽ ቢተው**

የአዲስ አበባ ከተማ መንገዶች ባለስልጣን የመንገድ መሰረተ ልማትን ዘመናዊ፣ ምቹ እና ሁለን አቀፍ በሆነ መንገድ በጥራት በመገንባት መዲናዋን ለነዋሪዎቿ ምቹ እና ከሌሎች ሀገራት ከተሞች ጋር ተወዳዳሪ ለማድረግ 24/7 (ሰባቱንም ቀን ሃያ አራት ሰዓት) እየሰራ ነው፡፡ ከዚህ ጎን ለጎን ማህበራዊ ኃላፊነቱን ለመወጣት በተለያዩ በጎ ፍቃድ ስራዎች ላይ እየተሳተፈ ይገኛል። ከነዚህም መካከል የአቅመ ደካሞች ቤት እድሳት እና ግንባታ በዋነኝነት ይጠቀሳል፡፡ ባለፉት ዓመታት በርካታ ቤቶችን በመገንባት ለአቅመ ደካሞች አስረክቧል፡፡ በተጠናቀቀው 2017 በጀት ዓመት በቂርቆስ ክፍለ ከተማ ገንብቶ ያስረከባቸውን ቤቶች ለአብነት መጥቀስ ይቻላል፡፡



ፎቶ- ከመንገዶች ባለስልጣን

ከተጎሳቆለ ቤት ወጥተው በታደሰ ቤት መኖር የጀመሩት ወይዘሮ እናኑ መሸሻ

በቤት እድሳት ተጠቃሚ ከሆኑት መካከል ወይዘሮ እናኑ መሸሻ አንዷ ናቸው፡፡ በክፍለ ከተማው ወረዳ 05 ቡልጋርያ ሰፈር ነዋሪ ናቸው፡፡ ቤታቸው ለረጅም ጊዜ ምንም እድሳት ሳይደረግለት በመቆየቱ የአፈር ቤታቸው ምርጉ ከግማሽ በታች ፈራርሷል። የቀረውም ቢሆን ምንም መከላከል የማይችል ነበር። ሆኖም ወይዘሮ እናኑ ከአንድ ልጃቸው ጋር በቤቱ ከመኖር ውጭ አማራጭ አልነበራቸውም፡፡ በበጋ ወቅት ብርድ እና ንፋስ ያስቸግራቸዋል። የክረምቱ ደግሞ ከዚህም ይከፋል። ጭንቀቱ የእሳቸው ብቻ ሳይሆን አብረዋቸው የሚኖሩ ጎረቤቶቻቸውም ጭምር ነው። ዝናብ ጠብ ሲል “እንዴት ሆነው ይሆን” ብለው በስራ ላይ ሆነው እንኳን እንደሚያስቧቸው እና ደውለው እንደሚጠይቋቸው ጎረቤቶቻቸው ይናገራሉ፡፡ ዝናብ በበረታ ጊዜ ቤታቸው በጎርፍ ውሃ ይሞላል፡፡ ያኔ ደርሰዉ ውሃውን ከቤት እየቀዱ ወደ ውጭ በመድፋትም ያግዟቸዋል፡፡

ህይወታቸውን በፈለጉት መልክ ለማስተካከል ያቃታቸው እናት ፈጣሪ እጁን እንዲዘረጋላቸው ከማልቀስ እና ከመማፀን በቀር ማድረግ የሚችሉት ነገር አልነበረም፡፡ “ቤቴ ከመፀዳጃ ቤት ጋር ተያይዞ የተሰራ በመሆኑ ሽታው በተደጋጋሚ ለበሽታ አጋልጦኛል። ታምሜ ተኝቼ እንኳን ሰዎች ቤቴ መጥተው ለመቀመጥ አይፈልጉም፤ በቁማቸው ጠይቀውኝ ይመለሳሉ” ይላሉ ወይዘሮ እናኑ ያለፈውን ጊዜ በማስታወስ።፡

በቃ ሲል ይበቃል! ይባል አይደል፡፡ የወይዘሮ እናኑ ለቅሶ ሰሚ አገኘ፡፡ የአዲስ አበባ ከተማ መንገዶች ባለስልጣን ማልቀስ ይብቃዎት! ብሎ የልባቸውን መሻት ሊፈጽም በራቸውን አንኳኳ፤ በግማሽ የፈረሰ ቤታቸውን ሙሉ በሙሉ አፍርሶ፣ ለወይዘሮ እናኑ ብቻ ሳይሆን አብረዋቸው ለሚዋሰኑት ሶስት ጎረቤታቸውም ጭምር በዘመናዊ መልክ ቤት ገንብቶ አጠናቀቀ፡፡

እነዚህን ገንብቶ ያጠናቀቃቸው ቤቶች ምርቃት እና የቁልፍ ርክክብ ስነ ስርዓት በሀምሌ1 ቀን 2017 ዓ.ም ተከናውኗል፡፡ በስነ ስርዓቱ ላይ የባለስልጣኑ የኮርፖሬት ሰርቪስ ዘርፍ ምክትል ዋና ዳይሬክተር አቶ ጀማል ዶሌቦ፣ የቂርቆስ ክፍለ ከተማ ዋና ስራ አስፈፃሚ ምስክር ነጋሽ (ዶ/ር)፣ የቂርቆስ ክፍለ ከተማ የብልፅግና ፓርቲ ጽ/ቤት ኃላፊ አቶ አደፍርስ ኮራ፣ የባለስልጣኑ እና የክፍለ ከተማው አመራሮች እና የአካባቢው ነዋሪዎች ተገኝተዋል፡፡

ምክትል ዋና ዳይሬክተር አቶ ጀማል ዶሌቦ በምርቃቱ ወቅት ባደረጉት ንግግር፣ “ባለስልጣኑ ማህበራዊ ኃላፊነቱን ለመወጣት ሰው ተኮር ስራዎችን ይሰራል። ለአቅመ ደካሞች መአድ ማጋራትን፤ ለ50 ልጆች ቋሚ ድጋፍ ማድረግ፤ በአበይት በዓላት ላይ ዝቅተኛ ደሞዝ ላላቸው ሰራተኞች በዓልን ተደስተው እንዲያሳልፉ የተለያየ ድጋፍ መስጠት እና የአቅመ ደካሞችን ቤት እድሳት እና ግንባታ በእቅድ ያከናውናል። በቀጣይ ይህን ስራውን ሰፋ ባለመልኩ አጠናክሮ ይቀጥላል፡፡ በዚህ ስራ የተሳተፉ እና የገንዘብ ድጋፍ ያደረጉ ተቋራጮች እና አማካሪ ድርጅቶች ልትመሰገኑ ይገባል” ብለዋል፡፡

የቂርቆስ ክፍለ ከተማ ዋና ስራ አስፈፃሚ ምስክር ነጋሽ (ዶ/ር) በበኩላቸው፣ “የቤት እድሳት እድሉን ያገኛችሁ የቤት ባለቤቶች እንኳን ደስ አላችሁ፡፡” በማለት ክፍለ ከተማው ሰው ተኮር የሆኑ እና የህብረተሰቡን አኗኗር የሚያሻሽሉ ስራዎችን አጠናክሮ እንደሚቀጥል ተናግረዋል፡፡

የቤት ርክክብ ስነ ስርዓቱ ላይ ደስታቸውን መግለፅ የተሳናቸው ወይዘሮ እናኑ አይኖቻቸው ሲያነቡ ታይተዋል፡፡ የዛሬው እንባ ከዚህ ቀደሙ ይለያል፡፡ ዛሬ ከአይናቸው የሚፈልቀው የደስታ እንባ ነው፡፡ ትናንት የነበሩበትን አስታውሰው የዛሬውን ቤታቸውን ሲመለከቱት ልዩነቱ አራምባ እና ቆቦ የሆነባቸው ወይዘሮ እናኑ “በቀድሞው ቤቴ ያሳለፍኩትን ሳስታውሰው ዳግም እንደተወለድኩ ነው የምቆጥረው” ብለዋል፡፡

በእድሉ ተጠቃሚ የሆኑት ሌላኛዋ የቤት ባለቤት ወይዘሮ ይደመሙ ታደሰ ይባላሉ፡፡ ወይዘሮ ይደመሙ በመንገድ ፅዳት ስራ ተሰማርተው ቤተሰባቸውን የሚያስተዳድሩ የአንድ ልጅ እናት ናቸው። “እዚህ ቤት የገባሁት ልጄ በሽተኛ ስለነበር መንግስት ሰጥቶኝ ነው።” ሲሉ በ2011 ዓ.ም ስለተሰጣቸው ቤት የሚያስታውሱት ወይዘሮ ይደመሙ፣ “አሁን እድለኞች ነን፤ ልጄም ታክሞ ድኖ ትምህርቱን እየተከታተለ ይገኛል» ብለዋል፡፡

ወይዘሮ ይደመሙ የቤታቸውን ቁልፍ ሲረከቡ፣ “ከጭቃ ቤት ወደ ብሎኬት ቤት በመግባቴ ተደስቻለሁ” የሚሉት ወይዘሮዋ፣ የቤት እድሳት ላከናወነላቸው የአዲስ አበባ ከተማ መንገዶች ባለስልጣን ላቅ ያለ ምስጋናቸውን አቅርበዋል፡፡ በተጨማሪም በዚህ ስራ ለተሳተፉ እና ላስተባበሩ የክፍለ ከተማ እና የቀጠና ኃላፊዎችን አመስግነዋል፡፡ የ 14 ዓመት ልጃቸው ዳንኤል ንጉሴም ቤታቸው በዚህ መልኩ ተሰርቶ በማየቱ መደሰቱን ገልጿል፡፡

እድሳት የተከናወነለት ሦስተኛው ቤት ባለቤት የ94 አመቱ አዛውንት አቶ ትርፌ ተግባሩ ናቸው፡፡ አቶ ትርፌ ተግባሩ በወረዳው ማህበራዊ ፍርድ ቤት ዳኛ ሆነው እርጅና ሳይበግራቸው ሀገራቸውን በማገልገል ላይ ይገኛሉ፡፡ ቤታቸው እድሳት እስኪደረግለት ድረስ ከልጆቻቸው እና የልጅ ልጆቻቸው ጋር ለረጅም ዓመታት በዚሁ ቤት ኖረዋል፡፡ በቁልፍ ርክክብ ስነ ስርዓቱ ላይ ቤታቸው በአዲስ መልክ በብሎኬት ተሰርቶ፣ አምሮበት እና በአስተማማኝ መልኩ ተገንብቶ፤ አሁን ላይ ያለውን ገፅታ ሲመለከቱ የተደሰቱት አዛውንቱ “ዛሬ ብሞት አይቆጨኝም፡፡ እንኳን በእውኔ በህልሜም ይህን አያለው ብዬ አስቤ አላውቅም” ሲሉ ተደምጠዋል፡፡

ባለስልጣኑ የገነባቸው አራቱ መኖርያ ቤቶች እያንዳንዳቸው ሶስት ክፍል ሲኖራቸው ዘመናዊ መፀዳጃ ቤትም አለው፡፡ ቤቶቹ ከመሬት ከፍ ተደርገው በመገንባታቸው ከእንግዲህ ዶፍ ሲዘንብ ውሎ ሲዘንብ ቢያድር ጎርፍ ቤቴ ይገባ ይሆን ብለው ወይዘሮ እናኑ እና ጎረቤቶቻቸው አያስቡም፡፡ በተጨማሪም በዘመናዊ መልክ የተሰራው መፀዳጃ ቤት አካባቢውን ከመጥፎ ሽታ ነፃ አውጥቶታል፡፡

በርክክቡ ላይ የተገኙት የአካባቢው ነዋሪ እና የቀጠናው ኮሚቴ አቶ ደጀኔ ቶልቻ፣ ባለስልጣኑ የሰራውን ስራ በማድነቅ “ማህበራዊ ኃላፊነቱን ለመወጣት ያከናወነው ተግባር ለሌሎች አርአያ የሚሆን ነው” በማለት ሌሎች ባለሀብቶች፣ መንግስታዊ እና የግል ተቋማት እንዲሁ ማህበራዊ ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል፡፡

የአዲስ አባባ ከተማ መንገዶች ባለስልጣን በ2017 በቂርቆስ ክፍለ ከተማ ከአደሳቸው አራት ቤቶች በተጨማሪ በለሚ ኩራ ክፍለ ከተማ ቦሌ አራብሳ ሳይት 5 አንድ ቤት፣ አዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ አማኑኤል አካባቢ አንድ እንዲሁም ልደታ ክፍለ ከተማ ወረዳ 09 አምስተኛ አካባቢ ሁለት ቤቶችን ገንብቶ በማጠናቀቅ ለባለቤቶቹ አስረክቧል፡፡

ባለስልጣኑ አብረውት የሚሰሩትን ተቋራጮች እና አማካሪ ድርጅቶችን በማስተባበር በበጀት ዓመቱ ለሰራቸው 8 ቤቶች 7 ሚሊዮን ብር ወጪ አድርጎል። የቤቶችን ዲዛይን በማውጣት እና ሂደቱን በመከታተል ግንባታው እንዲጠናቀቅ አድርጓል፡፡ የባለስልጣኑን ዓላማ በመረዳት አጋርነታቸውን ካሳዩ መካከል ይርጋለም ኮንስትራክሽን፣ ድሪባ ደፈርሻ ኮንስትራክሽን፣ ሜልኮም ኮንስትራክሽን፣ ሶፍ ኡመር ኮንስትራክሽን እና ጥላሁን ኮንስትራክሽን ይገኙበታል፡፡

ሁሌም በጎ ፈቃድ ሥራዎችን በማከናወን የሚታወቀው የአዲስ አበባ ከተማ መንገዶች ባለሰልጣን በ2018 በጀት ዓመት ለ30 አቅመ ደካሞች ቤቶችን ለማደስ በእቅድ የያዘ ሲሆን ከቤት እድሳት በተጨማሪ ሌሎች የበጎ ፍቃድ ስራዎችንም አጠናክሮ ይቀጥላል፡፡

ኢኮኖሚ

# ዘመናዊው የግብይት ማዕከል በ4 ኪሎ

- **የገበያ ማዕከሉ የነዋሪውን ኢኮኖሚያዊ ብሎም ማህበራዊ ተጠቃሚነት በማረጋገጥ ረገድ ሚናው የላቀ መሆኑ ተገልጿል**

**በሄለን ጥላሁን**

በእግር የመጓዝ ልምድ ካለዎት ከጥቂት ዓመታት በፊት በአዲስ አበባ ከተማ ላይ የነበሩትን የእግረኞች መንገድ ገፅታ ማስታወስዎ አይቀርም፡፡ በእነዚያ መንገዶች እንደ አሸዋ፣ ድንጋይ፣ ጠጠር እንዲሁም ሲሚንቶ ያሉ የተከመሩ የግንባታ ግብዓቶች እና ተረፈ ምርቶች፣ እንደ ሥራ ቦታ ማስፋፊያነት የሚጠቀሙ የንግድ ተቋማት፣ ሕገ ወጥ የመንገድ ዳር ንግዶች የመሳሰሉት እንቅፋት ሆነው ማስቸገራቸው ይታወሳል። ይህ ሁኔታ የእግረኛውን እንቅስቃሴ በማስተጓጎል ለትራፊክ አደጋ ጭምር ተጋላጭ ከሚያደርጉ ምክንያቶች መካከል ግንባር ቀደም ተጠቃሽ ስለመሆኑ በርካቶች ምስክር ናቸው፡፡ አዲስ አበባን የማይመጥን ገፅታ ተላብሶ የቆየው ሰዎች ማፋሰሻ ቱቦዎችን፣ አጥሮችን እንዲሁም ወንዞችን እንደመጸዳጃ እና ቆሻሻ ማስወገጃ የመጠቀሙ ጉዳይ ለእግረኛ ተጓዥ የጤና ጠንቅ እስከመሆን ደርሶ የነበረ የቅርብ ጊዜ ትዝታችን ነው፡፡



ፎቶ በመባጽዮን ሀ/ገብርኤል

በ4 ኪሎ የገበያ ማዕከል ለግብይት ከተዘጋጁ መካከል የፍራፍሬ ምርቶች እና አልባሳት ይገኙበታል

እነዚህ ከላይ የጠቀስናቸው የመዲናዋ የቀደሙ ገፅታዎቸ አሁን ላይ እጅግ በሚያስደንቅ ሁኔታ ተለውጠዋል። ለውጡን ለመታዘብ በየጎዳናዎቹ መንቀሳቀስ፣ ዓይንን ገልጦ መመልከት፣ ያለፈውን የከተማዋን ገፅታ ማስታወስ እና ሚዛናዊነት ባለው አዕምሮ ማነጻጸር በቂ ነው፡፡ እኔም፤ ከአምስት ኪሎ ወደ አራት ኪሎ የሚወስደውን መንገድ ግራና ቀኝ እያማተርኩ በተጓዝኩበት ወቅት የተመለከትኩት የከተማዋ ዕድገት እና መሻሻል አድናቆት ፈጥሮብኛል። እንደስሟ አዲስ ሆና የተሞሸረችው አዲስ አበባ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ እየተሠሩ ባሉ የኮሪደር ልማት ሥራዎች እየተደመምኩ መዳረሻዬን በመሐል አራት ኪሎ ተገንብቶ በቅርቡ ለአገልግሎት በበቃው የአራት ኪሎ የገበያ ማዕከል አደረግሁ፡፡

በመዳረሻዬ የተመለከትኩት ለውጥ በጣም የሚያስደንቅ ሆኖ አግኝቼዋለሁ። ከዚህ ቀደም ይህ አካባቢ በጠባቡ የእግረኛ መንገድ ላይ የጎዳና ንግድ ታክሎበት የእግረኛውን የመንቀሳቀስ መብት ያስተጓጉል ነበር፡፡ አሁን ባለው ገጽታ አይደለም ለእግረኛ ቀርቶ ለባለ ሁለት እግር ተሽከርካሪ (ሳይክል) መንጃ ምቹ የሆነ መንገድ እንዲሁም በሰፋፊ የእግረኛ መንገድ ላይ እንቅስቃሴ ሲያደርጉ ቢደክሞት እንኳን አረፍ የሚሉበትና ጋዜጣ የማንበብ ፍላጎትዎን የሚያረካ ስፍራ ተዘጋጅቷል፡፡ በተለይ ወደ አራት ኪሎ የገበያ ማዕከል ጎራ ሲሉ ለመኪናዎ ደህንነትዎ ምቹ የሆነ የማቆሚያ ስፍራ ተዘጋጅቷል፡፡

የአራት ኪሎ የገበያ ማዕከል የነዋሪውን ኢኮኖሚያዊ ብሎም ማህበራዊ ተጠቃሚነት በማረጋገጥ ረገድ ሚናው የላቀ መሆኑን የዝግጅት ክፍላችን ያነጋገራቸው በማዕከሉ ምርትና አገልግሎት ለመሸጥ የገቡ ነጋዴዎች እንዲሁም ግብይት የሚፈፅሙ ነዋሪዎች ምስክርነታቸውን ሰጥተዋል፡፡ ከእነዚህ መካከል፡- በኪዊንስ ሱፐር ማርኬት ብርቱካን፣ አቮካዶ… ሲሸምቱ ያገኘናቸው አቶ ብሩክ ቡልቻ አንዱ ናቸው፡፡ ለምን ይህንን ሱፐር ማርኬት እንደመረጡ ላቀረብንላቸው ጥያቄ፤ የኪዊንስ ሱፐር ማርኬት ከዚህ ቀደም ማዕከሉን ፒያሳ አድርጎ ምርቶቹን በሚሸጥበት ጊዜ የረጅም ጊዜ ደንበኛ መሆናቸውን በማስታወስ፤ ሱፐር ማርኬቱ በምርቶቹ ጥራት እና በዋጋ ተመጣጣኝነቱ በሸማቹ ሕብረተሰብ የሚመረጥ ነው፡፡ የእሳቸውም አመጣጥ ያ ጥሩ ስምና ዝና ያለው የንግድ ተቋም አዲስ በተከፈተው የአራት ኪሎ የገበያ ማዕከል ሥራ መጀመሩን በመስማታቸው እንደሆነ ገልፀውልናል፡፡

እንደ አቶ ብሩክ ገለፃ፤ ወደኪዊንስ ሱፐር ማርኬት ከመጡ ከሚገዟቸው ምርቶች አንዱ ብርቱካን ነው፡፡ እኛም በተገኘንበት ዕለት አንዱን ኪሎ ብርቱካን በ109 ብር፣ አቮካዶም እንዲሁ በ54 ብር ገዝተዋል፡፡ እነዚህን ምርቶች አካባቢያቸው ላይ ካለ የፍራፍሬ መሸጫ ሱቅ የሚገዙት ብርቱካን በ200 ብር እና አቮካዶ በ58 ብር ነው፡፡ አራት ኪሎ ይህንን የመሰለ የገበያ ማዕከል መገንባቱ በአካባቢው እንቅስቃሴ ለሚያደርግ ሰው ጥሩ የገበያ አማራጭ የፈጠረ ነው፡፡

ለመኪናቸው ደህንነት ምንም ሳይጨነቁ ተረጋግተው በሌሎች ሱቆች የሚፈልጓቸውን ነገሮች ከሸመቱ በኋላ ትንሽ አረፍ ብለው፤ ሻይ ቡና በማለት ለራሳቸው ጥሩ ጊዜ እንዳገኙ የሚናገሩት አቶ ብሩክ፣ አብዛኛውን ጊዜ በሥራ ተወጥረው እንደሚያሳልፉ፣ በሥራ አካባቢያቸው ሁሉንም እቃ በአንድ ቦታ መሸመት የሚያስችል እንዲህ አይነት የገበያ ማዕከል እንደሌለ እንዲሁም ጊዜን ብሎም ጉልበትን እንደሚቆጥብ መስክረዋል፡፡ በማዕከሉ የቀረቡ ምርቶች ከዋጋ አንፃር ተመጣጣኝ መሆናቸውንም አንስተዋል፡፡

በማዕከሉ የኪዊንስ ሱፐር ማርኬት ስራ አስኪያጅ አቶ መኪ ዲጋ ለዝግጅት ክፍላችን በሰጡት ማብራሪያ፤ በምግብ የፍጆታ እቃዎች ላይ ተገቢውን ቅናሽ በማድረግ የነዋሪውን ፍላጎት መሰረት ያደረጉ ምርቶች ለገበያ እያቀረቡ መሆኑን ተናግረዋል፡፡ አስራ ሁለተኛ ቅርንጫፍ በሆነው የአራት ኪሎ የገበያ ማዕከል ውስጥ የሚገኘው ኪዊንስ ሱፐር ማርኬት ከሚድሮክ እህት ኩባንያዎች ከሆነው የእርሻ ልማት የሚገኙ ምርቶች ላይ ቅናሽ በማድረግ ለተጠቃሚዎች እየተሸጠ ይገኛል፡፡ በቅናሽ ዋጋ የሚያቀርቧቸው የአግሮ ኢንዱስትሪ ምርቶች እንዲሁም የአትክልትና ፍራፍሬ ውጤቶች በስፋት በሸማቾች ዘንድ ተፈላጊ ናቸው፡፡ ለዚህ ደግሞ ከዋጋ አንፃር ተመጣጣኝ ብሎም የሸማቹን ኪስ የማይጎዳ መሆኑን ጠቅሰዋል፡፡

የሚድሮክ እርሻ ልማት ውጤት የሆኑት የፍራፍሬ ምርቶች እንደ ብርቱካን፣ አቮካዶ፣ ፓፓያ፣ ካሮት የመሳሰሉ እንደቅደም ተከተላቸው በኪሎ ግራም በ109፣ በ54፣ በ40 እና በ72 ብር ለህብረተሰቡ ተደራሽ ለማድረግ ተችሏል፡፡ በአራት ኪሎ የገበያ ማዕከል ውስጥ ይህን መሰል አገልግሎት መስጠት መቻላቸው የከተማዋን ነዋሪ በቅርበት ለመድረስ እንደሚያስችላቸውም አብራርተዋል፡፡

በገበያ ማዕከሉ ያደረግነው ቅኝት አላበቃም፡፡ ሌላኛው መዳረሻችንን ያደረግነው በፀሃይ ኮስሞቲክስ ሱቅ ነው። በዚህ ሱቅ የተለያዩ ዘመናዊ ልብሶች፣ የመዋቢያ እቃዎች እንዲሁም ቦርሳዎችን ሲሸጡ ያገኘናቸውን ወይዘሮ እፀገነት አስፋው አነጋግረናል፡፡ የቀድሞዋ አራት ኪሎ አሁን ላይ ተውባ እና የዘመኑ የአሰራር ሂደቶችን ተከትላ መታደሷ ወደ አካባቢው ለሚመጣ ሠው ጥሩ ቆይታ የሚያደርግበትን ገፅታ እና ምቹ ሁኔታ የፈጠረ መሆኑን መስክረዋል፡፡ ወደ አካባቢው የመጡና ወደ ግብይት ማዕከሉ ጎራ ያሉ እንደየ ፍላጎታቸው ሸምተው መሄድ የሚችሉበት ሁኔታ ተፈጥሯል። ጥሩ የሆነ የመኪና ማቆሚያ ተገንብቶ ለአገልግሎት መብቃቱ ተሽከርካሪ ይዞ የሚመጣ ሠው ያለአንዳች መቸገር የሚፈልገውን ግብይት ጊዜ ወስዶ መፈፀም የሚችልበት ሁኔታ የሚፈጥር መሆኑን አስረድተዋል፡፡

እንደ ወይዘሮ እፀገነት ገለፃ፤ በሱቃቸው ከ600 ብር እስከ 2 ሺህ ብር የሚያወጡ የተለያዩ ዘመናዊ አልባሳት አሏቸው፡፡ የመዋቢያ ቁሳቁሶች እንደ የጆሮ ጌጥ፣ ፀጉር ማስያዣ የመሳሰሉት እንዲሁ ከ200 ብር አንስቶ እስከ 500 ብር ድረስ ይሸጣሉ። የገበያ ማዕከሉ ከየትኛውም አቅጣጫ ለሚመጣ ሸማች ለትራንስፖርት ምቹ በሆነ ስፍራ ላይ እንደሚገኝ ገልፀዋል፡፡

“የአራት ኪሎ የገበያ ማዕከል ሥራ መጀመሩን ከጓደኞቼ ጋር በእግር ጉዞ በምናድግበት ወቅት ነው ያወቅነው” የምትለው ወጣት ሃና፤ በማዕከሉ ተንቀሳቅሳ የሱቆቹን የምርት ዓይነት በመመልከት አድንቃ ብቻ አልተመለሰችም፡፡ የሚያስፈልጓትን ምርቶች በተመጣጣኝ ዋጋ በማግኘቷ ጊዜ ሳታጠፋ ገዝታለች፡፡ ይህንን አስመልክቶ እንደገለፀችልን፤ ልብስ በ1 ሺህ 200 ብር፣ ጫማ በ1 ሺህ 500 ብር፣ የፀጉር ቅባት በ300 ብር እንዲሁም ሻምፖዎችን በ500 ብር ገዝታለች፡፡ ይህም ከዚህ ቀደም በሌሎች ሱቆች ትገዛው ከነበረው አንፃር በዋጋ ቅናሽ ያለው መሆኑን አብራርታለች፡፡

ሌሎችም ጥሩ ለአይን ማረፊያ የሆኑ ባህላዊ ቁሳቁሶች መሸጫ መኖሩን መታዘቧን የምትናገረው ወጣት ሃና የተለያዩ ትኩስ ፍራፍሬዎችንም በዚሁ የገበያ ማዕከል ማግኘት መቻሏን አክላለች፡፡

በቅርቡ የአዲስ አበባ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ የ4 ኪሎ የገበያ ማዕከልን፣ መኪና ማቆሚያን እና 4 ኪሎ ፕላዛን መርቀው ለአገልግሎት ክፍት ማድረጋቸው ይታወሳል። ፕሮጀክቶቹ ከመሬት በታች የተገነቡ እጅግ ዘመናዊ 102 የስጦታ እና የአልባሳት መደብሮች፣ ካፍቴሪያዎች፣ ማንበቢያ ስፍራዎች፣ ሱፐር ማርኬቶች፣ ከ100 በላይ ተሽከርካሪዎችን በአንድ ጊዜ የሚያስተናግድ የመኪና ማቆሚያ እና በአንድ ጊዜ እስከ 5 ሺህ ሰዎችን መሰብሰብ የሚያስችል የፕላዛ፣ የአንፊ ቴአትርና የተለያዩ የጥበብ ስራዎችን ማቅረቢያ ስፍራዎችን መያዛቸውን፤ የሲቪል ተሳትፎን፣ የባህል ዕድገትን፣ የእግር ጉዞን የሚያበረታቱ፣ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የታገዙ፣ ሁሉንም የህብረተሰብ ክፍል በተለይም አቅመ ደካሞችና አካል ጉዳተኞችን ታሳቢ ያደረጉ መሆናቸውን ከንቲባዋ በማህበራዊ የትስስር ገጻቸው ያጋሩት መረጃ ያመላክታል።

አዲስ ልሳን ጋዜጣ በሐምሌ 26 ዕትሟ “የ4 ኪሎ ፈርጦች” በሚር ርዕስ ባስነበበችው ጽሑፍ ላይ በኢትዮጵያ የኢኮኖሚክ አሶሴሽን ከፍተኛ ተመራማሪ ሞላ አለማየሁ (ዶ/ር) እንደገለጹት፣ አንዲት ከተማ ምቹ ለመባል መሰረታዊ የሆኑ አገልግሎቶችን ማሟላት አለባት። ከዚህ በተጨማሪም ነዋሪዎች የተሻለ የሚዝናኑበትን መሰረተ ልማት ማሟላት ይኖርባታል፡፡ በአጠቃላይ ዜጎች የሚፈልጉትን መሰረተ ልማት በበቂ ሁኔታና በጥራት ማቅረብ የምትችል ከተማ ለኑሮ ምቹ ነች ተብሎ ይታሰባል፡፡

የአንድ መስኮት አገልግሎት የሚባሉ አሰራሮች በመላው አለም እየተለመዱ መጥተዋል የሚሉት ሞላ (ዶ/ር)፣ የአራት ኪሎ ፕሮጀክቶች ንግድ ያቀላጥፋሉ፤ ጊዜን ይቆጥባሉ፤ የስራ እድል ይፈጥራሉ፤ ሻጭና ገዥን በአንድ ያገናኛሉ፣ የኑሮ ደረጃን ያሻሽላሉ፤ ምክንያቱም ብዙ አገልግሎቶችን በአንድ የያዘ ማእከል ነው፡፡ ስለዚህ ከተማዋን ምቹ ከማድረግ በተጨማሪ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታውም ከፍተኛ ነውና ወደ ሌሎች ቦታዎች መስፋፋት እንዳለባቸው አብራርተዋል፡፡

# መጥፎ ገጠመኞችን የሸኙ ጎዳናዎች

## “ከጓደኞቼ ጋር ስጓዝ ባልተዘጋ ጉድጓድ አብረን ገብተን እናውቃለን”

ወጣት ሙላት ብርሃን



ፎቶ በመባጽዮን ሀ/ገብርኤል

ወጣት ሙላት ብርሃን

ፎቶ በመባጽዮን ሀ/ገብርኤል

ወታደር ለማ ዲሚሉ

**በሄለን ጥላሁን**

ወጣት ሙላት ብርሃን የዓይን ብርሃኑን ያጣው ከ7 ዓመት በፊት ነው፡፡ ሆኖም በርካታ ነገሮችን ለመረዳት ደቂቃም አይፈጅበትም፡፡ የዝግጅት ክፍላችን በኮሪደር ልማት የተሰሩ መንገዶች ላይ ቅኝት ለማድረግ አራት ኪሎ በተገኘንበት ወቅት ነው ያገኘነው፡፡

“ከዚህ ቀደም የአዲስ አበባ ጎዳናዎች አካል ጉዳተኛውን ታሳቢ ያደረጉ ነበሩ ወይ? ስንል ላቀረብንለት ጥያቄ በአንድ ወቅት ከደረሰበት አጋጣሚ ጋር አስተሳስሮ እንደሚከተለው ገልጾታል። “ከአራት ኪሎ ወደ አምስት ኪሎ የሚወስደውን መንገድ ይዘን ከትምህርት ቤት ጓደኛዬ ጋር በእግር ስንጓዝ ባልተዘጋ ጉድጓድ ውስጥ አብረን ገባን። ለበርካታ ሰዓታት እየጮህን ሰዎች እንዲረዱን ብንጣራም ማንም በአግባቡ ሊሰማን አልቻለም ነበር፡፡ እኛም ውስጥ ሆነን የደረሰብን የከፋ ጉዳት ባለመኖሩ አምላካችንን በማመስገን አረፍ ካልን በኋላ በኬናችን (የአይነ ስውራን መንገድ መምሪያ ነጭ በትር) ከፍ አድርገን አንኳኳን። በስተመጨረሻም ሰዎች ደረሱልን፡፡ አሁን ላይ ያ ክፍት የነበረው ቱቦ ተስተካክሏል” ሲል አጫውቶናል፡፡

“አዲስ አበባ ድሮ እና ዘንድሮ የነበራት ገጽታ እንዲህ በቀላሉ የሚተረክ አይደለም” የሚለን ወጣት ሙላት፣ አሁን ባለው ተጨባጭ ሁኔታ ለዓይነ ስውራን ምቹ ሁኔታዎች ተፈጥረዋል። የመንገድ ጉዞ ሳደርግ መንፈሴ ይታደሳል። በመናፈሻዎች አካባቢ ለመዝናናት ሩቅ መንገድ እንሄድ ነበር፡፡ አሁን ግን በአቅራቢያችን የውሃ ፏፏቴ እየሰማን እንዲሁም ከዛፎች የምናገኘውን መልካም አየር እየማግን ተፈጥሮን እንድናደንቅ መልካም እድል ተመቻችቶልናል፡፡

የመፀዳጃ አገልግሎትም ቢሆን በየአቅራቢያችን ስለተዘጋጁ ካለምንም ስጋት ለአካል ጉዳተኛው በተመቻቹ ስፍራዎች እንጠቀማለን፡፡ ለዚህም ጥሩ የስልጣኔ ማሳያ እንዲሁም ለዜጎቿ ምቹ የሆነች አዲስ አበባን ለማየት መቻላችን ትልቅ እፎይታ ነው፡፡ ፈጣሪ ቢፈቅድና የአይን ህክምናዬን በስኬት ለማጠናቀቅ ከቻልኩ አዲሲቷን አዲስ አበባ በመልክ አያታለሁ የሚል እምነት አለኝ” ሲልም አክሏል፡፡

የሀገር ፍቅር መገለጫው ብዙ ነው፡፡ ሌላኛው ባለታሪካችን በውትድርና ሙያ በነበሩበት ወቅት ሁለት እግራቸውን ያጡት ወታደር ለማ ዲሚሉ ናቸው። በደረሰባቸው የአካል ጉዳት ሳይበገሩ በዊልቸር ተጉዘው ጉዳያቸውን ያስፈፅማሉ፡፡

እንደ ወታደር ለማ ገለፃ፤ ለአፍታም ቢሆን በቤት ውስጥ መቀመጥን አይፈልጉም፡፡ ታድያ የአዲስ አበባ ጎዳናዎች እንደ እሳቸው ላሉ አካል ጉዳተኞች በነጻነት ለመንቀሳቀስ ምቹ አልነበሩም፡፡ ተከፍተው ያልተዘጉ ጉድጓዶች አካል ጉዳተኛውን ይፈትናሉ። ለተደራራቢ የአካል ጉዳት ተጋላጭ ያደርጋሉ፡፡

የመንገድ ገጠመኛቸው ብዙ እንደሆነ የሚናገሩት ወታደር ለማ፣ በተለይ በክረምት ወራት አስፋልቶቹ ብሎም የእግረኛ መንገዶች ውሃ ስለሚያቁሩ ደልዳላነቱን (ምቹነቱን) ለማወቅ ያስቸግራቸው እንደነበር ነግረውናል፡፡

> “ኮሪደሩ በተሰራባቸው አካባቢዎች ሁሉንም አካል ጉዳተኛ ታሳቢ ያደረገ የመንገድ ስርዓት መኖሩ እንቅስቃሴዎችን እንደ ልብ ለማድረግ አስችሏል”

“መንገዴን ጠብቄ ስሄድ መለስተኛ በሆነ ጉድጓድ ውስጥ እስከመግባት የደረሰ ነገር ይገጥመኝ ነበር፡፡ ‘አደጋ ይፈጠርብኝ ይሆን’ የሚል ስጋት ገብቶኝ ሰዎችን እንዲያሻግሩኝ አልያም እንቅፋት የሆነብኝን መንገድ እንዲያሳልፉኝ ስጠይቃቸው ‘ሰዓት የለንም፤ አልያም እንቸኩላለን’ በሚል እንደ ባይተዋር ጥለውኝ ይሄዳሉ፡፡ በርግጥ ሁሉም ሰዎች በዚህ ልክ ምላሽ አይሰጡኝም። ሰብዓዊነትን የተላበሱ ሰዎች ከጠየኳቸው በላይ ቀናነታቸውን አሳይተውኛል” ብለዋል፡፡

በመዲናዋ በአብዛኛው በሚባል ደረጃ ለዊልቸር ተብሎ የተዘጋጁ መንገዶች በበቂ ሁኔታ አልነበሩም፡፡ ያሉትም የመንገድ ጠርዞቹ ጎዳናዎችን ለመሻገር ምቹ አልነበሩም የሚሉት ወታደር ለማ፣ አሁን ግን በተለይ ኮሪደሩ በተሰራባቸው አካባቢዎች ሁሉንም አካል ጉዳተኛ ታሳቢ ያደረገ የመንገድ ስርዓት መኖሩ እንቅስቃሴዎችን እንደ ልብ ለማድረግ አስችሏል። በተወሰኑ ርቀቶች የተዘጋጁ የመፀዳጃ ክፍሎች አካል ጉዳተኛውን ታሳቢ ያደረጉ ናቸው፡፡ በረቀቀ እና አስደሳች በሆነ አግባብ የተሰሩ የመንገድ መሰረተ ልማቶች ለአካል ጉዳተኛው ምቹ ሁኔታን ፈጥረዋል፡፡ ረዘም ያለ ጉዞ አድርገን ቢደክመን እንኳን ጥሩ አየር እየወሰድን እረፍት የምናደርግበት ብሎም ተፈጥሮን የምናደንቅበት ሁኔታ ተፈጥሯል። እነዚህ ደረጃቸውን ጠብቀው የተሰሩ ስራዎች በሌሎችም አካባቢዎች መስፋት እንዳለባቸው ተናግረዋል፡፡

አካል ጉዳት ማለት የአዕምሮ፣ የስሜት ህዋሳት እና የአካል መጎዳት ሲሆን ግለሰቡን በማህበረሰቡ ውስጥ እኩል ተሳትፎ እንዳያደርግ የሚገድብ ነው። አካል ጉዳተኝነት በተፈጥሮ ወይም በሰው ሠራሽ ምክንያቶች ይከሰታል። ማየት፣ መናገር፣ መስማት... የማይችል ሰው ማለት ነው፡፡ ስለዚህ በሚሰሩ የልማት ስራዎች እንዲሳተፉ ብሎም ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ ይገባል። በዚህ ረገድ ስለ አካል ጉዳተኞች እና አካል ጉዳተኝነት ግንዛቤን የማሳደግ ሥራ መስራት አስፈላጊ ነው።

የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ጠቅላላ ጉባኤ በታህሳስ ወር 1993 ዓ.ም ያጸደቃቸውን ሃያ ሁለት ደንቦችንና ድንጋጌዎችን ስንመለከትም አካል ጉዳተኞች ምንም ልዩነት ሳይደረግባቸው በህብረተሰቡ ውስጥ ባሉ ሁሉም እድሎች እኩል ተጠቃሚ እንዲሆኑ በግልጽ አስቀምጧል፡፡

የአንድ ሀገር እድገት የተሟላ እንዲሆን አካል ጉዳተኞችን በሁሉም ዘርፍ ማሳተፍና ተጠቃሚነታቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡ ከዚህ አንጻር አዲስ አበባ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በተለይም ደግሞ በኮሪደር ልማቱ ላይ ሁሉንም ታሳቢ ያደረጉ የልማት ስራዎችን እያከናወነች ትገኛለች፡፡ ይህ በጎ ጅምር ከዚህም በላይ እንዲጠነክር በትኩረት መስራት ከእያንዳንዱ ባለድርሻ አካል ይጠበቃል እንላለን፡፡

## የግልጽ ጨረታ ማስታወቂያ

### የጨረታ ቁጥር 001/2018

**በቦሌ ክፍለ ከተማ የወረዳ 02 ፋይናንስ ጽ/ቤት በ2018 በጀት ዓመት የአንደኛ ዙር ግዥ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን በግልጽ ጨረታ አወዳድሮ መግዛት ይፈልጋል።**

| የሎት ቁጥር | የአገልግሎት ዓይነት | የጨረታ ማስከበሪያ (ሲፒኦ) |
|---|---|---|
| ሎት 1 | የእስቴሽነሪ ወይም የጽህፈት መሳሪያ | 10,000 |
| ሎት 2 | የደንብ ልብስ | 5,000 |
| ሎት 3 | የጽዳት እቃ | 10000 |
| ሎት 4 | የትራንስፖርት ኪራይ | 200 |
| ሎት 5 | ህትመት ስራ | 1,000 |
| ሎት 6 | የደንብ ልብስ ለመስፋት | 500 |
| ሎት 7 | የኤሌክተሮኒክስ ጥገና | 200 |

ስለሆነም መስፈርቱን የሚያሟሉ ተጫራጨቾች ቀርበው መወዳደር ይችላሉ፡፡

1. የሃገር ውስጥ ተጫራቾች አግባብነት ያለው በዘመኑ የታደሰ ንግድ ስራ ፈቃድ ማቅረብ የሚችል፡፡
2. የሃገር ውስጥ ተጫራቾች አግባብነት ያለው ንግድ ምዝገባ ማቅረብ የሚችል፡፡
3. የሃገር ውስጥ ተጫራቾች ግብር የመክፈል ግዴታቸውን የተወጡ መሆኑን
4. የሃገር ውስጥ ተጫራቾች የግብር ከፋይነት መለያ ቲን ነምበር ማቅረብ አለባቸው፡፡
5. የሃገር ውስጥ ተጫራቾች የቫት ተመዝጋቢዎች የሆኑ
6. ተጫራቾች የጨረታ ማስረከቢያ ለእያንዳንዱ ሎቶች በባንክ በተረጋገጠ ሲፒኦ/CPO/ ማቅረብ አለባቸው።
7. በአቅራቢዎች ዝርዝር የተመዘገበ መሆን አለበት
8. ተጫራቾች በአማርኛ ቋንቋ የተዘጋጀውን የጨረታ ሰነድ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ለ10 ተከታታይ የስራ ቀናት የሚቆይ ሲሆን በ11ኛ ቀኑ ጥዋት 4 ሰዓት ታሽጎ 4፡30 ይከፈታል ፡፡
9. ለእያንዳንዱ ሎት የማይመለስ የኢትዮጵያ ብር 100/አንድ መቶ ብር/ በመክፈል ፋይናንስ የሥራ ክፍሎች ቦሌ ወረዳ 02 ህንጻ 4ኛ ፎቅ መውሰድ ይቻላል ተጫራቾች የሚወዳደሩበት ዋጋ ሲያቀርቡ ቫት ያጠቃለለና ከላይ የተጠቀሱትን ማስረጃዎች አሟልተው በታሸገ ፖስታ አንድ ኦርጅናልና አንድ ኮፒ ፋይናንስ የሥራ ክፍሎች ቦሌ ወረዳ 02 ግዥ ቡድን ለዚሁ በተዘጋጀው የጨረታ ሳጥን ውስጥ እስከ አስራ አንደኛው (11) የስራ ቀን ከጠዋቱ 4፡00 ሰዓት ብቻ ማስገባት ይኖርባቸዋል፡፡ ሆኖም ግን ይህ ቀን የሥራ ቀን ካልሆነ ቀጥሎ ባለው የመጀመሪያ የስራ ቀን የሚገባ መሆኑን እንገልፃለን፡፡
10. ተጫራቾች በተወዳደሩበት እቃ አይነት ጨረታው ከመከፈቱ በፊት ባሉት ሁለት ቀናት ናሙና ማቅረብ አለባቸው፡፡ ከሰነዱ ጋር የተያያዘውን ስፔስፊኬሽን ማህተም በማድርግ መመለስ አለባቸው፡፡
11. ጨረታው በዚያው ቀን ከ ጠዋቱ 4፡30 ሰዓት ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት ፋይናንስ የሥራ ክፍሎች ቦሌ ወረዳ 02 ህንጻ 4ኛ ፎቅ ይከፈታል፡፡
12. ተጫራቾች የጨረታ አሸናፊ ሆነው የተገኙባቸውን ዕቃዎችን ከአጠቃላይ ዋጋ 10% የውል ማስረከቢያ በማስያዝና ከቡድኑ ጋር የግዥ ውል ስምምነት መፈፀም ይኖርባቸዋል፡፡
13. ከላይ የተጠቀሱትን መስፈርት ሳያሟሉ በጨረታ ላይ ለመሳተፍ መሞከር ከጨረታው ያሰርዛል፡፡
14. መ/ቤት ጠቅላላ ለጨረታው ከቀረበው ብዛት 20% ከፍና ዝቅ ብሎ የግዥ ትዕዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡
15. መ/ቤቱ የተሻለ ዘዴ ካገኘ ጨረታውን በሙሉም ሆነ በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡
16. ከዚህ በፊት በማንኛውም ተቋም በዕቃ አቅርቦትም ሆነ በአገልግሎት አሰጣጥ ችግር ምንም አይነት ጉለት ያልታየበት፡፡

ተጨማሪ ማብራሪያ ካስፈለገ ቦሌ ክ/ከተማ ወረዳ 02 የፋይናንስ የስራ ክፍሎች ግዥ ቡድን 4ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 4.1 ያናግሩን

ለተጨማሪ መረጃ ቢሮ መጥተው መጠየቅ ይችላሉ

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በቦሌ ክ/ከተማ የወረዳ 02 አስተዳደር ፋይናንስ የስራ ክፍሎች ፅ/ቤት**

## የጨረታ ማስታወቂያ ቁጥር 001-2018 ዓ.ም

**የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፕላንና ልማት ቢሮ በ2018 ዓ.ም በጀት ዓመት የተለያዩ ቋሚና አላቂ የቢሮ እቃዎች በግልጽ ጨረታ አወዳድሮ መግዛት ይፈልጋል።**

| ሎት | የሚገዛው የእቃ ዓይነት | የጨረታ ማስከበሪያ (cpo) መጠን በብር | ምርመራ |
|---|---|---|---|
| 1 | ስማርት ዲስፕሌይ ቦርድ እና የተለያዩ ቋሚ የቢሮ እቃዎች | 3000.00 | |
| 2 | የጽህፈት መሳሪያ እና ቀለሞች | 4000.00 | |
| 3 | የደንብ ልብስ | 2000.00 | |
| 4 | ኮምፒዩተር፣ ፎቶ ኮፒ፣ ፕሪንተር፣ ላፕቶፕ፣ ስካነር እና ፕሎተር ጥገናና ሰርቪስ | 2000.00 | |
| 5 | የጽዳት እቃዎች | 2000.00 | |
| 6 | የመኪና ሽታ | 2000.00 | |
| 7 | ህትመት | 2000.00 | |
| 8 | ለወርቃማው ሰኞ የሻይ፣ ቡና፣ የዳቦ መስተንግዶ አቅርቦት እና የመስተንግዶ እቃዎች | 1000.00 | |

በዚህ መሠረት ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን መስፈርቶች የሚያሟሉ ድርጅቶች በጨረታው እንዲሳተፉ ይፈልጋል፡:

1. ተጫራቾች ህጋዊ የታደሰ ንግድ ስራ ፈቃድ፣ የተጨማሪ እሴት ታክስ፣ የግብር ከፋይ ምዝገባ፣ ንግድ ምዝገባ ምስክር ወረቀት እና ወቅታዊ ክሊራንስ ማስረጃ ማቅረብ የሚችሉ መሆን አለባቸው፡፡
2. ተጫራቾች የጨረታው ሰነድ የማይመለስ ብር 500 /አምስት መቶ ብር/ በመክፈል ጨረታው በአዲስ ልሳን ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ለ10 ተከታታይ የስራ ቀናት ቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 4 ለም ሆቴል አካባቢ ኤም ኤ ህንጻ 12ኛ ፎቅ ቤተ መጻፍትና ዶክመንቴሽን ከፋይናንስና ክፍያ ዳይሬክቶሬት ክፍል የጨረታ ሰነዱን መግዛት ይችላሉ፡፡
3. ተጫራቾች የሚወዳደሩበትን ዋጋ በስፔስፊኬሽኑ እና በናሙናው መሰረት ሆኖ ይህ ጨረታ በጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ጀምሮ ለ10 ተከታታይ የስራ ቀናት 11ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 11-02 የግዥ ዳይሬክቶሬት ክፍል ለዚሁ በተዘጋጀው የጨረታ ሳጥን ዋናውንና ኮፒውን በተለያየ ፖስታ በማሸግ ማስገባት ይኖርባቸዋል፡፡
4. ጨረታው በ11ኛዉ የስራ ቀን ከጠዋቱ በ4፡00 ሰዓት ታሽጎ በዕለቱ ጠዋት 4፡30 ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት ይከፈታል፡፡
5. መስሪያ ቤቱ የተሻለ አማራጭ ካገኘ ጨረታውን ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

አድራሻ፡- ቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 4 ለም ሆቴል አካባቢ ኤም ኤ ህንፃ 11ኛ ፎቅ እንገኛለን፡፡

ለበለጠ መረጃ ስልክ ቁጥር 011-8-13-42-08

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፕላንና ልማት ቢሮ**

ዮዲት ጉርጂ አርጋው በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 13 ካርታ ቁጥር ቦሌ13/40/7/4/17628/21532/03 ሴሪ ቁጥር 0126130 የሆነ በጽ/ቤታችን ተመዝግቦ የሚገኝ ይዞታ / የቤት ባለቤትነት ምዝገባ ምስክር ወረቀት/ ካርታ ስለጠፋባቸው በማናቸውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ /ይዤዋለሁ/ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እስከ 30 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ቦሌ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

በቶላ ጉርሙ ሮቢ አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በን/ስ/ላ/ክ/ከ/ወረዳ 02 የሚገኘው የይዞታ ልዩ መለያ /ካርታ/ ቁጥር AA000080204224BA030324 ሴሪ ቁጥር C001981 በጽ/ቤታችን በስማቸው የተመዘገበ የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት(ካርታ) ስለጠፋባቸው በማንኛውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ/ይዤዋለሁ/ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ 90 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርትፍኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የንፋስ ስልክ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው በለሚ ኩራ ክ/ከተማ ክልል ውስጥ የሚገኝ በካርታ ቁጥር ቦ/አያ/142/2531/01 ሴሪ ቁጥር 005726 አዩ ጌታቸው በላቸው ስም ተመዝግቦ የሚገኝ የኮንዶሚንየም ቤት እናት ማህደር ከለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት በማህደር ክፍላችን ተፈልጎ ባለመገኘቱ ማህደራቸውን ልናደራጅላቸው ስለሆነ ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት ቀን አንስቶ በ30 ቀናት ውስጥ በለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት ተቃውሞውን እንዲያቀርቡ እያሳሰብን፣ በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ተቃውሞ የማያቀርቡ ከሆነ በምትኩ በመመሪያው በሚፈቅደው መሰረት ሌላ ካርታ የሚሰጣቸው መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

## የግልጽ ጨረታ የግዥ ማስታወቂያ

### ጨረታ መለያ ቁጥር 001/2018 ዓ.ም

በአዲስ አበባ አስተዳደር በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 05 ፋይናንስ ጽ/ቤት ከዚህ በታች ለተዘረዘሩት ሎት-1 ቋሚ ዕቃ (የመኪና ጎማ፣ ቪዲዮ ካሜራ እና ሞንታርቦ)፣ ሎት2- እስቴሽነሪ ዕቃዎች፣ ሎት-3 የጽዳት ዕቃዎች፣ የሎት-4 የደንብ ልብስ፣ ሎት-5 የመስተንግዶ አገልግሎት፣ ሎት-6 የኪራይ አገልግሎት (መኪና፣ ሞንታርቦ፣ ዲኮር እና ድንኳን ኪራይ አገልግሎት) እና ሎት-7 ጥገና አገልግሎት (ፈርኒቸርና ኤሌትሮኒክስ ጥገና) በግልጽ ጨረታ አወዳድሮ ለመግዛት ይፈልጋል፡፡ በዚህ መሰረት ጨረታውን ለመሳተፍ የሚፈልጉ ሕጋዊ ተጫራቾች የሚከተሉትን መስፈርቶች የሚያሟሉ መሆን አለባቸው፡፡

1. ተጫራቾች በዘርፉ የተሰማሩበት ሕጋዊ ፈቃድ ያላቸውና የዘመኑ ግብር ለመከፈላቸው ማስረጃ ማቅረብ የሚችሉ
2. በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ በአቅራቢነት የተመዘገበና ማስረጃ ማቅረብ የሚችሉ
3. የታደሰ ንግድ ፈቃድ ያለው
4. ተጨማሪ እሴት ታክስ የምዝገባ የምስክር ወረቀት ማቅረብ የሚችል
5. ተጫራቾች ከዚህ በታች የተጠቀሰውን የጨረታ ማስከበሪያ በባንክ የተረጋገጠ C.P.O ማቅረብ አለባቸው።

| የሎት ቁጥር | የሎት ዝርዝር | የተጠቀሰው የጨረታ ማስከበሪያ ሲፒኦ በኢትዮጵያ ብር |
|---|---|---|
| ሎት-1 | ቋሚ ዕቃ (የመኪና ጎማዎች፣ ቪዲዮ ካሜራ እና ሞንታርቦ) | 30000.00 |
| ሎት-2 | እስቴሽነሪ ዕቃዎች (የቢሮ መገልገያ ዕቃዎች) | 30000.00 |
| ሎት-3 | የጽዳት ዕቃዎች | 30000.00 |
| ሎት-4 | የደንብ ልብስ | 30000.00 |
| ሎት-5 | የመስተንግዶ አገልግሎት | 10000.00 |
| ሎት-6 | የኪራይ አገልግሎት (መኪና፣ ሞንታርቦ፣ ድንኳን እና ዲኮር ኪራይ) | 10000.00 |
| ሎት-7 | የጥገና አገልግሎት (ፈርኒቸርና ኤሌትሮኒክስ) | 15000.00 |

6. የጨረታ ሰነዱን ማስታወቂያው ከወጣበት ቀን ጀምሮ በየሎት የማይመለስ ብር 300 /ሶስት መቶ ብር/ በመክፈል የተዘጋጀውን ሰነድ ከተቋሙ ቢሮ ቁጥር 305 እየቀረቡ መግዛት ይቻላል፡፡
7. ተጫራቾች ጨረታው ከወጣበት ቀን አንስቶ ባሉት 10 ( አስር ) ተከታታይ የስራ ቀናት ቢሮ ቁጥር 5 ድረስ በመምጣት ዋጋውን የተሞላበትን የጨረታ ሰነዱን ዋጋውንና ፎቶ ኮፒ ለየብቻው በማሸግ ለዚሁ በተዘጋጀው የጨረታ ሳጥን ውስጥ ማስገባት አለባቸው፡፡
8. ጨረታው በ11ኛው ቀን ከጠዋቱ 4፡00 ሰዓት ታሽጎ በዛው በ11ኛው ቀን ከጠዋቱ 4፡30 ሰዓት ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት ይከፈታል፡፡ የጨረታው መዝጊያና መክፈቻ ቀን የስራ ቀን ካልሆነ በሚቀጥለው የስራ ቀን በተሰጠው ተመሳሳይ ሰዓት ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት ይከፈታል፡፡
9. ተጫራቾች ያሸነፉበትን ዋጋ የውል ማስከበሪያ 10%ማስያዝ አለባቸው፡፡
10. ተጫራቾች ጨረታው ከመከፈቱ በፊት ለሚወዳደሩበት ናሙና ለሚቀርብባቸው ዕቃዎች ናሙና ማቅረብ እና በተጨማሪ የቢሮ መስተንግዶ አገልግሎት ለምትጫረቱ ነጋዴዎች ናሙና ለሚያስፈልጋቸው ዕቃዎች ናሙና ማቅረብ አለባቸው፡፡ ናሙና የማይቀርብባቸው ቋሚ ዕቃዎች መስሪያ ቤቱ ባቀረበው ስፔስፊኬሽን መሰረት ማቅረብ አለባቸው፡፡
11. የጨረታው አሸናፊ ድርጅት ያሸነፈበትን ዕቃ በራሱ ትራንስፖርት መ/ቤቱ ድረስ ማቅረብ ይኖርበታል።
12. መ/ቤቱ ለጨረታው ከቀረበው ዕቃ እስከ 20% የመቀነስ ሆነ የመጨመር መብቱ የጠጠበቀ ነው፡፡
13. መ/ቤቱ የተሻለ አማራጭ ካገኘ ጨረታውን ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

ተጨማሪ ማብራሪያ ካስፈለገ በአካል በመቅረብ ከመገናኛ ወደ 24 ቀበሌ ኮከብ ህንፃ አጠገብ ወረዳ 05 አስተዳደር በመቅረብ 3ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 305 ፋ/ጽ/ቤት መጠየቅ ይቻላል፡፡

ስልክ ቁጥር፡-09-05-60-96-79

**የቦሌ ክ/ከተማ ወረዳ 05 አስተዳደር ፋይናንስ ጽ/ቤት**

በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ አስተዳደር በወረዳ 12 ክልል ውስጥ በካርታ ቁጥር አ/ቃ/2083/5/119905/00 ሴሪ ቁጥር 1624188 በእመቤት በቀለ ዴቢሶ ስም የተመዘገበዉ የቤት ባለይዞታነት እና ባለቤትነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት/ካርታ ስለጠፋባቸው በማንኛውም መልኩ በእጇ ይገኛል የሚል አካል ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ30 ቀን ጊዜ ውስጥ በጽ/ቤታችን ይዘው መቅረብ የሚችሉ መሆኑን እያሳወቅን ይህ ካልሆነ በምትኩ ሌላ የመሬት ይዞታ መብት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እንደሚሰጣቸው እናሳውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ አቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ ቅ/ጽ/ቤት**

## ጨረታ ማስታወቂያ

### በልደታ ክፍለ ከተማ ወረዳ 06 እውቀት ለፍሬ ከፍተኛ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት በ2018 በጀት ዓመት ለመስሪያ ቤቱ ስራ አገልግሎት የሚውሉ፡-

| የሎቱ አይነት | ሎቱ የሚወክለው ዘርፍ | ለየሎቱ የሚያዘው የጨረታ ማሰከበሪያ ሲፒኦ መጠን |
|---|---|---|
| ሎት-1 | የፅፈት መሳሪያ | 15000/አስራ አምስት ሺህ ብር/ |
| ሎት-2 | የደንብ ልብስ | 15000/አስራ አምስት ሺህ ብር/ |
| ሎት-3 | የፅዳት እቃ | 15000/አስራ አምስት ሺህ ብር/ |
| ሎት-4 | ኮምፒውተርና ፕሪንተር | 40000/አርባ ሺህ ብር/ |
| ሎት-5 | ፈርኒቸር | 5000/አምስት ሺህ ብር/ |
| ሎት-6 | መፅሃፍት እና | 1000/አንድ ሺህ ብር/ |
| ሎት 7 | የጀነሬተርና ፎቶ ኮፒ ጥገና | የለውም |

በጨረታ ቁጥር 01/018 አወዳድሮ እቃዎቹን እና አገልግሎቶቹን ለመግዛት ይፈልጋል በመሆኑም በዚህ መሠረት ከዚህ በታች የተጠቀሱትን መስፈቶች የሚያሟሉ ድርጅቶችና ግለሰቦችን በጨረታው እንዲሳተፍ ይፈልጋል፡፡

1. ከላይ በዝርዝር ለተጠቀሱት ዕቃዎች አግባብነት ያለው ሕጋዊ የታደሰ ንግድ ፈቃድ ያላቸው
2. የዘመኑን ግብር የከፈሉ እንዲሁም በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ወይም አዲስ አበባ መስተዳደር ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ በዕቃ አቅራቢዎች ዝርዝር ለመመዝገባቸው የምስክር ወረቀት ማቅረብ የሚችሉና ቫት ተመዝጋቢ የሆኑ እንዲሁም የግብር ከፋይ መለያ ቁጥርና ግብር ክሊራንስ ማቅረብ የሚችሉ መሆን አለባቸው፡፡
3. ተጫራቾች ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ለ10 ተከታታይ የስራ ቀናት ዘወትር በስራ ሰዓት በልደታ/ክ/ከተማ በዕውቀት ለፍሬ ከፍተኛ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት በመገኘት ለሙሉ ሰነድ 200 (ሁለት መቶ ብር ብቻ) በመክፈል የጨረታውን ሰነድ መውሰድ ይችላሉ። ጨረታው የሚዘጋው ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ በወጣ በ11ኛው ተከታታይ የስራ ቀናት ከጠዋቱ 4፡30 ሰዓት ተዘግቶ 5፡00 ይከፈታል፡፡
4. ተጫራቾች እያንዳንዱ ዕቃ እና አገልግሎት የሚሸጡበትን ዋጋ ከነቫቱ መግለጽ አለባቸው፡፡
5. በተራ ቁጥር 1 እና 2 ላይ የተጠቀሱትን ሰነዶች እና ከተቋሙ የሚገዙትን ሰነድ ጭምር ኦርጅናሉን ኮፒ በማድረግ በ2 በተለያዩ ፖስታዎች አስገብቶ ኦርጅናልና ኮፒ ብሎ በመፃፍና በማሸግ ሙሉ አድራሻቸውን በመጥቀስ ሰነዱ ላይ በመፈረም ማህተም በመምታት በዕውቀት ለፍሬ ከፍተኛ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት በግዢ ቢሮ ገቢ ማድረግ አለባቸው፡፡
6. በጨረታ ሰነዱ ላይ ዋጋ በሚሞሉበት ጊዜ ስተት ከተፈጠረ በአንድ መስመር ሰርዞ ካናቱ ፊርማ በማድረግ ማስተካከል ይፈቀዳል ነገር ግን በፍሉድ ማጥፋት እና ስርዝ ድልዝ ማድረግ አይፈቀድም፡፡
7. ተጫራቹ ዋጋ መሙላት ያለበት በተቋሙ ሰነድ ላይ ብቻ ሲሆን ከዚህ ውጪ ሌላ ሰነድ መጠቀም አይፈቀድም፡፡
8. ከተቋሙ ፍላጎት ወይም ስቴሲፊኬሽን ውጪ በራስ ፍላጎት ማርክ ጠቅሶ ዋጋ መስጠት አይቻልም
9. በሰነዱ ላይ ዋጋ በሚሞሉበት ወቅት የማይወዳደሩበትን እቃ ዋጋ መሙያ ቦታውን ባዶ መተው አይፈቀድም፡፡
10. ተጫራቾች የተጠቀሱትን ዕቃዎች በሙሉ ወይም በከፊል መጫረት ይችላሉ በተጨማሪም መደበኛ የጨረታ ሰነዱን በተጫራች የሚሞሉትን እና መፈረም ያለባቸውን ቦታዎች በአግባቡ ሞልቶ ፈርሞ መሃተም አድርጎ መመለስ አለባቸው
11. በጨረታ ለቀረቡት እቃዎች ሳምፕል የሚገቡ እቃዎች የማወዳደሪያ ሰነዱ ላይ ተጠቅሰዋል ናሙና መቅረብ ያልቻሉ እቃዎችን ከውጤት በኋላ በአካል ይዞ በመምጣት ማሳየት እና ትዛዝ ሲሰጠው ማስገባት ይኖርበታል፡፡
12. ከላይ በተጠቀሰው መሰረት CPO በልደታ ክፍለ ከተማ እውቀት ለፍሬ ከፍተኛ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት ስም በማሰራት ማቅረብ ይኖርባቸዋል።
13. አሸናፊ ለሚሆኑ ተጫራቾች የውሉን 10 በመቶ ሲፒኦ ማስያዝ አለባቸው፡፡
14. የጨረታ ማስከበሪያ ሲፒኦ የሚወዳደሩትን የሎት መጠን ያክል ደምሮ በአንድ ሲፒኦ ማሰራት ይቻላል፡፡
15. ጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት አምራች ካልሆኑ በስተቀር በደብዳቤ የማናስተናግድ መሆኑን እናሳውቃለን፡፡
16. አሸንፎ እቃ የሚያቀርብ ድርጅት የካሽ ሪጅስተር ማሽን ሊኖረው ይገባል፡፡

አድራሻ ፡- የቀድሞ 3 ቁጥር ማዞሪያ ቶታል ስልክ 011-8346370

**ልደታ ክ/ከተማ አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት እውቀት ለፍሬ ከፍተኛ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት**

# የሊጉ ጅማሮና ተጠባቂ ጨዋታዎች

**በሳህሉ ብርሃኑ**

እንደ ጎል ዶት ኮም መረጃ የእንግሊዝ ፕሪሚየር ሊግ እስከ 4 ነጥብ 7 ቢሊዮን የሚደርስ የቴሌቪዥን ተመልካች ያለው ተወዳጅ ውድድር ነው፡፡ በጉጉት ሲጠበቅ የነበረውና የዓለማችን ምርጥ ተጫዋቾችና አሰልጣኞች የሚፋለሙበት ይህ ውድድር በትላንትናው ዕለት ተጀምሯል። የተጫዋቾች ዝውውር መስኮት ተሳትፎ፣ የቅድመ ውድድር ጊዜ የወዳጅነት ጨዋታዎች እና የአዳዲስ ታክቲኮች ሙከራ ደግሞ የሊጉ ክለቦች የዝግጅት ምዕራፍ ዋና ዋና ጉዳዮች ነበሩ።



ፎቶ- ከገፀ ድር

በእንግሊዝ ፕሪሚየር ሊግ በጠቅላላው 380 ጨዋታዎች ይከናወናሉ

ክለቦች ለቅድመ ውድድር ዘመን ዝግጅት በዋናነት በአሜሪካ እና በእስያ የሚገኙ ሀገራትን ጎብኝተዋል። በዚህ ጉዞ ወቅት ከሌሎች ታላላቅ የአውሮፓ ክለቦች ጋር የወዳጅነት ጨዋታዎችን በማድረግ አዳዲስ ተጫዋቾችን እና ስልቶችን ሞክረዋል። በውድድርና እረፍት ላይ ሆነው ቀጣዩን የውድድር ዘመን ለማሳመር ድክመታቸውን ማረሚያ መላ ሲፈለጉ ከርመዋል፡፡ እንደዚሁም ባለፈው ዓመት ባስመዘገቡት ውጤት ላይ ተመስርተው አብዛኞቹ ክለቦች በዝውውር ገበያው ላይ ትልቅ ኢንቨስትመንት አድርገዋል። በዚህም ክለቦች የጎደሉባቸውን ቦታዎች በአዳዲስ ተጫዋቾች ለመሙላት እና የተዳከሙ ክፍሎችን ለማጠናከር ጥረት አድርገዋል።

የዓለማችን ባለ ብዙ ተመልካቹ የእንግሊዝ ፕሪሚየር ሊግ የውድድር ዘመን እንደ አርሰናል እና ማንቼስተር ዩናይትድ ያሉ ክለቦች የአዲሱ ውድድር ዘመን ጅማሬያቸው ከግዙፍ ተጋጣሚዎች ጋር አገናኝቶ የውድድሩን ሂደት ገና ከወዲሁ አጓጊ አድርጎታል፡፡ ሻምፒዮን እንዲሆን በተጠበቀበት ያለፈው የውድድር ዘመን ለሦስተኛ ተከታታይ ዓመት በሊጉ 2ኛ ደረጃን ይዞ ያጠናቀቀው የሚኬል አርቴታው አርሰናል አዲሱን የውድድር ዘመን ወደ ኦልድትራፎርድ በመጓዝ ይጀምራል።

በክረምቱ የዝውውር መስኮት ከፍተኛ ተሳትፎ ያደረገው ክለቡ እንደ ትራንስፈር ማርኬት መረጃ እስካሁን ድረስ ለስድስት ተጫዋቾች ግዢ ከ200 ሚሊዮን ፓውንድ በላይ ወጪ አድርጓል፡፡ የ13 ጊዜ የሊግ አሸናፊው አርሰናል የመጀመሪያ ጨዋታውን ከማንችስተር ዩናይትድ ጋር የሚያደርግ ሲሆን፣ በውድድር ዓመቱ በሜዳው የመጀመሪያው ጨዋታ በኤምሬትስ ስታዲየም አዲስ አዳጊውን ሊድስ ዩናይትድ ያስተናግዳል፡፡ ለሶስተኛው ሳምንት መርሃ ግብር ወደ አንፊልድ ተጉዞ ከሻምፒዮኑ ሊቨርፑል ጋር ትልቁን ጨዋታ ያከናውናል፡፡

በ4ኛ እና 5ኛ ሳምንት ኖቲንግሃም ፎረስት እና ማንችስተር ሲቲ የሚኬል አርቴታን ከዋንጫ ማምጣት ግዴታ ጋር የሚጀምር ውድድር ዘመን ሊያከብዱ የተሰለፉ ሌሎች ክለቦች ናቸው።

የአርሰናል እግር ኳስ ክለብ ባለፉት ሶስት የውድድር ዘመናት በተከታታይ የፕሪሚየር ሊጉን ሁለተኛ ደረጃ ይዞ አጠናቅቋል። ቡድኑ በዝውውር መስኮት ላይ ቪክቶር ጂዮኬሬሽን በመሳሰሉ ተጫዋቾች በመጠናከሩ ብዙ ተንታኞች እንደሚሉት ከሆነ፣ አርሰናል ለዋንጫው አሸናፊነት ከፍተኛ ግምት አግኝቷል፡፡

የ2024/25 የውድድር ዘመን በክለቡ የፕሪሚየር ሊግ ተሳትፎ ታሪክ እጅግ አስከፊው ነበርና ለቀጣዩ ተጠናክሮ መቅረብ የማንችስተር ዩናይትድ አሰልጣኝ ሩበን አሞሪምና የክለቡ ኃላፊዎች ቀዳሚ ተግባር ነው። ብራዚላዊውን ማቲውስ ኩንሃን ከወልቭስ፣ ምቡሞን ከብራይተን እንደዚሁም ግዙፉን አጥቂ ቤንያሚን ሼሽኮ ከወደ ጀርመን አስመጥቷል፡፡ ሌሎች ዝውውሮችን ለመጨረስ የሂሳብ መዝገቡን ማስተካከያ መላ እየፈለገ ያለው ዩናይትድ በኦልድትራፎርድ አርሰናልን በማስተናገድ የውድድር ዘመኑን የሚከፍት ሲሆን፣ ከዚያም ወደ ክራቨን ኮቴጅ አቅንቶ ፉልሃምን ከገጠመ በኋላ በሜዳው በርንሌይን ይጋብዛል፡፡

በማንችስተር ደርቢ ወደ ኢቲሃድ በማቅናት ማንችስተር ሲቲን ከሚገጥምበት የ4ኛ ሳምንት መርሃ ግብር መልስ በሜዳው ከቼልሲ ጋር የሚያደርጋቸው ጨዋታዎች የሩበን አሞሪምን ጅምር ከሌሎቹ ክለቦች አንጻር ከባድ እንዲመስል ያደርጉታል።

ከሻምፒዮንነት ደስታቸው መልስ አስደናቂ ዝውውሮችን እየፈፀሙ በሌላ ከፍታ እየመጡ ያሉት ቀዮቹ ሊቨርፑሎች ሚሎሽ ኬርኬዝን ከወሰዱበት ቦርን ማውዝ ጋር በሚያደርጉት ጨዋታ አዲሱን የውድድር ዘመን እንደሚከፍቱ የሊጉ መርሃ ግብር መረጃ ያሳያል፡፡ ኒውካስል ዩናይትድ የመርሲሳይዱ ክለብ የውድድር ዓመቱ የመጀመሪያ እውነተኛ ፈተና ሊሆን 2ኛ ሳምንት ላይ በሜዳው ይጠብቃቸዋል፡፡ በሦስተኛ ሳምንት መርሃ ግብር ያለፈው የውድድር ዘመን ተከታያቸው አርሰናልን የሚገጥሙበት ጨዋታ የአርነስሎትን ቡድን መልክ የማሳየት አቅም አለው። በ4ኛ ሳምንት በአንፃራዊነት ቀለል ባለው መርሃ ግብር ከበርንሌይ ጋር ከተጫወተ በኋላ በመርሲሳይድ ደርቢ ብርቱ ፉክክር የሚደረግበትን ጨዋታ ከሜዳው ውጭ ያደርጋል ይላል ቢቢሲ ያጋራው መረጃ፡፡

የሊቨርፑል እግር ኳስ ክለብ ባለፈው የውድድር ዘመን በአርነስሎት አመራር ስር የፕሪሚየር ሊጉን ዋንጫ ማንሳት ችሏል። ቡድኑ ጥቂት ወሳኝ ተጫዋቾችን ቢሸጥም፣ በዝውውር ገበያ ላይ ከፍተኛ ገንዘብ በማውጣት እንደ ፍሎሪያን ዊርትዝ እና ሌሎችም ኮከብ ተጫዋቾችን አስፈርሟል። ይህ ደግሞ ይበልጥ ጠንካራ ተፎካካሪ እንደሚያደርገውና በዚህም ምክንያት የዘንድሮው የዋንጫ ለአሸናፊነት የተሰጠው ግምት ከፍተኛ ሆኗል።

ከውጤት አንፃር ዥንጉርጉር መልክ ካለው የውድድር ዘመን በኋላ በዝውውር መስኮቱ በንቃት በመሳተፍ ራሱን እያጠናከረ ያለው ማንቸስተር ሲቲ የ2025/26 ተጋጣሚዎቹን ያወቀው በዓለም ክለቦች ዋንጫ ተሳትፎ ላይ ሆኖ ነው። ያለ በቂ እረፍትና ዝግጅት በአዲሱ የውድድር ዘመን በመክፈቻው መርሃ ግብር ወልቭስን የሚገጥም ሲሆን ቶተንሃም፣ ብራይተን፣ ማንችስተር ዩናይትድ እና አርሰናል በመጀመሪያዎቹ አምስት ሳምንታት የሚገጥማቸው ቡድኖች ናቸው።

ሎስ አንጀለስ ኤፍሲን በማሸነፍ የዓለም ክለቦች ዋንጫ ጅምሩን ያሳመረው የኤንዞማሬስካው ቡድን ቸልሲ ከአሜሪካ ሲመለስ ወደ ሊግ ሻምፒዮንነት መንበር የመጠጋት ዓላማ እንደሚኖረው ይጠበቃል። በመጀመሪያዎቹ ሳምንታት ከአራት የለንደን ክለቦች ጋር በመጫወት የ2025/26 ውድድር ዘመንን የሚጀምሩት ሰማያዊዎቹ፣ በግዝፈት ምድብ እኩዮቻቸው ከሆኑት ክለቦች አንጻር ቀለል ያሉ ተጋጣሚዎች ያገኙ ይመስላሉ።

ከክሪስታል ፓላስ፣ ዌስትሃም ዩናይትድ፣ ፉል ሃም እና ብሬንት ፎርድ ጋር የሚጫወተው ቼልሲ አምስተኛው ሳምንት ላይ ከሜዳው ውጭ ማንችስተር ዩናይትድን ይገጥማል። በተለይም በዓለም የክለቦች ዋንጫ ምክንያት በቂ የማገገሚያ እረፍት አለማግኘታቸው የምዕራብ ለንደኑ ክለብና የጣልያናዊው አሰልጣኝ ፈተና ይመስላል።

በፈረንሳዊው አሰልጣኝ ሬጂስ ለብሪስ እየተመራ ሰንደርላንድ ከስምንት ዓመታት በኋላ ወደ እንግሊዝ ፕሪሚየር ሊግ የተመለሰው ሊድስ ዩናይትድ፣ በርንሌይ እና ሰንደርላንድ ወደ ፕሪሚየር ሊጉ ማደጋቸው ይታወቃል። ኢፕስዊችታውን፣ ሌይስተር ሲቲ እና ሳውዝሃምፕተን በተቃራኒው ከእንግሊዝ ፕሪሚየር ሊግ ወደ ሻምፒዮንሺፕ የወረዱ ክለቦች ናቸው።

## የሊጉ አዳዲስ ህጎች

የ2025/26 የእንግሊዝ ፕሪሚየር ሊግ የውድድር ዘመን የጨዋታውን ፍጥነት እና ፍትሃዊነት ለማሻሻል ታስበው የመጡ አዳዲስ ህጎች አሉ። እነዚህ ህጎች በተለይም የግብ ጠባቂዎችን ባህሪ፣ የተጫዋቾችን ከዳኞች ጋር የሚያደርጉትን ግንኙነት እና የቫር ቴክኖሎጂ አጠቃቀምን ይመለከታሉ።

የጨዋታ ጊዜን ማባከን ለመከላከል የግብ ጠባቂዎች ኳሱን በእጃቸው መያዝ የሚችሉበት ጊዜ ከስድስት ወደ ስምንት ሰከንዶች ከፍ ብሏል። ይህ ህግ ቀድሞም የነበረ ቢሆንም ብዙ ጊዜ ተግባራዊ አይደረግም ነበር። አሁን ግን ዳኞች ከ5 ሰከንድ ጀምሮ በጣት ምልክት ጊዜውን ያሳያሉ፤ ከስምንት ሰከንድ በላይ የያዘ ግብ ጠባቂ ቡድኑ ላይ የማዕዘን ምት (corner kick) እንዲሰጥበት ያደርጋል አዲሱ ህግ።

በሌላም በኩል ጨዋታ ላይ ብዙ ተጫዋቾች ዳኛን ከብበው ሲከራከሩ የሚታየውን ሁኔታ ለመቀነስ፣ አሁን ላይ ከዳኛው ጋር ስለ ውሳኔዎች መወያየት የሚችለው የቡድኑ አምበል ብቻ እንደሆነና ከሱ ውጪ ያለ ተጫዋች ሳይፈቀድለት ወደ ዳኛው ከቀረበ ቢጫ ካርድ ሊሰጠው እንደሚችል ተደንግጓል።

ከፊል- አውቶማቲክ የጥፋት (Offside) ቴክኖሎጂ ባለፈው የውድድር ዘመን መጨረሻ ላይ መተግበር የጀመረ ሲሆን፣ በዘንድሮው የውድድር ዘመን ሙሉ በሙሉ አገልግሎት ላይ ይውላል ተብሏል። ይህም የጥፋት ውሳኔዎችን በፍጥነትና በትክክል ለመወሰን እንደሚረዳና የቫር ውሳኔዎች ላይ የሚፈጠረውን መዘግየት እና ውዝግብም እንደሚቀንስ ይጠበቃል። እንደዚሁም ውሳኔዎችን ይበልጥ ግልጽ ለማድረግ ይረዳ ዘንድ በዘንድሮው የውድድር ዘመን ዳኞች የቫር ውሳኔዎችን ከገመገሙ በኋላ፣ ውሳኔውን በስታዲየሙ ድምፅ ማጉያ (public address system) አማካኝነት ለደጋፊዎች እንዲያብራሩ ይፈቀድላቸዋል።

> የተጫዋቾች ዝውውር መስኮት ተሳትፎ፣ የቅድመ ውድድር ጊዜ የወዳጅነት ጨዋታዎች እና የአዳዲስ ታክቲኮች ሙከራ የሊጉ ክለቦች የዝግጅት ምዕራፍ ዋና ዋና ጉዳዮች ነበሩ

የእንግሊዝ ፕሪሚየር ሊግ አወዳዳሪው አካል ይፋ ያደረገው ሌላኛው ህግ የፍጹም ቅጣት ምትን የተመለከተ ሲሆን አንድ የፔናሊቲ ምት የሚመታ ተጫዋች ኳሷን ድንገት ሁለት ጊዜ ቢነካት፣ ቀድሞ የነበረው ቅጣት ተሰርዞ ፔናሊቲው እንደገና እንዲመታ ይደረጋል። ይህም ባልታሰበ ስህተት ምክንያት የቡድኑን ጥቅም እንዳይቀንስ ይረዳል ተብሎ ታምኖበታል። እነዚህ አዲስ የሚተገበሩ ህጎችም በጨዋታው ላይ ትልቅ ተጽእኖ ይኖራቸዋል ተብሎ ይጠበቃል።